# ሰመመን

ሲሳይ ንጉሡ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
1978
አዲስ አበባ

# ሰመመን

ከሲሳይ ንጉሡ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
1978
አዲስ አበባ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
Kuraz Publishing Agency

ስልክ / TEL. 11 27 19 — ፖስታ ሣ. ቁ. / P. O. Box 30933

አዲስ አበባ — ADDIS ABABA
ኢትዮጵያ — ETHIOPIA

፩ኛ እትም ጥቅምት ፲፱፻፸፫
፪ኛ እትም ታህሳስ ፲፱፻፸፫
፫ኛ እትም ግንቦት ፲፱፻፸፮

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ።
ALL RIGHTS RESERVED

የሽፋን ሥዕል—ሰብለ ግብረ ሕይወት

ንግድ ማተሚያ ቤት

# ምዕራፍ አንድ

የፍልስፍናው መምህር ዮናታን እጅጉ ፣ የተማሪዎቻቸውን ወረቀት በማረም ላይ ሳሉ ፣ አንድ በግዴለሽነት የተሠራ የጥናት ጽሑፍ ገጠማቸው ። ጽሑፉ የአቤል ሙሉዬ መሆኑን ማመን ስላቃታቸው ፣ ከቢሮአቸው ድረስ አስጠርተው ጠየቁት ።

“ አቤል ፣ ይህ የጥናት ጽሑፍ ያንተ ነውን ? ”
“ አዎ ! የኔ ነው ። ”
“ ስትሠራው ተቻኩለህ ነበር መሰለኝ ? ”

አቤል ስለ ተደናገጠ ዝም አለ ። ቶሎ መልስ አልሰጣቸውም ። ዮናታንም ድንጋጤውን ከገጽታው ላይ ስላነበቡ እንጋገራቸውን ለማቅለል ሞከሩ ።

“ ማለቴ ለዝግጅቱ የሰጠኋችሁ ጊዜ አንሶአችሁም ሊሆን ይችላል ። ”

አሁንም አቤል መልስ አልሰጠም ። የይድረስ — ይድረስ ሥራ መሥራቱን ልቡ ያውቃል ። ጊዜ አንሶት አልነበረም ። እንዲያውም ከተሰጠው ጊዜ አንድ ሳምንት ቀድሞ ነው ያስረከበው ። በመሠረቱ ፣ መምህሩ በሰጡት የጊዜ ገደብ ውስጥ የጥናት ጽሑፍ ተሠርቶ መቅረብ አለበት ። ከዚያ በኋላ የመምህሩ ድርሻ እንደ ሥራው ጥራትና ይዘት ፣ ውጤት መስጠት ነው ። አስተዋዩ ዮናታን ግን ፣ በተበላሸው የአቤል ወረቀት ላይ ሳያመዛዝኑ ርምጃ መውሰድ አልፈለጉም ። ዐይናቸውን ወረቀት ላይ ተክለው በሐሳባቸው የአቤልን ለውጥ ለማጥናት ተገደዱ ።

በአዲስ አበባው ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና ትምህርት ክፍል የዓመቱ ተመራቂዎች ሰባት ናቸው ። ከሰባቱ መሐል አንዱ አቤል ሙሉዬ ነው ። መምህር ከማናቸውም ይልቅ በአቤል ላይ ያላቸው እምነት ላቅ ያለ ነው ። የሦስቱን ዓመት የዩኒቨርስቲ ትምህርት እያጠናቀቀ የመጣው ከፍ ባለ ውጤት

ነው ። ከዚህም በላይ በክፍል ውስጥም ሆነ በውጭ ፣ በግል የሚያቀርበው ጥልቅ ‘ዲያሎግ’ በዮናታን ልብ ውስጥ ትልቅ ቦታ ነበረው ። የዮናታን ምኞት አቤል በከፍተኛ ማዕረግ ተመርቆ የበለጠ ከፍተኛ ትምህርት እንዲከታተል ነው ። “ . . . ታዲያ ይህ የአፋፍ ላይ እንቅፋት ምን ይሆን ? ” ሲሉ ዮናታን ራሳቸውን ጠየቁ ።

ካቀረቀሩበት ወረቀት ቀና ብለው መነጽራቸውን በጣታቸው ሽቅብ ገፋ እያደረጉ ፣ ለአቤል ድንገተኛ ጥያቄ አቀረቡለት ።

“ ዕድሜህ ስንት ነው ? ”

“ ሃያ አንድ ። ”

“ ገና ወጣት ነህ ” አሉት ፣ የደረሰበትን የትምህርት ደረጃ ከዕድሜው ጋር በማነጻጸር ።

“ በአንደኛና በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያለሁ ሦስት ያህል ክፍሎች በእጥፍ ነበር ያለፍኩት ፤ ለዚህ ነው በጊዜ ዩኒቨርስቲ የገባሁት ” አላቸው መገረማቸውን በማየት ።

“ ወላጆችህ በቅርብ ናቸው ? ”

ይህ ድንገተኛ ጥያቄ አቤልን ቢያስደነግጠውም ፣ ከጥናት ጽሑፉ ጉዳይ ወጣ ያለ አርዕስት በመሆኑ ወዶታል ። ይሁንና በተዘዋዋሪም ቢሆን ለዚህ ጥያቄ መንሥኤው የጥናት መበላሸት መሆኑን ሳይገምት አልቀረም ።

“ በቅርብ እንኳ የሉም ። ጎንደር ክፍለ ሀገር ናቸው ” ሲል መለሰ ።

“ የኑሮ ደረጃቸው እንዴት ነው? ”

“ መቼም ጎርሰው ያድራሉ ። ቋሚ የገቢ ምንጭ ግን የላቸውም ” ካለ በኋላ ፣ ድንገት ግልፍ ብሎት ፣ “ ያው እንደ አብዛኛው ኢትዮጵያውያን ወላጆች የእኔኑ እጅ ተጠባባቂዎች ናቸው ” ሲል አከለበት ።

ይህ ከጥያቄአቸው ውጭ ቢሆንም ፣ አንድ አቤል የተመፈረበት ጉዳይ መሆኑን ከአነጋገሩ ለመረዳት ዮናታን ብዙ



ጊዜ አልወሰደባቸውም ። ሆኖም የእሳቸው መንደርደሪያ በአቤል ውስጥ በቅርብ የደረሰ አደጋ ወይም አጋጣሚ እንዳለ ለመረዳት ነበር ። በዚህ ረገድ ቀጥተኛ መልስ ባያገኙም ጥርጣሬአቸውን ለማስወገድ ችለዋል ።

“ ታዲያ . . . ” ብለው ዮናታን መናገር ያሰቡትን ሳይጨርሱ ፣ አጠገባቸው ያለው ቴሌፎን አቃጨለ ። የስልክ ጥሪው የማን መሆኑን በልባቸው ገመቱ ።

“ ሁሉ . . . ሲብሊንግ ” አሉ አንዳች ነገር እንደሚጠብቁ ሁሉ ፊታቸው ላይ ጉጉት እየተነበበ ።

የደወለችው ሚስታቸው ሞኒካ ነበረች ። ንግግራቸው በጀርመንኛ ስለሆነ ፣ አቤል ከዮናታን አፍ ምንም ነገር ሊረዳ አልቻለም ። ነገር ግን የዮናታን ሚስት ጀርመናይት መሆኗን በዩኒቨርስቲው አካባቢ ሲወራ ይሰማ ስለ ነበር ፣ ዮናታን አሁን የሚነጋገሩት ከሷ ጋር መሆኑን ገመተ ።

ሰሞኑን በርሊን ውስጥ የሚገኘው የሞኒካ ወንድም በጠናታም ከባድ ቀዶ ሕክምና እንዲደረግለት እየተጠባበቀ ነበር ። ዮናታንና ሚስታቸውም ይህንኑ ጉዳይ በቴሌፎን በመከታተል አብረው ሲጨነቁ ነው የከረሙት ። የተጠቀሰው ዕለት ደርሶ ሦስት ሰዓት ያህል የፈጀ ቀዶ ሕክምና ከተደረገለት በኋላ ፣ ወንድሟ በሰላማዊ ሁኔታ እንደሚገኝ ዘመዶቿ ከበርሊን ደውለው ለሞኒካ ይነግሯታል ። ሞኒካም ወደ ዮናታን የደወለችው ይህንኑ ልታበሥራቸው ነበር ።

ዮናታን ቴሌፎኑን ከዘጉ በኋላ ፣ በደስታ ስሜት ፊታቸው ፈካ ። ከአቤል ጋር ጀምረውት የነበረውን አርዕስት በዜናው ጣልቃ ገብነት ለማሳጠር ተገደዱ ።

“ . . . እስቲ ለማንኛውም እንደገና እየው ” አሉት ፣ በሚያባብል ድምፅ ።

አቤል በእሽታ ራሱን ነጠ ።

“ ሐሳብ ውስጥ ገብተህ ወይም ተቻኩለህ ይሆናል እንጂ ፣ አንተ እንዲህ ዓይነት ሥራ እንደማትሠራ እተማመናለሁ ” እያሉ ለአቤል ወረቀቱን መልሰው ሰጡት ።

ወረቀቱን ሲቀበላቸው ፊቱ ላይ አንድ ስሜት አነበቡ ። ስሜቱ የገባቸው ይመስል ፣ “ አይዞህ የሦስት ሳምንት ጊዜ ሰጥቼሃለሁ ። ረጋ ብለህ ሥራው ” አሉት ።

አቤል ሲወጣ ከአንድ እሱነቱ ውስጥ ሁለት ስሜቶች እየተሟገቱ ነበር ።

“ ስማ አቤል ! አሁን ወረቀቱን መልስህ የተቀበልካቸው ምን ልትጨምርበት ነው ? የተቻለህን ያህል ሠርተሃል ። ይልቅ ፤ ‘ የማውቀው ይህን ያህል ነው ፤ በቃ ’ በልና መልስላቸው ፤ ያሻቸውን ውጤት ይስጡህ ” ይላል አንዱ ስሜቱ ።

“ ይህን ማመንታትህን ትተህ እንደ ገና በደንብ አጥርተህ ለመሥራት ሞክር ። ተፍጨርጨር ። የመጨረሻ ዓመትህ መሆኑን አትርሳ ። ወላጆችህም በተስፋ የአንተኑ እጅ ጠባቂዎች መሆናቸውን አትርሳ ። የሚወዱህን መምህርም አታስቀይማቸው . . . ” ይላል ሌላው ስሜቱ ።

“ የወላጆችህም ችግር ሆነ የመምህርህ ፍቅር ከችሎታህና ከአቅምህ በላይ ሊያደርግህ አይችልም ። የምትችለው ያንን ያህል ነው ፤ በቃ ! . . . ”

“ እስቲ ለማንኛውም እንደ ገና እየው . . . ”

እንዲህ ስሜቶቹ እየተሟገቱ ከመኝታ ክፍሉ ደረሰ ።

ሦስቱም የመኝታ ክፍል ጓደኞቹ እዚያው ውስጥ ነበሩ ። አቤል ምንም ሳይነግራቸው በቀጥታ ወደ አልጋው ሔዶ በአንድ ጎኑ ዐረፍ አለ ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አቤል ለመኝታ ክፍል ጓደኞቹ ወሬ ማካፈል ቀርቶ ፤ አብረውት መሆናቸውም እያስጠላው ነበር ። ብቸኝነት እያጠቃው ስለ መጣ ፤ ብቸኛ ክፍል ውስጥ ቢሆን ምንኛ በወደደ ! . . . ከራሱ ጋር በመጣላቱ የፈጠረው ጥላቻ እንጂ ፤ ከአንዳቸው ጓደኞቹ ጋር ግጭት አልነበረውም ።

እስክንድር ማንደፍሮ አቤልን ተደራራቢ አልጋ የሚጋራው የመኝታ ክፍል ጓደኛው ነው ። በዩኒቨርስቲው ውስጥ ሦስት ዓመት አብረው ቆይተዋል ። ከመኝታ ክፍል ጓደኝነታቸውም ሌላ ፤ ሁለቱም የፍልስፍና ተማሪዎች ናቸው ። እስክንድር ከአቤል በዕድሜ ላቅ ያለ ሲሆን ፤ በአቤል የትምህርት ጉብዝና ላይ ጤናማ የሆነ ቅናት አለው ።

ሌሎቹ ሁለቱ የመኝታ ክፍል ጓደኞቹ ሳምሶን ከሊሌ እና እምራት ጣሰው ናቸው ። ሁለቱም በግቢው ውስጥ የሚታወቁት በቅጽል ስማቸው ነው ። ሳምሶን ከስሙ ጋር



‘ ጉልቤው ’ የሚል ቅጥያ ስለ ወጣለት ፤ ማንኛውም ተማሪ ሲጠራው ሳምሶን ‘ ጉልቤው ’ እያለ ነው ። እምራት ደግሞ የሚታወቀው ‘ ድብርት ’ በሚል ቅጽል ስም ነው ። በተማሪው ዘንድ ትክክለኛ ስሙ ጭራሽ ተረስቷል ማለት ይቻላል ።

ሳምሶን ‘ ጉልቤው ’ እና አቤል መኝታ ክፍል የመጣው በዚህ ዓመት ነው ። ከእስክንድር ጋር የአንድ ሠፈር ልጆች ስለሆኑ ፤ አንድ የፍልስፍና ተማሪ ፈተና ወድቆ ከወጣ በኋላ ፤ ክፍላቸው ውስጥ ትርፍ መኝታ መኖሩን አይቶ ነው የመጣው ። የሁለተኛ ዓመት የምጣኔ ሀብት ተማሪ ነው ። በአንደኛ ዓመት ትምህርቱ ባገኘው ዝቅተኛ ውጤት ፤ “ ማስጠንቀቂያ ” ውስጥ ቢገባም ስፖርቱን አላቋረጠም ። ስፖርትና ምግብ በጣም ይወዳል ። የዚያኑ ያህልም ሰውነቱን ስላዳበረ ፤ እፍላኑቱ ይፈታተኑዋል ። ለዚህ ነው ‘ ጉልቤው ’ የሚል ቅጥያ የወጣለት ። በዚህ ዓለም ላይ ማንም ሰው የሚ የሚል ቅጥያ የወጣለት ። በዚህ ዓለም ላይ ማንም ሰው የሚ ያሸንፈው አይመስለውም ። እንኳን እሱን ቀርቶ ጓደኞቹን የሚደፍር ከመጣ ፤ “ ማነው እሱ ? እናቱን ! ” ብሎ ማፍጠጥ ነው ። “ ጥርሱን ነው የማወልቀው ! ” — ሌትም ከሆነች ‘ ጥርሷን ነው የማወልቀው ! ’ — የጡንቻ መፈክሮቹ ናቸው ። ሁሌ ሁሉን ሰው እንዳንቀጠቀጠ ነው ። አንድ ቀን ብቻ በአንድ የግቢው ወጣት ተደፍሮአል ።

ሳምሶን የምግብ አዳራሽ ሰልፍ አይወድም ። ሁሌ ጥሶ ሲገባ ነው የሚገባው ። አንድ ቀን እንደ ለመደው ሰልፍ ጥሶ ሲገባ ሲል ፤ ከፊት የነበረ በዕድሜው በሰል ያለ ወጣት በአድራጎቱ በሽቆ ፤ ‘ ጭንቅላት እያለህ ለምን በጡንቻህ ታስባለህ ? በጡንቻው የሚያስብ እህያ ብቻ ነው ” አለው ። ሳምሶን ‘ ጉልቤው ’ ይህን ሰውና ቃላቱን እስከ መቼም አይረሳቸውም ። ካልተደባደብኩ ብሎ ለጊዜው ቢጋበዝም ፤ ከዚያ በኋላ ባላቸው ግንኙነት ለራሱም ከማይገባው ስሜት ወጣቱን ያከብረው ነበር ።

እምራት ፍጹም ዝምተኛ ነው ። ብሶትም አለበት ። እዚያው ለዚያው ይብሰለሰላል እንጂ በወጉ አይናገርም ። ዝምታው ያስጠላል ። ማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ጣዕም የሌለው ዝምታው ያስጠላል ። ማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ያለ አይመስልም ። “ ድብርት ” የሚል ቅጽል ያወጡለትም

ለዚህ ነው ። ከሳምሶን ጋር ተደራራቢ አልጋ ቢጋሩም ቅሉ አይስማሙም ። ሳምሶን ንጋት ላይ እየተነሣ የሚሠራው ስፖርት ድምፅ ስለሚፈጥር ፣ 'ድብርትን' ያናድደዋል ። አልጋው ላይ የሚያደርገው መወራጨት ያበሽቀዋል ። ከሁሉም በላይ 'ድብርትን' የሚያናድደው ደግሞ የሳምሶን ፌስ ነው ። በየጊዜው ቁልቁል ሲያቦንበት ፣ አፍንጫውን ይዞ ከመንፋነፍ ሌላ ምርጫ አልነበረውም ።

አሥራት 'ድብርት' ሌላ በጣም የሚጠላው ነገር ቢኖር መኝታውን ማንጠፍ ነው ። እንዲሁ እንዳድበሰበሰ የየትምህርት ወራቱን ይጨርሳታል እንጂ ፣ አንሶላውን አራግፎ በቅጡ አያነጥፍም ። ካልሲውን ማጠብም አይወድም ። ከእንእስክንድር የሚጣላው በዚህ ነው ። ትምህርትም ከሌሎች በጋራ ማጥናት ወይም መወያየት አይሆንለትም ። እድፍጦ ከርሞ ፈተና ላይ መሟሟት ነው ፣ የእሱ ችሎታ ።

ጓደኞቹ ዝቅ አርገው የሚገምቱት ዕውቀቱና ፣ ፈተና ላይ የሚያመጣው ከፍ ያለ ውጤት ያለመጣጣም ብዙዎቹን ያስገርማቸዋል . . .

አቤል ከዮናታን ቢሮ ከተመለሰ በኋላ ፣ ለአንዳቸውም ነገሩን ሳያነሣ ቢቆይም ፣ የገጽታውን መለዋወጥ በማየት እስክንድር መወትወቱ አልቀረም ።

"ምነው ? ሀገር ሰላም አይደለም እንዴ ?"

"ምን እባክህ ፣ እነ ዮናታን ረበሹኝ" አለ አቤል ስሜቱን አክፍቶ ።

"አ ! አባታችን ፣ ምን አርግ አሉህ ?" ፍቅሩን ለመግለጽ የሚጠቀምበት የአነጋገር ስልት ነበር ።

"ሰሞኑን የሰጡኣቸውን የጥናት ጽሑፍ እንደ ገና እንድሠራው አዘዙኝ ።"

"ምን ታረገዋለህ ! መበርታት ነው ። አይዞህ ስድስት ወር እኮ ነች የቀረችን ።"

በሱ ቤት ስድስት ወሩን የስድስት ሰዓት ያህል አቅልሎ መናገሩ ነው ። ለአቤል ግን ስድስት ወሩ ስድስት ዓመት ሆኖ ነበር የተሰማው ።



# ምዕራፍ ሁለት

የዓመቱ ትምህርት ከተጀመረ ሁለት ወር እንኳ ባይሞላም ፣ የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች በጥናት ተዋክበዋል ። አብዛኛው ተማሪ ፣ ፊቱን ወደ ቀለም መልሶአል ። አንዳንዱ ደግሞ የሌላው አጠናን ተስፋ አስቆርጦት ፣ የትምህርት አሰጣጡ ክብደት ወይም ደግሞ አንድ የሙከራ ፈተና አስበርግጎት ፣ የመሰናበቻ ጊዜውን ብቻ በመጠባበቅ አሥራ ስድስት ሰዓት ይተኛል ። አይብዛ እንጂ አቤል የገጠመው ዓይነት ችግር ውስጥ ገብቶ የሚዋዥቅም አይጠፋም ።

የሁለተኛና የሦስተኛ ዓመት ተማሪዎች መጠነኛ መረጋጋት ይታይባቸዋል ። ጥናቱ በመጀመሪያና በመጨረሻ ዓመት ተማሪዎች ላይ ያደላል ። በተለይ በርካታ ተማሪ የሚያረግፈው የመጀመሪያ ዓመት አጋማሽ ፈተና እንደ ጦር ስለሚፈራ ተማሪዎቹ ፣ "የገና ማዕበል" የሚል ስም አውጥተውለታል ።

የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች ፣ ለትምህርቱ ብቻ ሳይሆን ለግቢውም እንግዳ ስለሚሆኑ ፣ መቸኮልና መረበሽ ይታይባቸዋል ። በዚሁ ምክንያት ፣ 'ፍሬሽ ጠጣው' የሚል ስያሜ ወጥቶላቸዋል ። ትግላቸው ፈተና ለማለፍ ብቻ ሳይሆን ዩኒቨርስቲ ውስጥ የመቆየት ህልውናቸውን አስከብረው ይህን ስያሜ ለማስፋቅም ጭምር ነው ።

ትዕግሥት ፈረደ ፣ ከማዕበሉ ግፊት ለመዳን ከሚፍጨረጨሩት የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች አንዷ ናት ። አብዛኛውን ጊዜ የምታጠናው ከዋናዉ ቤተ መጻሕፍት ጀርባ የሚገኝ ዋርካ ሥር ነው ። ጓደኛዋ ማርታ ደመቀ ፣ ይህን ቦታ እምብዛም ባትወደውም ፣ በትምህርቱ ረገድ የትዕግሥትን ርዳታ ስለምትፈልግ ብዙ ጊዜ አብራት ታጠናለች ።

ሰሞኑን የመጀመሪያ ዓመት አጋማሽ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ትምህርት ፈተና አለ ስለ ተባለ ፣ ሁሉም የሚያጠኑት

ይህንኑ ነው ። አብዛኛው ተማሪ የአጠናን ስልት የለውም ። መደናገጥ ይበዛበታል ። የአንድ ትምህርት ፈተና አለ ከተባለ ፣ ተማሪው ሙሉ ኃይሉን እዚያ ትምህርት ላይ ያውላል ።

የተቀሩት ትምህርቶች ሳይታዩ ይከርማሉ ። ሌላ ፈተና ሲመጣ ደግሞ ወደ ሌላዉ ይዘመትበታል ። ትምህርትን በአእምሮ ውስጥ ከሚቀርፅ የአጠናን ዘዴ ይልቅ ፣ በሽምደዳ ለጊዜው ያህል ዐውቆ መሰናከሉን የማለፍ ልምድ እየዳበረ መጥቷል ።

ትዕግሥትና ማርታ ከዋርካው ሥር ተቀምጠው ይህንኑ ትምህርት በማጥናት ላይ ሳሉ ፣ አንድ ወጣት በአካባቢያቸው ውልብ ሲል ታያቸው ። ቀድማ ያየችው ትዕግሥት ነበረች ። ሆኖም ቶሎ ብላ ዐይኗን ሰበረች ።

ማርታ ወጣቱን እንዳየችው ከአፏ አምልጧት —
" ያውልሽ ! " አለቻት ።

" ምን? " አለችና ትዕግሥት የማርታን ሐሳብ ለማደናገር ቶሎ ብላ ፣ " በይ ይልቅ ልጠይቅሽ " አለቻት ።

" ምን ? " አለቻት ማርታም ፣ ድንገት ባመለጣት ቃል ተደናግጣ ።

" ከምናጠናው ትምህርት ውስጥ ነዋ ! "

" እሺ ፣ ጠይቂኝ " አለች ማርታ — ለአፏ ያህል ። ልቧ ግን ወደ ዐለፈው ጉዳይ ቀርቶ ነበር ።

' ለምንድነው የምትደብቂኝ ? ' ስትል አሰበች ፣ እኔ እንደ ሆንኩ ነቅቼባታለሁ ። ሞኝት ! በእሷ ቤት ማንም አላወቀብኝም ብላ እኮ ይሆናል ። ያበጠው ይፈንዳ እንጂ ፣ ዛሬ አውጣጣታለሁ ብላ በልቧ ፎከረች ።

" ግን ዋና ነሽ ፣ ትዕግሥት ሙች ! "

" ምነው ? ምን አረግኩሽ ? " አለች ትዕግሥት ፣ ነገሩ ቢገባትም እንዳላወቀች ሆና በመቅረብ ።

" ስለ እሱ ሳነሣብሽ ለምን ትዘጊኛለሽ ! " አለቻት ፣ ድርቅ ብላ ጉዳዩን ግልጽ በማውጣት ።



ትዕግሥት ምንም አልመለሰችም ። ከው አለች ። ወደ ኋላዋ አስታወሰች ። በእርግጥም ስለ አቤል ስታነሣባት ብዙ ጊዜ ዘግታታለች . . .

አንድ ጊዜ ማርታ አቤልን ከሩቅ ስታየው ፣ ከትዕግሥት ጋር ጨዋታ ለመክፈት ብላ ፣ " ትዕግሥትዬ ! ይሄ ልጅ በትምህርቱም በጣም ጎበዝ ነው አሉ ። በሦስተኛ ዓመት አጋማሽ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በሁለት ትምህርት " B " አግኝቶ ካልታነቅኩ ብሎ አስቸግሮ ነበር ይባላል " አለቻት ።

" ለምን ? " አለች ትዕግሥት ፣ ለጨዋታው ብዙም ቅሜቷን ያልሰጠች በመምሰል ።

" ጂ.ፒ.ኤ.ው ትንሽ ዝቅ ስላለበት ነዋ ! ከአራት ነጥብ ወርዶ እያውቅም ይላሉ " አለች ማርታ ፣ የትዕግሥትን ስሜት የሳበች መስሏት ፣ ከፋኛ የተገረመች ያህል -ራሷን እየነቀነቀች ።

" ኧረ ? " አለችና ትዕግሥት ቶሎ ብላ ወደ ሌላ አርዕስተ -ጉዳይ ዞረች ። ማርታም በሆዷ በሽቃ ነገሩን ተወችው ።

ሌላ ጊዜ ደግሞ ፣ በመኝታ ክፍላቸው ውስጥ ከሌሎቹ ሁለት ልጃገረዶች ጋር ሆነው ስለ ትምህርት መስክ መረጣ ጉዳይ ሲጨዋወቱ ፣ በማርታ ሐሳብ ውስጥ አቤል ብቅ አለባትና ፤

" እኔ አንዳንድ ልጆች ጥሩ ጭንቅላት ኖሮአቸው ለምን የማይሆን መስክ እንደሚመርጡ ይገርመኛል " አለች ።

" እንዴት ? " አለች ትዕግሥት ።

" አሁን ዘንድሮ በፍልስፍና ትምህርት ከሚመረቁት ተማሪዎች መሐል አንድ ልጅ አለ ። ብታዪው እኮ . . . "

" የቱ ነው ? " ሲሉ ሁለቱ ልጃገረዶች ጠየቁ ። ትዕግሥት የአቤል ጉዳይ መነሣቱ ስለ ገባት ፣ አንገቷን አቀርቅራ ከጥፍሯ ውስጥ ቆሻሻ ታወጣ ጀመር ።

ማርታ ነቃችባት ። ግን ጨዋታዋን አላቋረጠችም ። በጣም ጎበዝ ነው የሚባለው " እያለች ለሁለቱ ልጃገረዶች

ለማስረዳት ሞከረች ፤ ስሙንም ታውቀዋለች ። ሆኖም በትዕግሥት ፊት መጥራቱ የሚያስደነግጣት ወይም ሌላ ጥርጣሬ የሚያሳድርባት ስለ መሰላት ስሙን አልጠራችም ።

ሁለቱ ልጃገረዶች የአቤል ምስል ዐይነ ኅሊናቸው ውስጥ ሊመጣላቸው ስላልቻለ ፥ “ እሺ ብቻ ጨዋታውን ቀጥዪ ” አሏት ።

“ እና እሱን ብሆን ” አለች ማርታ ፥ “ እንደሱ ጭንቅላት ቢኖረኝ ፣ ሜዲሲን ወይም ኢንጂነሪንግ ነበር የምመርጠው ። ”

“እንደሱ ማለት እንኳ አትችዪም ፥ ” አለች አንደኛዋ ልጃገረድ ። “ ሰው እንደ ፍላጎቱ ነው ። አንቺ የምትዪው ልጅ የፍልስፍና ጥማትና ፍላጎት ይኖረው ይሆናል ። ደግሞስ የከበደና የከበረ ትምህርት ሜዲስን ብቻ ነው ያለው ማነው እሱ ? ! በእኔ ግምት ማንኛውም የትምህርት ዐይነት የተከበረና ዋጋ ያለው ነው ። ዋናው ነገር እንደ ባለቤቱ ፍላጎትና አያያዝ ነው ”

ትዕግሥት ልቧ ቅቤ ጠጣ ። ደስታዋ የልጃገረዷ አነጋገር አቤልን ስለሚደግፍ ሳይሆን የራሷም እምነት ስለሆነ ነበር ። በትዕግሥት አመለካከት ፥ ፍላጎትና ትክክለኛ ስሜት በገንዘብ መለወጥ የለበትም ። የመስከ መረጣው ጉዳይ በአብዛኛው ተማሪ ዘንድ ፥ “ ስሜቱ የትኛውን ይከተላል ? ” መሆኑ ቀርቶ ፥ “ የትኛው ብዙ ገንዘብና ዕድገት ያስገኛል ? ” የሚለው ሆኖአል ። ቢገኝም ቅሉ ፣ ያለስሜትና ፍላጎት የሚሠራ ሥራ ብኩንነትን ፥ ግዴለሽነትንና ራስን መጣልን እንደሚያ ስከትል አርቆ የሚያስበው እምብዛም አልተገኘም ።

ለማንኛውም ፥ መነሾው የአቤል ጉዳይ በመሆኑ ፥ ትዕግሥት ጨዋታውን ተካፍላ ይህን አስተያየት ለመስጠት አልቻለችም ። ስሜቷን አፍና ዝም አለች ።

ማርታም የአቤልን አርዕስት ያነሣችው የትዕግሥትን ስሜት ለማጥናት ነበር እንጂ፥ ለክርክሩ ብዙም ደንታ አልነበራትም ። ስለዚህ ያን ዕለትም በሽቃ አሳለፈችው . . .

ትዕግሥት ይህንና የመሳሰሉትን ካስታወሰች በኋላ ፥ ‘ በእርግጥም ስለ አቤል ስታነሣብኝ ብዙ ጊዜ ዘግቻታለሁ ’ ብላ አሰበች ።



ማርታ ወሬ ትወዳለች ። በተለይ የፍቅር ወሬ ከሆነ አናፍንፋ ነው የምትሰማው ። ልማድ ሆኖባት ነው እንጂ ፥ በፍቅረኞች መሐል ገብታ ተንኮል ለመሥራት አይደለም ። ከትዕግሥት ጋር በዩኒቨርስቲው የመኝታ ክፍል ውስጥ ተደራራቢ አልጋ ላይ ስለሚተኙና አብዛኛውን ጊዜ አብረው ስለሚያሳልፉ ፥ የአጭር ጊዜ ምስጢርም ቢሆን ስርስራ ስለማወቅ ባለመቻሏ ከልቧ በሽቃለች ። ትዕግሥት ከአቤል ጋር የዐይን ፍቅር እንደ ጀመረች ከጠረጠረች እንኳ ወር ያህል ይሆነዋል...

“ በእውነት ዋና ነሽ ” ስትል ደገመች ማርታ ፥ “ እኔ ጓደኛዬ ነሽ ብዬ የሆዴን ሁሉ እጫውትሻለሁ ። አንቺ ግን ልብሽ አይያዝም ። ”

ትዕግሥት ተረበሸች ። “ ልብሽ አይያዝም ” የሚለው ቃል አስደነገጣት ።

“ እኔ ‘ ኮ ደብቂሽ አይደለም ። ”

“ ደብቀሽኝ ነው እንጂ ! እረ ታዘብኩሽ ዋና ነሽ ” አለች ማርታ ፥ እንጀት በሚበላ አነጋገር ።

“ ማርታ ሙች መደበቄ አይደለም . . . አንዳንዴ መንገድ ላይ ስንገጣጠም . . . ያየኛል ። በቃ ”

የማርታ የወሬ አንቴናዎች ከመቼውም በላይ ነቁ ። ሕዋሳቶቿ ከትዕግሥት አፍ ሲወጣ ፥ ለመስማት ሲጓጉ ለከረሙለት ነገር ተቁነጠነጡ ።

“ እንዴት ማየት ? ዝም ብሎ ማየት ? ” ስትል አፋጠጠቻት ።

“ አዎ ፥ በቃ . . . እንዴት ልበልሽ ? ” አለች ትዕግሥት፥ ሁኔታው ለገለጻ አስቸግሮአት ” . . . ዝም ብሎ ያየኝና ዐይን ለዐይን የተገጣጠምን እንደሆን ተሽማቆ ዐይኑን ይሰብራል ” አለች ፥ የራሷን ደብቃ ።

ማርታ በልቧ ሣቀች ። ሴቶች አብዛኛውን ጊዜ ተወዶን እንጂ ወደድን እንደማይሉ ታውቃለች ። ልምዱ አላት ። ማርታና ትዕግሥትን አጋጣሚ በመኝታ ክፍል አገናኝቶአቸው ፥ የትዕግሥት የቀለም ትምህርት ጉብዝና አስተሳሰራቸው እንጂ ጓደኞች ሊሆኑ የሚችሉ አልነበሩም ። በአስተዳደግና በአኗኗር ሁኔታ ብዙ ይለያያሉ ።

ፍቅር ለደብረ ዘይቷ ትዕግሥት እንግዳ ነገር ነው። ፍቅር ተደጋግሞ በተጀመረ ቁጥር አዲስ መሆኑ ባይቀርም ቅሉ ፣ ለመሐል አራዳ አደጓ ማርታ እንግዳ ነገር አልነበረም ። ቀን ከወንድ ጓደኛ ጋር መውጣት ፣ ማደር ፣ በተለያዩ የጫዋታ ቦታዎች ላይ መገኘት ፣ ከማርታ አፍ የማይጠፉ ጨዋታዎች ናቸው ። ትዕግሥትም እነዚህን መሳይ የማርታ “ ምስጢሮች ” ስታዳምጥ በመክረሟ ፣ በዚህ ዕለት “ ልብሽ አይያዝም ” ያለቻትን ለማስተባበል ስትል ፣ ደብቃ የቆየችውን የአቤልን ጉዳይ ለማውጣት ተገደደች ።

“ ለመሆኑ ስንት ጊዜ ሆነው ? ” አለች ማርታ ፣ ለጥናት የገለጠችውን ደብተር ጭራሹን ዘግታ ።

“ ምኑ ? ” አለች ትዕግሥት ፣ ጥያቄው ቢገባትም በአንዴ መመለሱ አስቸግሮአት ።

“ ከአቤል ጋር በዐይን . . . ከጀመራችሁ ነዋ ? ” አለ ቻት ድርቅ ብላ ።

ትዕግሥት የአቤል ስም ሲነሣ የባሰ ድንግጥ አለች — ደስታ የተቀላቀለበት ድንጋጤ ።

“ በግምት ስድስት ሳምንት ይሆነዋል ” ካለች በኋላ ፣ ወዲያው ፣ “ እኔ እኮ እሱ ስለሚያየኝ ነው እንጂ . . . ” አለችና ብግዴለሽነት ዐይኗ ትከሻዋን ነቀነቀች ።

“ እ . . . ሺ? ” አለች ማርታ ፣ ጨዋታው በዚሁ እን ዳያልቅ በመሥጋት ። ትዕግሥት ትክ ብላ ከማየት በስተቀር ምንም አልተነፈሰችም ።

“ አሥራ አንደኛ ክፍል እያለሁ አንድ መምህር ምን አለ መሰለሽ ? ”

“ ምን አለ? ” አለች ትዕግሥት ፣ ለመልሱ ብዙም ያልጓጓች በመምሰል ።

“ መጀመሪያ ለክፍሉ ጥያቄ አቀረበ ። ”
“ ምን የሚል ? ”
“ ፍቅር የሚጀመረው ከየት ነው ? ”
“ ከየት ነው አላችሁ ታዲያ ? ”
“ እኔ ፣ ‘ ከአካባቢ ወይም ከአቅራቢያ ’ ብዬ መለስኩ ።



ሌሎችም የመሰላቸውን መለሱ ። በመጨረሻ መምህሩ ራሱ ‘ ፍቅር የሚጀምረው ከዐይን ነው ’ ብሎ ገላገለን ። ”

ትዕግሥት ነገሩ ቢኮረኩራትም አልሣቀችም ። ማርታም አልረካችም ። ከትዕግሥት አፍ መስማት የፈለገችው ሁሉ ቀድሞ የምታውቀው ሆኖ ስላገኘችው ፣ አዲስ ምስጢር ስመ ሠርሠር ስልተው የቆሙት ሕዋሳቶቿ ሳይረዱ ቀሩ ።

“ አይ አንቺ ! ” አለቻት ቆይታ ቆይታ ።
“ እንዴት ? ”
“ እንዲሁ ነዋ ! ”

ትዕግሥት በመቅለስለስ ዐይኗት ትከሻዋን ነቀነቀች ።

# ምዕራፍ ሦስት

አቤል ከፍልስፍና መምህሩ የተቀበለውን የጥናት ጽሑፍ ሲሸሸው ሰንብቶ፣በአራተኛው ቀን የግዱን አነሣው ። አልጋው ላይ ጋደም እንዳለ ነበር — ለማንበብ የፈለገው ። ኮሶ የሚጠጣ ይመስል ፊቱን አጨማዶ ገለጠው።የመጀመሪያውን ገጽ ሳያነብ እያገላበጠ ከመሐል ደረሰ ። እንደ ገና ወደ ኋላ ተመለሰ ። የራሱ የእጅ ጽሕፈት አስጠላው ።

'ኤጭ !' አለ ፣ በመሰላቸት ድምፅ ። 'አሁን ምኑን ነው የማሻሽለው ? የቻልኩትን ያህል ሠርቻለሁ ፣ በቃ !'

ገና ሳያነበው ፣ የሚሻሻል ነገር የለበትም ብሎ ወሰነ ። እጆቹ ሳይታዘዙ የጥናት ጽሑፉን ወረቀት ከደኑ ።

'ምን ይመጣብኛል ?' ሲል አሰበ። እንደ ገና ባልሠራው ተሰቀል የሚለኝ የለ ። ያው ወድቆ መባረር ነው ። ይህ ደግሞ በእኔ አልተጀመረ ። ለምን ራሴን አስጨንቀዋለሁ ?'

የናታን በድንገት በሐሳቡ መጥተው ድቅን አሉበት ። ወረቀቱን ተቀብሏቸው ሲወጣ የተናገሩት ቃላት ታወሰው ።

"ሐሳብ ውስጥ ገብተህ ወይም ተቻኩለህ ይሆናል እንጂ ፣ አንተ እንዲህ ዐይነት ሥራ እንደማትሠራ እተማመ ናለሁ ። "

"ዕዳ እኮ ነው " አለ በሐሳቡ ። 'እሳቸው ደግሞ ለምን የሰው ችግር አይገባቸውም ? ፍቅር ወጥመድ ውስጥ ለገባ ተማሪ ጥናትና ሥራ ምንኛ እንደሚያስጠሉት ለምን አይረዱ ልኝም ? . . . ያውም አቅፎ ወይም ስሞ ወይም ተዳርቶ ማስ ከን በማይቻል በዐይን ፍቅር ለተለከፈ ተማሪ ! ነገር የጠፋው ቀድሞ ነው ። ትምህርት አስቀምጦ ፍቅር የተጀመረ ዕለት !'

ማፍቀር በአንድ አጋጣሚ የሚከሠት የሕያውነት ንጹብ ራቅ ሳይሆን ራሱ ሥራዬ ብሎ ጎትቶ ያመጣው ይመስል ፣ ገና የመጀመሪያ ዕለት ትዕግሥት ላይ ያረፉት ዐይኖቹን በልቡ

ረገማቸው ። ዕለቱ ፣ ያ የተረገመ ይሁን የተቀደሰ ያልገባው ዕለት ፣ በዐይን ሕሊናው መጣበት ...

ጥቅምት 14 ቀን ፈጽሞ የማትረሳ፣በአቤል አዕምሮ የተቀረፀች ዕለት ናት ። በዩኒቨርስቲዉ ውስጥ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች የሚመዘገቡበት ዕለት ነበር ። ተመዝጋቢዎቹ ለዩኒቨርስቲው አዲስ በመሆናቸው ፣ በአዲስ ስሜት ፊታቸው በርቶ ምዝገባው በሚካሄድበት መስኮት በኩል ሥርዓት ባጣ ሁኔታ ተሠልፈዋል ።

አቤል ለግል ጉዳዩ ምዝገባ ክፍል ደርሶ ሲመለስ ፣ ከተሠለፉት መሐል ከአንዷት ኮረዳ ጋር ዐይን ለዓይን ተገጣጠሙ ። ሁለቱም በቅጽበት ዐይናቸውን ሰበሩ ። አያውቃትም ፤ አታውቀውም ። ለጊዜው ለማያውቃት ልጅ መደንገጡ አላስገረመውም ። ጥቂት ወደፊቱ ከተራመደ በኋላ ፣ አስልቶ ዘወር ብሎ ተመለከታት ።

ጠይም ናት ፤ ካውያ ያልነካው ጸጉር ከማጅራቷም ባያልፍ ለማበጠር የሚያስቸግር ዐይነት አይደለም ። ቁመቷ አጭር ነው ፤ አለባበሷ እንደ ነገሩ ይመስላል ፤ገና ሲያያት አጠገቧ ካሉት ልጃገረዶች ጋር በሆነ ጨዋታ ትሣሣቅ ነበር ። ስትሥቅ ጉንጮቿ ስርጉድ ይላሉ ። በፈገግታ ጊዜ የሚሰረጐዱ ጉንጮች አቤል ከልጅነቱ ጀምሮ ይወዳል ።

ያያት ዕለት ፣ ያለ ምንም ሐሳብ ውሎ ማታ መኝታው ላይ ዐረፍ ሲል በስመመን አጭር ፣ ወይም ልጅ የሚሰረጐዱ ጉንጮቿን እያሳየች ልታጫውተው ከተፍ አለች ። ያለምንም ማመንታት ተቀበላት ። ቀን ያየውን ቁመናዋንና አለባበሷን በልቡ ደግሞ አደነቀላት ። እንሶላውን ተከናንቦ ፣ ዐይኑን ጨፍኖ ስትሥቅ በስመመን ተመለከታት ። “እየሣቀች የጉንጮቿን መሰርጐድ በማሳየት ብታስከፍል ዐይኑን የሚያሽ ያለ አይመስለኝም ” ሲል በሐሳቡ ደመደመ ። ልቡ ውስጥ ገብታ እንድትዘናና ፣ እንድትጫወት ፣ እንድትቦርቅ ፣ እንድትተኛ እንድትነሣ ፣ እንደ ልቧ እንድትሆን ፈቀደላት ።

ትዕግሥት ከዚያን ዕለት ጀምሮ በተፈቀደላት መሠረት ልቡ ውስጥ ገብታ ፣ እግሮቿን አኮራምታ ተቀመጠች ፤ ውላ ስታድር ተንፈራጣ ተቀመጠች ። ስታስልስ በጀርባዋ ጋደም አለች ። ስትከርም ጭራሹን ሐሳብዋን ጠቅልላ ተኛች ።



መጀመሪያ በአቤል ልብ ውስጥ ትምህርቱና ትዕግሥት ጸብ ሲፈጥሩ ፣ አቤል ዳኛ ሆኖ ፣ “ ዕረፉና ተቀመጡ ፣ ለሁለታችሁም ይበቃል ” አላቸው ። ጠባቸው እየከረረ መጥቶ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ ፣ አቤል በትምህርቱ ፈረደና ትዕግሥትን አነገሣት . . .

‘ . . . ያን ዕለት ነው — ነገር የጠፋው ! ’ አለ አቤል በልቡ ደጋግሞ ፣ በሐሳብ ወደ ኋላ ብዙ ከተጓዘ በኋላ ።

አንዳች ነገር የገፈተረው ይመስል፣ተፈናጥሮ ከመኝታው ላይ ወረደ ። ወዴት እንደሚሔድ ሳያስብ ነበር-የተነሣው ። ጫማውን አደረገና ክፍሉን ለቅቆ ወጣ ። ወዴትም ይሁን ! ሰው ወዳለበት-ትዕግሥትን ሊያይ ወደሚችልበት ። የሚነዘንዝ ሕሊናውን ለማሸነፍ ትዕግሥትን ማየት አለበት ። ከዚያ ዕለት ጀምሮ ብቸኝነቱን መሸሽ እሚችለው ትዕግሥት ላይ ዐይኑን በማሳረፍ ሆን ።

ከመኝታ ክፍሉ ወጥቶ ደረጃውን ሲወርድ እስክንድር ማንደፍሮን አገኘው ።

“ ታዲያስ አቤል ፣ ወዴት ነው ምትሔደው ? ”

“ እስኪ መጻሕፍት ቤት ልድረስ ብዬ ነበር ። ” እሱን ሲያይ በቅጽበት የመጣለት ሐሳብ ነበር ። በመቀጠልም ፣ “ ያንን የጥናት ጽሑፍ መምህሩን ላለማስቀየም ብዬ እንደገና ልሠራው ሞከርኩ ። ነገር ግን ገና ወረቀቱን ስገልጠው ያቅለሸልሸኛል አለው ።

“ በርታ ፣ እንደ ምንም መወጣት ነው ” አለ እስክንድር — ለማበረታታት ያህል ።

“ እሱማ የት ይቀራል ! ” አለ አቤል ፣ የውስጥ ስሜቱን ለመግለጽ በሚሞክር የደከመ አነጋገር ።

“ በል እንግዲህ ” ብሎት እስክንድር ሽቅብ ደረጃውን ወጣ ። አቤልም ቁልቁል እየወረደ የእስክንድርን አረማመድ ዘወር ብሎ ተመለከተ።ሁለት ሁለቱን ደረጃዎች ነበር — በአንድ እርምጃ የሚወጣቸው ።

አቤል በማያስደንቀው ነገር በመደነቅ ትክ ብሎ ተመለከተው ።

ከራሱ ጋር አወዳድሮት ነበር ያደነቀው ። አቤል ከጥቂት ሳምንታት ወዲህ የሥራ ፍላጎቱ ላልቶ ፣ የወጣትነት ስሜቱ በሆነ ነገር በርዶ ፣ ሲራመድ እንኳ እንደ ጎታታ ሽማግሌ ቀስ ብሎ ነበር የሚሔደው ፤ የመሰላቸት ዐይነት !

በዚህ አረማመድ ወደ መጻሕፍት ቤት አመራ ። ዋናው መጻሕፍት ቤት ለመድረስ አጭር መንገድ እያለለት በጀርባ በኩል ለመዞር በዙሪያ ጥምጥም መንገድ ሔደ ። በዋርካው በኩል ለማለፍ ፈልጎ ነበር ።

ቀስ ብሎ የዋርካውን አካባቢ ማተረ ። ትዕግሥትና ማርታ እዚያ አልነበሩም ። ዋርካውን ባየ ቁጥር አንድ ነገር ትዝ ይለዋል ። አሁንም በእግሩ ወደ ፊት እየተራመደ በሐሳቡ ብዙ ዓመት ወደ ኋላው ተጓዘ . . .

በጎንደር ከተማ ውስጥ ነዋሪዎቹ እንደ ጣኦት የሚያመልኩበት አንድ ግዙፍ ዋርካ ነበር ። አቤል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ በነበረበት ጊዜ ከመኖሪያ ቤቱ የሚመላለሰው በዋርካው በኩል ነበር ። ማታ ከትምህርት ቤቱ ሲመለስ ፣ አብዛኛውን ጊዜ ሁለት ወጣት ፍቅረኞች በዋርካው አካባቢ ይመለከት ነበር ። ሰዓት ጠብቀው ነው የሚገናኙት ። ብዙውን ጊዜ ወንድየው ቀድሞ ስለሚመጣ እየተንጎራደደ ይጠብቃታል ። መምጣቷን ገና ከሩቅ ሲመለከት ፣ ፊቱ በርቶ ጥርሶቹ ብልጭ ይላሉ ። እሷም እጠገቡ ስትደርስ የመትለሰለስ ፈገግታ ታሳየዋለች ።

ደብተሯን ይቀበላትና ከንፈሯን ይስማታል ። ተቃቅፈው በቀስታ ርምጃ መራመድ ይቀጥላሉ ።

አቤል ያኔ ገና ልጅ ቢሆንም ፣ ሁኔታቸው ስለሚያስደስተው ፣ ሥራዬ ብሎ በደስታ ይከታተላቸው ነበር ። ከትምህርት ቤት ሲወጣ እንደ መክሰስ የሚናፍቀው እነሱን ማየት ነበር ። ምናልባት ዋርካው አካባቢ ቀድሞ ከደረሰ እንኳ እስኪመጡ ድረስ ተደብቆ ይጠብቃቸዋል ። ቆዳው ምኝ ቢመስልም ውስጡ ብልጣ ብልጥ ስለ ነበር ፣ እነሱን ለማየት እንደሚከታተላቸው እንዳያውቁበት ይጠነቀቅ ነበር ። በዝግታ በሚራመድበት ጊዜም ራቅ ብሎ የሚከተላቸው ፣ ራሱን እንደ ተራ መንገደኛ ወይም በየመንገዱ እየተጫወተ እንደሚሔድ ልጅ አስመስሎ ነበር ። እየቆየ ሲመጣ ግን ፣ እነሱም ሳይ



ነቁበት አልቀሩም ። ሆኖም አቤል ብቻ ሳይሆን በፍቅራቸው ሁኔታ የሚደነቁ ብዙ ተመልካቾች እንዳሏቸው ስለሚገምቱ ደንታም አይሰጣቸውም ነበር ። ወንድየው ያማሩ ልብሶች እየለበሰ በተወሰነው ሰዓት ከዋርካው አካባቢ ከመምጣቱ በቀር ምን ሥራ እንዳለው አይታወቅም ። እሷ ግን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ነበረች ።

ጨዋታቸው አለማለቁ ተመልካቻቸውን ሁሉ ያስገርመዋል ። ተገናኝተው ከተሳሳሙ በኋላ በፋሲል ግንብ በኩል አድርገው በኤሊ አረማመድ ረዥርም መንገድ ይጓዛሉ ። በዚህ ሁሉ ጊዜ በየቀኑ ወሬ አያልቅባቸውም ። ጨዋታቸው ይብስ የሚጐላው መለያያቸው ቦታ ሲደርሱ ነበር ። ከሦስት ጊዜ ያላነሰ ይሰነባበታሉ ። ጨዋታቸውን ደምድመው ለመለያየት ከተሳሳሙ በኋላ ፣ በመጨባበጥ ዐይነት እጅ ለእጅ ተያይዘው አዲስ ጨዋታ ይቀጥላሉ ። ደሞ እንደ ገና ይሳሳማሉ ።

“ እስኪ መታወቂያ ” የሚል የጥበቃ ጓድ ድምፅ አቤልን ከሐሳብ ጉዞው መለሰው ። ቤተ መጻሕፍቱ በር ላይ ደርሶ ነበር ። መታወቂያውን አውጥቶ አሳየና ወደ ውስጥ ገባ ። በቀጥታ የፍልስፍና መጻሕፍት ወደ ተደረደሩበት ረድፍ እያመራ ፣ ‘ የታደሉ ናቸው ’ አለ በልቡ ፣ ሁለቱን ፍቅረኞች በማስታወስ ። ‘ እሱ የሷን ሰውነት እሷም የሱን ሰውነት መዳሰስ በመቻላቸው ፣ የልባቸውን አውጥተው መጫወት በመቻላቸው ፣ የፍቅርን እስትንፋስ መተንፈስ በመቻላቸው በእርግጥ የታደሉ ናቸው ። ሳይነጣጣሉ ፣ ሳይፈራሩ ፣ የፍቅርን ቃጠሎ በጋራ በመቀበላቸው የታደሉ ናቸው ። ’

ዐይኖቹ መጻሕፍት መምረጣቸው አላቋረጠም ። ነገር ግን ፣ ሐሳቡ ፈጽሞ መመለስ ስላልቻለ ፣ ትርጉም የለሽ ተራ ፈደላት ነበር — የሚመለከተው ።

‘ ምን ይመስለው ? ’ አለ ፣ ‘ ወንድየው ምን ይመስለው ? ዐይኖቹ ተርበው ልቡ እየነጠረ መምጣቷን ሲጠብባቅ ፣ እሷም መንገድ ርቆባት በልቧም በእግሯም ከንፋ ስትደርስለት ፣ ዋርካው ሥር ሲገናኙ ፣ ዕቅፍ አድርጎ ሲስማት ምን ይመስለው ? ምን ይሰማው ? መታደል ነው ። መታደል ! . . . ’

በደመ-ነፍስ ከመደርደሪያው ላይ አንድ መጽሐፍ አወረደ ። ዐይኑን ስለሳበው ብቻ ነበር ። ዝም ብሎ እያገላበጠው ከራሱ ጋር ንትርኩን ቀጠለ ።

‘ እኔስ ይህን ማድረግ የማልችለው ለምንድን ነው ? ’ ሲል ራሱን ጠየቀ ። ‘ ትዕግሥትን አቅፎ መሳም ፣ ከትዕግሥት ጋር የልቤን መጫወት ፣ ይህን ማድረግ የማልችለው ለምንድነው ? . . . ’

ትዕግሥት በፈገግታ ጉንጮቿን እየሰረጎደች መጥታ ከፊቱ ቆማ ፣ “ ፈሪ ስለሆንክ ነዋ ! ጰርጳራ!” የምትለው መሰለው ።

‘ ታዲያ የምወዳትን ከፈራሁማ የልቤን ለማን ልናገረው ነው? . . . ’



# ምዕራፍ አራት

የሥራ ክፍላቸው በር ሲንኳኳ ዮናታን ካቀረቀሩበት መጽሐፍ ቀና ብለው ፣ “ አቤት ! ይግቡ ” አሉ ።

እስክንድር ማንደፍሮ ፣ ከልብ ያልሆነ ፈገግታ እያሳየ ገባ ። የቢሩ ኳኳታ ከትኩስ ምርምር ላይ ቢያባንናቸውም ቅሉ ፣ የመጣው ሰው እስክንድር መሆኑን ባስተዋሉ ጊዜ ዮናታን ደስ አላቸው ።

የማንበቢያ መነጽራቸውን እያወለቁ ፣ “ ተቀመጥ ፣ እስክንድር ” በማለት መቀመጫውን አመለከቱት ።

“ እህሳ ? ጥናት እንዴት ይዞሃል ? ”
“ እየታገልኩ ነው ። ”

“ ምን አስበሃል ? ትምህርቱን ትቀጥልበታለህ ? ወይስ . . . ”

ለመጀመሪያ ዲግሪ የመጨረሻ ዓመት ተማሪ መሆኑን በሚመለከት ያቀረቡለት ጥያቄ ነበር ።

“ ገና አላሰብኩትም ” አለ እስክንድር ፣ “ ደግሞ በዚህ ጉዳይ ላይ ውጤቱ ወሳኝነት ይኖረዋል ።”

“ እዎ ” አሉ ዮናታን ፣ ራሳቸውን እየነቀነቁ ። “ በርትተህ ከሠራህ ጥሩ ውጤት ታመጣለህ ። ”

የእስክንድር መልስ ፈገግታ ነበር ። ጥቂት ሴኮንዶች በዝምታ ከቆዩ በኋላ ፣ “ አቤል ጓደኛህ ነውን ? ” ሲሉ ጠየቁት። ሌላው ሁሉ ዝብዝብ ፣ ዮናታን ለመንደርደሪያ ያህል ያቀረቡት ነበር እንጂ ፣ እስክንድርን ከክፍላቸው ድረስ ያስጠሩት ለዚህ አርዕስት-ጉዳይ ነበር ።

እስክንድር ወዲያውኑ ጉዳዩ ገባው ። በመጀመሪያ ዮናታን ያስጠሩት በእጃቸው ስላለው የጥናት ጽሑፍ ጉዳይ

ሊያነጋግሩት መስሎት ነበር ። አሁን ግን የተፈለገበትን ነገር ጠረጠረ ።

“ አዎ ፣ አንድ ክፍል ውስጥ ነው የምንተኛው ። አብዛኛውን ጊዜም አብረን እናጠናለን ” ሲል መለሰ ።

“ አሃ ! ደኅና . . . እንዴት ነው ? በቅርቡ የምታውቀው የደረሰበት ችግር አለ?” ጥያቄው ቢገባውም ፣ እስክንድር ሀሳባቸውን የተረዳላቸው ለመምሰል አልፈለገም ።

“ እንዴት ማለት? ” ሲል ጠየቃቸው ።

“ ማ . . . ማለቴ ፣ መንፈሱን የሚረብሸው ወይም የሚያበሳጨው በቅርብ የደረሰበት አጋጣሚ እንዳለ ? ”

“ እኔ እንደ ገባኝ አንዲት ልጅ ያፈቀረ ይመስለኛል ” አላቸው ነገሩን ፍርጥርጥ አድርጎ ።

ዮናታን እንዳች ውጤት ያገኙ ይመስል መላ ሰውነታቸው ነቃ ። ፊታቸው ላይ ያልተንጸባረቀ ውስጣዊ ፈገግታ ፈገግ አሉ ።

“ እህ ! እህ ! ” እያሉ ራሳቸውን ነቀነቁ ።

“ ግን ደግሞ እንደ ገመትኩት ” ሲል ቀጠለ - እስክንድር ። „ እኔ እንደ ገመትኩት ፍቅሩ ከዐይን አላለፈም ። ”

“ እንዴት ማለት ? ”

“ ከልጅቷ ጋር መነጋገር ቀርቶ ፣ ሰላምታ እንኳ ተሰጣጥተው አያውቁም ። ” በግምት አስመስሎ አቀረበው እንጂ በትክክል የደረሰበትን ነበር የተናገረው ። ከዐይኑ ወዲያ ምን ማስረጃ ያስፈልጋል ? . . . እስክንድር ለአቤል የመኝታ ክፍል ጓደኛው እንደ መሆኑ መጠን የቀን ተቀን ተግባሩን ተከታትሎ ማጥናት ለሱ ከባድ አልነበረም ።

ዮናታን ማንኛውንም መረጃ በእጃቸው ያገቡ ያህል ገጽታቸው በርቶ ወደ ኋላቸው ተለጥጠው ተቀመጡ ። እስክንድርን ያስጠኑት ፤ ለአቤል ችግር መጠነኛ መንደርደሪያ ይሰጠኛል ብለው ነበር ። ስለ አቤል ከጠበቁት በላይ የሚያውቅ ሆኖ በማግኘታቸው ደስ አላቸው ።



“ ታዲያ ስለ ሁኔታው ከአቤል ጋር ተወያይታችሁ ታውቃላችሁ ? ”

“ እዬዬ ! ” አለ እስክንድር ፣ ራሱን እየነቀነቀ ። “እንኳን መወያየት ቀርቶ ፣ ገና የነገሩ ጫፍ ሲነካበት ፊቱ ይለዋወጣል ። ለማንም ስለዚህ ጉዳይ የሚያወራ አይመስለኝም ። ምክንያቱም ፣ በአካባቢው መቼም ከእኔ በላይ የሚቀርበው የለም ። ”

ዮናታን ዝም አሉ ፤ በልባቸው የዚህ ምክንያት ምን ሊሆን እንደሚችል እያብሰለሰሉ ነበር ። እስክንድር ቀጠለ ፡—

“እንዲያውም የኀዳው ፣ ጉዳዩን ለብቻው መያዙ ይመስለኛል ። ከፍተኛ ጭንቀት ነው ያተረፈው ። ከእኛ ከጓደኞቹ ጋር ቢወያይበት ኖሮ ፣ ምናልባት ጭንቀቱ ይቀንስለት ነበር ” አለ የራሱን ግምት በመጨመር ።

እስክንድር ይህን ተናግሮ እንዳበቃ ፣ የዮናታንን ዐይን ተመለከተ ። ከርሳቸው ሐሳብ ወይም ጥያቄ ይጠብቅ ነበር ። ዮናታን ግን ፣ በአካል እስክንድር አጠገብ ቢሆኑም ቅሉ ፣ በሐሳብ ርቀው ሔደው ነበር ። በእሳቸው አስተሳሰብ የዐይን ፍቅር ቀላል ጉዳይ አይደለም ። የዐይን ፍቅር ሲነሣ ምን ጊዜም ትዝ የሚላቸው አሳዛኙ ካርል ነው ። ስለዚህ ሰው ታሪክ ያጫወቱቻቸው ባለቤታቸው ሞኒካ ናት ። አሁንም እስክንድርን አጠገባቸው እንዳስቀመጡ በሐሳባቸው ከታሪኩ ትውስት ውስጥ ሰምጠው ነበር ።

በዘመነ ፋሺዝም በጀርመን ኮንሰንትሬሽን ካምፕ ታጉረው የሂትለርን በትር ከቀመሱት ሰዎች መሐል አንዱ ፣ የሞኒካ አባት ናቸው ። አባቷ ፣ ካርል ስለሚባል ወጣት ያወጉት ነገር ነበር ። እሳቸው ታሪኩን የሚያወሩት ምስኪኑ ካርል እያሉ ነው ። ሞኒካም ይህንን ጨዋታ ለዮናታን አውርታላቸዋለች ።

ካርል ፣ ከሞኒካ አባት ጋር አንድ ክፍል ውስጥ ነበር የታጎረው ። በፀረ - ፋሺዝም እንቅስቃሴው በጣም የታወቀ ወጣት ነበር ። በፋሽስቶች እጅ ያልቀመሰው ዐይነት ሥቃይ የለም ። ከዚያ በላይ በአካዳሚክ ሕይወቱ በጣም የተደነቀ ነበር ። ነገሮችን በቀላሉ ይረዳል ። ሁኔታዎችን በማነጻጸር ረገድ

ፈጣን ነው ። እንደ ዲስኩር ከጀመረ አድማጮቹን አፍ አስከፍቶ ይውሳል ። ነገር ግን ብዙ ጊዜ አይናገርም ። በእምነቱ ከብረት የጠነከረ ዲሲፕሊን ነበረው ።

ይህ ወጣት ታጋይ በኮንሰንትሬሽን ካምፕ ቆይታው ጊዜ ፣ ድንገት አንዲት ሴት ይወዳል ። የሚያሳዝነው ይህች የወደዳት ሴት የአንድ ፋሺስት ጄኔራል ሚስት መሆኗ ነው ። በሩቅ ከማየት በቀር ቀርቦ ለማነጋገር ዕድል አልነበረውም ። ሴትዮዋ እዚያ ግቢ ውስጥ የምትመጣው የጄኔራሉ ሚስት በመሆኗ ፣ እስረኞቹን መጎብኘት እንደ መዝናኛዋ አድርጋ ነው ። አብዛኛውን ጊዜ ምሽት ሲቃረብ ወደ ካምፑ ብቅ ብላ ፣ በሥቃይ የሚማቅቁ እስረኞችን በማየት ተዝናንታ ትመለሳለች ። ምስኪኑ ካርል ዐይኑ ውስጥ የሴትዮዋ ውብት ገብቶ እንቅልፍ እየነሣው ይመጣል ። መምጫዋን ሰዓት ጠብቆ ያያታል ። እሷ ግን ህልውናውንም አታውቅለትም ።

ሁኔታው እያደገ ይሔድና ፣ ለካርል ድብቅ የውስጥ ሕመም ይሆንበታል ። ለማንም ሳይናገር ብቻውን ውስጥ ውስጡን ይማቅቃል ። የሞኒካ አባት ለካርል ቅርቡ ስለ ነበሩ ፣ ነገሩን በመከታተል ቀስ ብለው ደረሱበት ። ሴትዮዋን ያላየ ዕለት የሚሰማውን አሳዛኝ ስሜት አጠኑ ። ነገር ግን ፣ ምንም ሊረዱት አልቻሉም ። ከምስኪኑ ካርል አፍ የተገነዘቡት ነገር ቢኖር ፣ የሴት ውብት ሲማርከው የመጀመሪያ ጊዜው መሆኑን ነው ። የመጀመሪያ የፍቅር ዐይኑ በማይሆን ቦታ መገለጡና በአንዲት ሴት ላይ ማረፉ ነበር የሚያሳዝነው ።

ቀስ በቀስ ነገሩ ተዛምቶ ፣ በቅርቡ የነበሩት እስረኞች ጆሮ ውስጥ ገባ ። የፋሺስት ጄኔራል ሚስት በመውደዱ ፣ እስረኞች ሁሉ ካርልን አክ — እንትፍ አሉት ። ይህ መገለል በምስኪኑ ካርል ላይ የባሰ ጭንቀትና ብቸኝነት አሳደረበት ። በመጨረሻም አንድ ሌሊት ራሱን ገድሎ ተገኘ . . .

“ እሺ ፣ ከዚያ . . . ” አሉ ዮናታን ፣ በድንገት ከትውስታቸው እንደ ተመለሱ ።

እስክንድር ግር አለው ። ከቀን ሕልማቸው ሲባንኑ ፣ እንዲያው የተነፈሱት ቃል ነው እንጂ ፣ እስክንድር መቀጠል ያለበት ምንም የተያያዘ ነገር አልነበረም ። እናም ከደካማ ፈገግታ በቀር ምንም አልመለሰም ።



“ እባክህ በዘዴ እየቀረብክ አጫውተው” አሉ ፣ የአባትነት ቃና ባለው አነጋገር ። “ አሁን ባለው ሁኔታ ላይ ብቸኝነት ከተጨመረበት መጥፎ ደረጃ ላይ ይደርሳል ። እና እባክህ ብቸኝነት እንዳይሰማው ለማድረግ ሞክር ። ”

“ እሺ ” ብሎ እስክንድር ከተቀመጠበት ተነሣ ። ክፍሉን ለቅቆ ሊወጣ ሲልም ፣ ዮናታን በባለ አደራነት ስሜት አጥብቀው ጨብጠው ነቀነቁት ።

‘ የዐይን ፍቅር የዋዛ በሽታ አይደለም ’ አሉ ዮናታን ፣ ራሳቸው ለራሳቸው ። ‘ አቤልን ከዚህ ሕመም ለማዳን ምን መደረግ አለበት ? ’ የተለያዩ የመፍትሔ ሐሳብ በጭንቅላታቸው ውስጥ መጣ ። ለጥቂት ደቂቃ ያህል ወደ ኋላቸው ተለጥጠው ተቀመጡ ፤ መነጽራቸውን መልሰው ዐይናቸው ላይ አደረጉ ።

ወረቀቶቻቸው ፣ ጠረጴዛው ላይ እንደ ተበታተኑ ጥለዋቸው ከክፍላቸው ወጡ ። ወደ አቶ መዓምር ክፍል ነበር የሄዱት ። አቶ መዓምር ለዮናታን ከሥራ ጓደኝነታቸውም ሌላ የቅርብ ጓደኛቸው ናቸው ።

ሰላምታ ተለዋውጠው እንደ ተቀመጡ ዮናታን ያለምንም መንደርደሪያ በቀጥታ ወደ መጡበት ጉዳይ አመሩ ።

“እባክህ አንድ ተማሪዬ ስለ ታመመ ፣ በምን መንገድ ልንረዳው እንደምንችል እንድታማክረኝ ነበር ”

“ ማ የሚባል ? ”

“ አቤል ! አቤል ፤ ታስታውሰዋለህ ? ”

“ ኦ ! አዎ አስታውሰዋለሁ ፤ ያ ጎበዙ ልጅ አይደለም ?” አሉ አቶ መዓምር ። ከአንድ ዓመት በፊት ሁለት ተከታታይ ኮርሶች አስተምረውት ነበር ። “አሁን ታዲያ ምን ነካው?” በማለት ጠየቁ ።

“ አንዲት ልጅ በዐይኑ ወደዷል የሚል መረጃ ነው ያገኘሁት” አሉ ዮናታን ፣ ከአቀማመጣቸው ለጠጥ ብለው ።

"ታዲያ ይሄ ሕመም ነው ወይስ ፍቅር ?" አቶ መዓምር ጉዳዩን ቀለል አድርገው በመመልከት ዐይነት ፈገግታ ፈገግ አሉ ። የዮናታን ግንባር ግን ፈጽሞ አልተፈታም ።

"ሕመም ነው እንጂ ! ከባድ ሕመም ።"

"ማለቴ'ኮ ፤" አሉ አቶ መዓምር ፤ ከዮናታን ፊት ላይ ፈገግታ ባጡ ጊዜ ሽምቅቅ ብለው ነገሩን በማስተባበል ዓይነት ፤ "ማለቴ ፤ ይሄ የተፈጥሮ ጉዳይ ነው ፤ ሁላችንም ብንሆን በዐይናችን ሳናፈቅር አላለፍንም ። እንዲያውም ከራሴ ልምድ ብነሣ ተዋውቄ ካፈቀርኳቸው ይልቅ በዐይኔ ያፈቀርኳቸው በቁጥር ይበዛሉ ።"

"ለነገሩማ ፍቅር የሚጀምረው በዐይን ነው" በማለት ዮናታንም ፈገግ አሉ ።

"ታዲያስ ፤ አሁን እኮ ወደኔው መጡ" አሉ አቶ መዓምር ፤ የዮናታን ፈገግታ ለበለጠ ጨዋታ ጋብዟቸው ። "ፍቅር ጤንነት ነው ። በኔ ግምት ሕመም ወይም በሽታ የሚሆነው ጥላቻ ነው ። ዐይን ደግሞ ምን ጊዜም እንዲያፈቅር ያስፈልጋል ። ይህ ራሱ የሕይወት ቅመም ነው ። መጥፎ የሚሆነው ዐይን መጥላት ሲጀምር ነው ። ዐይን ተጨፍኖ አይኬድ ነገር !"

ዮናታን ውይይቱ ወደ ቀልድ እንዳዘነበለ ወይም ደግሞ መልኩን እንደ ለወጠ ተሰማቸው ። እሳቸው አክብደው ያመጡት የአቤል ጉዳይ ፤ ለአቶ መዓምር ለምን ቀልሉ እንደ ታያቸው ዮናታን ሊገባቸው አልቻለም ። 'አቀራረቡ ይሆን ?' ሲሉ በልባቸው አሰቡ ።

"የአቤልን የዐይን ፍቅር ግን ፤ እንዲህ አቅልለን አናየውም" አሉ እንደ ገና ኮስተር ብለው ፤ "በደረጃ እኛ ከምንለው ብዙ ይለያል ። እንዳጠናሁት ከሆነ ፤ ትምህርቱን በሚገባ መከታተል አልቻለም ። ግድ የለሽነትን ፤ ስልቹነትን እያሳየ ነው ። አልፎ አልፎም ከገለጻ ክፍል ይቀራል ። ቀድሞ አቤልን የምታስታውሰው ከሆነ ግን ፤ እንዲህ ዐይነት ተማሪ አልነበረም ። እና መፍትሔ ካልተፈለገለት መጥፎ ሁኔታ ላይ ነው የሚገኘው" አሉና ፤ የካርልን ታሪክ ሊያጫውቷቸው ምላሳቸው ላይ ከደረሱ በኋላ መልሱት ።



"እንደ ምንም ይችን ዓመት ሊጨርስ አይችልም ማለት ነው?" አሉ አቶ መዓምር ። በዩኒቨርስቲው ውስጥ በታሪክ መምህርነት ብዙ ዓመት ስላገለገሉ ፤ የአቤል ዐይነት ችግር በተማሪዎች ዘንድ መከሠት ፤ ለእሳቸው አዲስ ነገር አልነበረም ። እንዲያውም ከጊዜ ብዛት እንዲሰለቹ አድርጓቸዋል ። ፈተና ሲደርስ መታመም ፤ ቅጡን ባጣ የጥናት ብዛት መቀወስ ፤ በጭንቀት ብዛት ማበድ ፤ በፍቅር ተጠምዶ ከትምህርት ተዘናግቶ መባረር ፤ ለዩኒቨርስቲው እንግዳ በመሆን የጎበዝ ተማሪዎች ተደናግሮ መውደቅ ፤ ይህንና ይህን የመሳሰሉት ሁኔታዎች በደረጃ ይለያዩ እንጂ ፤ በየዓመቱ በዩኒቨርስቲው ውስጥ ሳይከሠቱ አያልፉም ። አሁንም ዮናታንን እጅግ ያሳሰባቸው ጉዳይ ፤ አቶ መዓምርን ምንም ያህል አልኮረኮራቸውም ።

"መጨረሱንማ ሊጨርስ ይችል ይሆናል ። ግን የሚያስፈልገው ጨርሶ መውጣቱ ብቻ ነው እንዴ ?" አሉ ዮናታን፤ ቁጣ ባዘለ ድምፅ ።

"ማለቴ ፤ ትምህርቱን ጨርሶ ሥራ ላይ ከዋለ ፤ ራሱን በማዝናናት አሁን ካለበት ሁኔታ ነጻ ሊወጣ ይችላል ።"

"እኔ ግን በዚህ መልክ አልመለከተውም" አሉ ዮናታን ። "አቤልን ዲግሪ አስይዘን ከዩኒቨርስቲ ማባረር ሳይሆን ፤ ታላቅ ምሁር የማድረግ ኃላፊነት አለብን ። ለዚህ ብቃት ያለው ልጅ ነው ። ደግሞም አሁን ባለበት ሁኔታ ትምህርቱንም ሳይጨርስ ይችላል ።"

"እንግዲህ ለሥነ ልቡና ጥናት በሳል ለሆኑቱ እናማክራቸዋ !" አሉ አቶ መዓምር ፤ ነገሩን ለማሳጠር ያህል ።

"ለአካዳሚክ ኮሚሽኑም አስታውቀን ፤ አንድ መፍትሔ ይፈለግለት እንጂ !" አሉ ዮናታን ።

# ምዕራፍ አምስት

ከምሽቱ ሦስት ሰዓት አካባቢ ይሆናል ። ማርታ ገና ከውጭ አልገባችም ። ትዕግሥትና ሁለት የመኝታ ክፍል ጓደኞቸ አልጋቸው ላይ ጋደም ብለው ፤ ከመጀመሪያ ዓመቷ ኮርስ አንዱ የሆነውን የኢትዮጵያ ታሪክ እያጠኑ ይጠያየቃሉ ።

የመኝታ ክፍላቸው በር ሳይንኳኳ ተከፈተ ። ቤተልሔም አሰግድ አንገቷን ብቻ ወደ ውስጥ ብቅ አድርጋ ተመለከቱች ።

“ኦ ቤተልሔም ፥ ግቢ” አሏት ሦስቱም በአንድ ድምፅ ። “ ማርታ አልመጣችም እንዴ ? ” ስትል ጠየቀች ።

“ ግቢ ፥ ትመጣለች ” አሏት ደግመው ። ወደ ውስጥ ገብታ ትዕግሥት አልጋ ላይ ከግርጌ ተቀመጠች ።

“ ምነው ቆየች ፤ ቶሎ እመጣለሁ ብላኝ ነበር ? ” ካለች በኋላ ፥ ቤተ ልሔም ሰዓቷን እየችና ፥ “እንዴ ፤ ሦስት ሰዓት ከሩብ ሆኗል ” ኮ ! ለመሆኑ ብትመጣስ ዘበኞቹ ያስገቧታል ብለሽ ነው?” አለች ፥ ተስፋ በቆረጠ አነጋገር ።

“ ከመጣችስ ያስገቧታል ፤ ልጅቷኮ ማርታ ነች ” አለች ትዕግሥት ፥በቀልድ ዐይነት -የማርታን ቅልጥፍና ለመግለጽ ። በርግጥም ማርታ አምሽታ በመጣች ቁጥር “ ጥብቅ ነን ”የሚሉትን የጥበቃ ጓዶች ጥርሷን አሳይታ ውሃ አድርጋቸው ነው የምትገባው ።

“ ይልቅ ” አለች ትዕግሥት በመቀጠል ፥“ ይልቅስ መምጣቷን ተጠራጠሪልኝ ” ለቤተ ልሔምም ጉዳዩ እንግዳ ነገር አይደለም ። ይልቁንም በተሳካ ጊዜ አብረው ነው ምሽቱን የሚወጡት ። ቤተ ልሔምን ከትዕግሥት ያስተዋወቀቻት ማርታ ናት ። የእነሱ ጓደኝነት ግን ከውጭ ጀምሮ ነው ፤አራት ዓመት ያህል አሳቸው ። እንዲያውም ቤተ ልሔም

ቀድሞት ዩኒቨርስቲ በመግባቷ ፣ በመሐል ለተወሰነ ጊዜ ጓደኛነታቸው ላልቶ ነበር እንጂ ፣ መጀመሪያ ላይ በጣም ጥብቅ ጓደኞች ነበሩ ። ቤተ ልሔም አሁን የሁለተኛ ዓመት ተማሪናት ።

ቤተ ልሔም የትዕግሥት አገላለጽ ስለ ገባት ማቀችና ፣ "መምጣትስ ትመጣለች ፤እዛ ሠርጉ ቦታ'ኮ ነው የሔደችው ። ቀን አብሬአት ነበርኩ ። ስለ ሁኔታው ተነጋግረን ለነገ እንዳንደክም ፣ ዛሬ እዚሁ አድረን ጠዋት ለመሄድ ወስነናል " አለቻት ።

ትዕግሥት ትዝ አላት ። እሑድ የጓደኛዋ ሠርግ እንደሚኖር ማርታ ነግራት ነበር ።

"አንቺም አብረሽን ትሔጃለሽ ፣ አይደለም ? " አለች ቤተ ልሔም ፣ የትዕግሥትን ዐይን ዐይን እየተመለከተች ።

"እስቲ እግዜር ያውቃል ፣ ጥናቱ'ኮ ተከምሮአል ? " አለች ትዕግሥት በማመንታት ዐይነት ።

ከኮሪደሩ ውስጥ የታኮ ጫማ ድምፅ ስለ ተሰማቸው ፣ ጭውውታቸውን ለአፍታ ያህል አቋረጡ ።

እንዳች ነገር በኋላው እንደሚያባርረው ሰው ፣ ማርታ በሩን ብርግድ አድርጋ ገባች ። ቤተ ልሔምን ከክፍሏ በማግኘቷ ደስ አላት ። ትንፋሿ እጥር — እጥር እያለ ፣ "ሄይ ቤቴ ! ቆየሁ እ ! ምን ታረጊዋለሽ ! " አለችና ሳመቻት ። ትዕግሥትንም ሳመቻት ። ከማዶ ያሉትን ሁለት ልጃገረዶች በፈገግታ ብቻ ሰላምታ ተለዋውጣቸው ፣ ከቤተ ልሔም ጎን ቁጭ አለች ።

"እንዴት ነው ? " አለችና ቤተ ልሔም ጠቀስ አረገቻት ። በሳመቻት ጊዜ ፣ ከንፈሯ እጅግ ለስልሶባት ነበር ። ለምስጢር ድርጊቶቻቸው ከንግግር የበለጠ በጥቅሻና በምልክት ይግባባሉ ።

"ምን ታረጊዋለሽ ? " አለችና ማርታ ፣ ከነልብሷ መኝታዋ ላይ ወጥታ ጋደም አለች ።

"ግን በርግጥ ሠርጉ ቦታ ነው፤ያመሸሽው ? " አለች ቤተልሔም ፣ ጥርጣሬ በተሞላበት አነጋገር ።



"ሙቼ እዚያው ነው ያመሸሁት " አለች ማርታ ። ስንሠራራ አመሸንና ፣ የቅርብ የሆንነው ማታ ጓዳ ገብተን ራት ከበላን በኋላ ፣ አንድ ውስኪ ተከፈተልን ። ሌላ ነበር ! አትሔጂም ብለውኝ በግድ ነው የመጣሁት ።"

"ፓ ! ግን ምንም የቀመስሽ አትመስዪም "
"ሁለት መለኪያ ነች'ኮ የጠጣኋት ፣ ቤቴ ሙች! "

"እሺ ፣ ከዚያስ ? ማ ሸኘሽ ? " አለቻት ፣ ከፊል ቅናት በተቀላቀለበት አነጋገር ።

"አንዱ ባለ ቆርቆሮ ነዋ ! "

ትዕግሥት ነገሩ ስለ ገባት ማቀች ። ከማዶ የተኙት ሁለት ልጃገረዶችም ከንፈራቸውን ከድነው ማቁ ። በከፊል ቢያጠኑም በከፊል ጆሮአቸው እነማርታ ጨዋታ ላይ ነበር።

"በሉ እንተኛ " አለች ማርታ ፣ ሹራቧን እያወላቀች "ነገ'ኮ በጠዋት ተነሺዎች ነን ።"

"አዎ ! እረ ትላንትም አልተኛሁም ። ሁኔታውን ላረጋግጥ ብዬ ነው'!ኮ አንቺጋ የመጣሁት!" አለችና ቤተ ልሔም ከተቀመጠችበት ተነሣች ።

"ሁኔታው ሁሉ የተሟላ ነው ። ጠዋት ተነሥተን መሔድ ብቻ ! "

"ደሞ ትዕግሥትን አንድ በያት ። እያመነታች ነው "

"ለምኑ ? ለመሔድ ? " አለች ማርታ ፣ በቁርጠኝነት አነጋገር ። " ወዳ በቀበሌ ተገዳ ! " ልማዳዊ የአነጋገር ዘዴዋ ነው ።

"ሆሆ ! ፈተና'ኮ እየተቃረበ ነው " አለች ትዕግሥት ፣ በማመንታት ዐይነት ። አብዛኛው ልቧ ግን በመሔድ ላይ ያጋደለ ነበር ።

"ታዲያ በአንድ ቀን ተአምር ልትፈጥሪ ነው ? " ስትል ቤተ ልሔም ተነሣች ። ልትሔድ የነበረችዋ ቤትዮ ጭራሽ ወገቧን ይዛ ማብራሪያ ትስጥ ገባች ። የሁለተኛ ዓመት ተማሪ በመሆኗ ፣ አገላለጿ አሁን የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች የሚ

ጨነቁበትን ሁኔታ ፣ “ አርጌው አልፈአለሁ ” በሚል የበላ ይነት ስሜት ነው ።

“ አንድ ነገር ልንገርሻ ትዕግሥት ” ስትል ጀመረች ። “ ይሄ ፍሬሽማን ላይ መረበሽ ፣ መጨነቅ ፣ ራስን ማሠቃየት ዝም ብሎ እየተለመደ የመጣ ነገር ነው ። እምናም በኛ ጊዜ እንዲሁ ነበር ። ማጥናት ሳይሆን ፊደላትን መስነጣጠቅ ነበር የተያዘው ። በዚያ ላይ ፣ ሁሉ ነገሩ የጭንቅ ግቢ ነበር የሚመስለው ፤ ከፊሉ ዊዝድሮዋል ለማውጣት ሲሯሯጥ ፣ አንዳንዱም ሲቀልድ ፣ አንዳንዱም ሌክቸረሮች በእጅዋ ናቸው እየተባለች ስትታማ ፣ አንዳንዱ ከአቅሙ በላይ ሌሊቱን ሙሉ ሲያጠና በተቀመጠበት እንቅልፍ ሲወስደው . . . ምኑ ቅጡ ፣ ግን መጨረሻው ምን ሆነ መሰለሽ ! ”

ከማዶ ያሉት ሁለት ልጃገረዶችም ፣ ጆሮአቸውን በጣም አስልተው ይሰማሉ ። ማርታ ብቻ እንደ ማሽለብ ስላረጋት በስመመን ነበር የምታዳምጠው ።

ቤት ልሔም ቀጠለች ፤ “ መጨረሻም ላይ ያው የገና ማዕበል መጣና ሁሉንም ለየ ። መውደቅ ያለበት ወደቀ ፤ ማለፍ ያለበት አለፈ ። ”

“ ታዲያ ለእሱማ ነው ‘ ኮ ይሄ መፍጨርጨር ” አለች ትዕግሥት ባልተደነቀ ስሜት ።

“ ማለቴ ” አለች ቤተ ልሔም ፣ ልትል የፈለገችውን በቅጡ እንዳልተረዱላት በመገመት ። “ ታዲያ መውደቅ ወይም ማለፍ ፣ ከሁለት አንዱን መጋፈጥ የማይቀር ዕዳ ሆኖ ሳለ መጨነቁ ምን ይጠቅማል ? እንደኔ እንደኔ የሚያስፈል ገው የተወሰነውን ነገር በፕሮግራም ማጥናት ነው ። ከዚያ ውጭ የራስ ጉዳይ ! ግን የሚገርምሽ ደግሞ ፣ ዩኒቨርስቲ ውስጥ አንድ የሚያስጠላው ነገር ፣ አንች እንደ ሌላው ጥናቱ ላይ ትኩረት ሳታደርጊ ፣ ደኅና ውጤት ያመጣሽ እንደ ሆን ሐሜቱ መከራ ነው ። ‘ሌክቸረሩን አውርዳው ነው ፣ ሬጅስትራር ውስጥ ዘመድ አላት ፣ ፈተና ወጥቶላት ነው ፣ ሌክቸረሩን እግሩ ላይ ወድቃ ለምናው ነው ፣ ጉቦ ሰጥታ ነው’ እረ ስንቱ ! ዩኒቨርስቲ የገባ ተማሪ በግድ መሠቃየት አለበት እንዴ? እንደኔ ‘ የአንደርስታንዲንግ ’ ጉዳይ ይመስ



ለኛል ። አንዳንዱ ብዙም ሳይጨነቅ ቶሎ ይገባዋል ። አን ዳንዱ ደግሞ ብዙ ሠርቶ ትንሽ የሚገባው አለ . . . ሀእ?”

በተዘዋዋሪም ቢሆን ፣ ራሷን በፕሮግራም ከሚያጠኑትና በቀላሉ ከሚገባቸው ምድብ ነበር የምታወራው ። እንዲህ ብዙ እንድትናገር ያረጋት ቁስሏ ነው ። እምና የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ ሳለች ፣ ከላይ የጠቀሰቻቸውን ሁኔታዎች ታም ታባቸዋለች ። እንዲያውም በጣም ደካማ በነበረችበት በኢ ትዮጵያ ጂኦግራፊ ኮርስ “ B ” ማምጣቷ ከአስተማሪው ጋር በግልጽ እንድትጠረጠር አድርጓታል ። እሷ ግን ፣ “ እኔ የቤንትሜሪ ተማሪ ስለ ነበርኩና ጥሩ መሠረት ስለ ነበረኝ የዩኒቨርስቲ ትምህርት በቀላሉ ነው የሚገባኝ ” ባይ ነች ። የማንኛውም የትምህርት ዐይነት ገለጻ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ስለሚሰጥና እሷ ደግሞ ፣ እንግሊዝኛ “ ፍሎዌንት ነኝ ” ስለምትል ፣ በቀላሉ ለመረዳቷ ይህም በከፊል ታማኝነት ያለው መከላከያዋ ነው ። በእርግጥም እንግሊዝኛ ስትናገር ለሚሰማት ፣ ፕሮናውንሲሽን የሚሸጥ ቢሆን ኖሮ ብዙ ያወጣላት ነበር ።

“ እምልሽ ” ስትል ቀጠለች ፣ “ አንዳንዶቹ እንደ ሚሉት ‘ጭራሽ አላጠናም’ ማለት እንኳ ዝም ብሎ ነው ። ማንኛውም ተማሪ ቢሆን ያጠናል ። የሚለያየው የአጠናን ደረጃውና ስልቱ ብቻ ነው ። ግማሹ ሌሊቱን ከቀን እያገናኘ ያጠናል ። ግማሹ ደግሞ በፕሮግራም አጭር ጊዜ ያጠናል ። በሳይኮሎጂ እንደ ተማርነው ግን ፣ ጥሩው ዘዴ በየአንድና ሁለት ሰዓት ጥናት ውስጥ የተወሰነ ዕረፍት መውሰዱ ነው ። እንቅልፍ በደንብ መተኛትም አእምሮ ጥናትን በደንብ እን ዲቀበል ይረዳል ። ”

የሳይኮሎጂ ነገር ስታነሣ ግልፍ አላት ። ጥሩ አስተማሪ ደርሶአት ስለ ነበር በርግጥም ጥሩ ዕውቀት ገብይታበታለች።

“ የሳይኮሎጂ አስተማሪያችን ስለ ጥናት ዘዴ ሲያስተ ምር ምን አለን መሰለሽ ?‘ከዩኒቨርስቲ ውስጥ እነዚህ ከመጠን በላይ እያጠኑ የሚያልፉ ተማሪዎች ፣ የመማር ኃይል (ፓቴን ሺያል) የላቸውም ። ዩኒቨርስቲው ውስጥ የሚቆዩት በትግል ነው ። ስለዚህም ጨርሰው በሚመደቡበት ሥራ ላይ በቂ ግል

ጋሎት ሊሰጡ አይችሉም’ ያለው ትዝ ይለኛል ። ችሎታው ካለሽ በቀላሉ ሊገባሽ ይችላል ። ችሎታው ከሌለሽ ግን ከንቱ ትግል ነው . . . ግን እኮ ሳይኮሎጂ መስጠት የነበረበት መጀመሪያ ዓመት ላይ ነው ። ከብዙ ጭንቀት ሊያድን ይችል ነበር” ስትል የራሷን ግምት አከለችበት ።

ማርታ ከስመመናዊ እንቅልፏ ባንና ተመለከተቻቸው ፤ አይኗ ፍም መስሏል ።

“ አልተኛችሁም እንዴ? ” አለች ግንባሯን እንደቋጠረች ፡ ከእንቅልፍ መንፈስ ሳቢያ በሚመነጭ ቁጣ የተሞላበት አነጋገር ። “ አንቺ ቤቴ! ሒጂና ተኚ ፡ ጠዋት እኮ ሐያጆች ነን ።”

ቀና ብላ ወደ ማዶ ደሞ ተመለከተች ። ሁለት ልጃገረዶች ገና እያጠኑ ነበር ። መብራቱ ሊጠፋላት እንደማይችል ገባትና ብስጭት ብላ ተመልሳ ተኛች ።



# ምዕራፍ ስድስት

አቤል ገና ጎህ ሳይቀድ ነው ከእንቅልፉ የሚነቃው ። የዛሬን እያርገውና በርትቶ በሚሠራበት ጊዜ ፡ ለጥሩ ጥናት የመረጣት ሰዓት ከሌሊቱ 11—1 ፡ 30 ያለችውን ነበር ። በዚያው ለምዶበት አሁንም ወደ 12 ሰዓት አካባቢ ይነቃና ፡ የቁርስ ሰዓት እስኪደርስ ድረስ ወዲያ ወዲህ ይንጎራደዳል ። ምንጊዜም ከመንጎራደድ ጋር የተያያዘች አንድ ተግባር አለችው ። ወደ ቁርስ ከመሔድ በፊት ከለል ያለ ቦታ ሆኖ ትዕግሥት ወደ ቁርስ ስትሔድ ማየት አለበት ። የዐይኑን ፍቅር መሳለም አለበት - ሌሊቱን እንዴት እንዳደረች. . .

እንደ ወትሮው እሑድ ጠዋት ከመኝታ ክፍሉ ወጥቶ በኮሪዶሩ መስታወት በኩል ቁልቁል ይመለከታል ። አንዳንድ ልጃገረዶች ከመኝታ ክፍላቸው ወደ ቁርስ ክፍል መሔድ ጀምረዋል ። ጥቂት ቆይቶ የአቤል ዐይን የሚፈልጋት አጭር ጠይም ልጃገረድ ፡ ከሁለት ልጃገረዶች መሐል ሆና ብቅ አለች ። እንደ ሌላው ጊዜ በነጠላ ጫማና በግዴለሽ አለባበስ አልነበረም የወጣችው ። ደምቃለች ፤ የክት ልብሷን ለብሳለች ፤ ከቁመቷም ከፍ ብላለች ። አቤል ቁልቁል ትክ ብሎ ተመለከታት ። በዐይነ ሕሊናው ከመኝታ ክፍሏ ገብቶ ሻንጣዋን በረበረ ። ሳያያት ስለማይውል ፡ ከቀን ብዛት ያሏትን ልብሶችና ጫማዎች ዓይነት ጠንቅቆ ያውቃል ። እንዲህ ዐይነት ጫማ ፈጽሞ አልነበራትም ፤ የተውሶ መሆኑን ገመተ ።

‘ስፒል’ ታኮ ያዋሰቻት ቤተ ልሔም ነበረች ። ማርታና ቤተ ልሔም የጎደላትን መድመቂያ ሁሉ አሟልተው ፡ ኩል ቀብተው ፡ ሽቶ ረጭተው ፡ የከንፈር ቀለም ቀብተው ነበር ያወጧት ። ብቻ እንደነሱ በስሱ ቀይ የከንፈር ቀለም ላይ ቡና ዐይነት እንደርብልሽ ቢሏት ሳትሰማ ቀረችና ተዋት ። ቅንድቧንም አልላጭም ብላ አናደደቻቸው ። አረማመዷም ያው ከደብረ ዘይት ይዛው የመጣችው ዐይነት ነበር ። በስፒል

ታኮው መራመድ እምብዛም አልቻለችበትም ። ግን ብልሀ
ስለ ሆነች ፣ ሚዛኗን እየጠበቀች ነበር-እግሮቿን የምትወረው
ራቸው ። ማርታና ቤተ ልሔም አለባብሰዋት ከጨረሱ በኋላ
አንዳንድ ጉድለቶቿን አይተው “ ገና ይቀራታል ” በሚል
መንፈስ እየተጠቃቀሱ ነበር የወጡት ። ለአቤል ግን በጣም
ደምቃበታለች ። ‘ የዛሬው ሌላ ነው የዋዛ አይደለም ’ አለ
በልቡ ። ዐይኑ ቀስ በቀስ ደም እየመሰለ ሔደ ። ‘ የታባታቸው
ነው የሚወስዷት?’ ሲል ለራሱ ተነፈሰ ። ሁለቱን ልጃገረዶች
ደምሥሩ ተገታትሮ ተመለከታቸው ። በተለይ ማርታን ! . . .

ማርታ አቤልን ትወደዋለች ። የጓደኛዋ የዓይን ፍቅረኛ
ስለሆነ ፣ በትምህርቱ ጎበዝ ነው ስለሚባል ፣ ወይም በሌላ
በየትኛው ምክንያት እንደሆን ለራሷም አይገባትም ። ግን
ትወደዋለች ። ሳታየው መዋል አትፈልግም ።

አቤል ግን ማርታን አይወዳትም ። ሁልጊዜ ከትዕግሥት
ስለማትለይ ታውቅብኛለች ብሎ ፈርቶ ፣ ከትዕግሥት ጋር
ሆነው ያሙኛል ፣ ይበጭቁኛል ፣ ያሾፉብኛል ብሎ ጠርጥሮ ፣
ትዕግሥትን በደንብ እንዳያያትና እንዳይጠግባት የእሷ አብሮ
መሆን ያገደው መስሎት ! ትዕግሥትን ታባልግብኛለች
ብሎ ፈርቶ ! ምክንያቱም በቅጡ አይገባውም ፤ ግን ለሁ
ሉም ይጠላታል ። ሳያያት ቢውል ይመርጣል ።

አሁንም በልቡ ረገማት ። በቀሉት ዐይኖቹ ውስጥ
እንባ የተቋጠረ መሰለውና ዐይኑን ጨመቀ ። ነገር ግን
ውስጥ ውስጡን ፤ ከመቆጥቆጥ በቀር ጠብ ያለ ነገር አልነ
በረም ።

“ ተከታትዬ መድረሻቸውን ማየት አለብኝ ! ” አለና
ዛቶ ። ተመስጦ ውስጥ ስለገባ ፣ አጠገባቸው ያለ ነበር የመ
ሰለው ። የሁለት ፎቅ ደረጃ መውረድ እንዳለበት የታየው
ቁልቁል ጉዞ ሲጀምር ነው ።

በቅርብ ጊዜ እንዳመጣው ጸባይ እጁን ኪሱ ከቶ ተጀ
ንኖ ሳይሆን ፣ ከሩጫ ባልተለየ ርምጃ ደረጃውን ወርዶ ወደ
ውጭ ብቅ ሲል ፣ ከማርታና ትዕግሥት ጋር ዐይን ለዐይን
ተገጣጠሙ ። ክው አለ ፤ እነሱም ክው አሉ ። ያጋጣሚ
ጉዳይ ነው ። እሱ የገመተው ደረጃውን እስኪወርድ እነሱ



ብዙ ዐልፈው ይሔዳሉ ብሎ ከኋላቸው ሊከታተል ነበር ።
ነገር ግን ቤተ ልሔም የሆነ ዕቃ ረስታ ወደ መኝታ ክፍሏ
ስለ ተመለሰች ፣ ቆመው እየጠበቋት ነበር ።

አቤል በድንጋጤ የሚሔድበት ጠፋው ። አይቶ እንዳላ
ያቻው ቶሎ አለና ዐይኑን ሰበረ ። ከአካባቢው ለማምለጥ
ያህል ፣ ወደ ቀኙ ታጥፎ ባላሰበው መንገድ ወደ ዋናው በር
ተጓዘ ። ከአጥር ውጭ ቀድሞ መጠበቅ በድንገት የመጣለት
ሐሳብ ነበር ።

“ ምን እንዳው ፣ ይቺ ቤቴ ደሞ አይሞላላት ” አለች
ማርታ ፣ ዐይኗን ወደ ሴቶች መኝታ ሕንጻ ወርውራ ።
ትዕግሥትን ከሐሳቧ ለማዘናጋት በድንገት የወረወረቻቸው
ቃላት ነበሩ ። አቤልን ካየችበት ሰዓት ጀምሮ የትዕግሥት
ልብ ትርታ ፣ በድንጋጤም ይሁን በደስታ ምን ያህል ከፍ
እንደሚል ማርታ ታውቃለች ።

ቤተ ልሔም ፊቷን ይቅርታ በሚጠይቅ ፈገግታ
ሞልታ ፣ ቁና ቁና እየተነፈሰች መጣችላቸው ።

“ አዳር ነው እንዴ?” አለች ማርታ ፣ ከፊል ቀልድ
ከፊል ንዴት በተቀላቀለበት አነጋገር ። ብዙ ስላቆየቻቸው
በልቧ በሽቃለች ። ቤተ ልሔም ልማዷ ነው ። በጣም ስት
ደሰት ወይም ደንግጣ ስትረበሽ ጥቂት ትረሳለች ። ሽንቷ
ደሞ ፣ አሁንም አሁንም ይመጣል ። ግን ሽንት ቤት ትገባ
ለች እንጂ ጥቂት ጭርር አርጋ ነው የምትወጣው ። በተለይ
ወደ ፈተና ክፍል ልትገባ ስትል ፣ በግማሽ ሰዓት ውስጥ
ሦስቴ ያህል ሽንት ቤት መድረስ አለባት ። አሁንም የሥርጉ
የደስታ ስሜት በውስጧ ስላለ ፣ ከመኝታ ክፍሏ የረሳ
ችውን ዕቃ ከያዘች በኋላ ፣ ሽንት ቤቱን ለሁለተኛ ጊዜ
ጎብኝታው ነበር የመጣችው ። ተጠናቃ መውጣት ትፈል
ጋለች ፤ ግን የተጠናቀቀች አይመስላትም ።

“ በሉ እባካችሁ ይሆን ግቢ ቶሎ እንልቀቅ ” አለች
ማርታ ። “ ተማሪው ’ኮ ወደ ቁርስ ቦታ መጉረፍ ጀምሮ
አል ” የተማሪዎቹን ትችት በመጠኑም ቢሆን ስለምትፈራ
እንዲህ ደምቃ በብዙ ተማሪ ፊት ማለፍ አልፈለገችም ።

ግቢውን ለቀው ሲወጡ፥ትዕግሥት በዐይኗ ግራ ቀኙን እየማተረች ነበር — አቤልን ፍለጋ ። ከደረጃ በወረደበት ሰዓት በአጭር ጊዜ እይታም ቢሆን፥ስሜቱን በሚገባ ተረድታለች ። የቅናት ፥ የመጨስ ሁኔታ አይታበታለች ። እና አሁን ተሸማቃ በዐይኗ ፈለገችው ፤ ብታየው እኮ ማርታን ከለላ አድርጋ የምትደብቀው ይመስል !

እሷ ልታየው አልቻለችም ። እሱ ግን ራቅ ካለ ቦታ ጥግ ይዞ እጁን በኪሱ አድርጎ ይመለከታቸው ነበር ። አስፋልቱን ተሻገሩ ። በዐይኑ ተከተላቸው ። ቆመው ታክሲ ሲጠብቁ ትዕግሥት አቤልን ለማየት ፈለገች ። መጀመሪያ ማርታና ቤተ ልሔም እንደማይነቁባት አረጋገጠች ። ከወደ መጡበት አቅጣጫ ዘወር አለችና የሐውልቱን አካባቢ ቀስ ብላ መቃኘት ጀመረች ። እንዳጋጣሚ በእሷና በአቤል መካከል አንድ የምታውቀው ሰው ከፊት ለፊቷ ሲመጣ ተመለከተችና እጇዋን እውለበለበች ። አቤል ለሱ የተላከ መልእክት መሰለውና ከደስታ ብዛት እሚያደርገው ነገር ጠፋው ። ከሰላምታው በተጨማሪ ሞቅ ያለ ፈገግታ ፥ ሆን ብላ ለሱ ያሳየችው መሰለው ።

እንኳን በፈገግታ ጊዜ ይቅርና ገና ልትናገር ስትል ጉንጯ ምንኛ እንደሚሠረጎድ ያውቃል ። መጀመሪያ ያየት ዕለት ‘ዲምፕዷ ታየ ! ሣቀች እኮ ! ሣቀች !’ አለ በድንገት ፥ ድምፁን እንደ ማልጎምጎም ዐይነት አፈን አድርጎ ። ለአጭር ቁመቷ ተመጥኖ የተሠራው የሚያምረው እግሯ ፥ ለሱ ብቻ የተፈጠረ እሚመስለው ባቷና ተረከዟ በሐሳቡ ታየው ። ከፋይ የሚመስለው ገጽታዋ እንደ ንጋት አድማስ እየፈካ የሳቂታ ዐይኖቹን ብርሃን ወደሱ ሲወረውር ታሰበው ። እጆቹን ከኪሱ አወጣና አወራጫቸው ። ከዛ በኩራት መንፈስ ወገቡን ያዘ ። ‘አዎን ልክ ነው ፤ትሣቅ ! ትዕግሥት ብቻ ትሣቅ ! ያምርባታል !’ አለ አሁንም አቤል ። ልክ እንዲህ ሲል ሳያስበው ራሱ መሣቅ ጀምሯል ። ከፊት ለፊቱ ሕፃን ልጅ ያቀፈች ሴትዮ ታክሲ እየጠበቀች ነበር ። ታዲያ ባጋጣሚ ወደ አቤል ፊቷን ስትመልስ ፥ አቤል ያለ ምክንያት እያያት ሲሥቅ ደነገጠችና ፥ “በስማም” ብላ የሕፃኑን ፊት በነጠላዋ ለበስ አድርጋ ፥ በፈጣን እርምጃ ወደ ማዶ ተሻገረች ።



ትዕግሥት “ሥቃ” ካበቃች ቆይታለች ። አቤል ግን አሁንም ችምችም ያለው ጥርሷና ስስ ከንፈሯ ይታየዋል ። “ለምንድነው ግን ” አለ ለራሱ ። “ለምንድነው ይሄን ውበት ለማንም የምታሳየው?!” ደሞ ቅናቱ አገረሸበት ።

“ምን አስፈራህ አቤል ? ለምትወዳት ልጅ አንድ ቃል መተንፈስ አቃተህ ! ምን መሰለችህ ? እርሷም ሰው ነች’ኮ ። ወጣት ነው ፤ ወጣት ነች። ‘ወደድኩሽ’ ማለት ምን ያስቸግራል ?‘ደስ ትይኛለሽ’ በላት ። እንቢ ብትልህ ‘ኮ አትሞትም!. . .”

ልክ ይሄን ከማለቱ እነ ትዕግሥት ታክሲ አስቆሙና ገቡ ። መኪናው ተነሣ ። አቤል ኪሱን ዳበሰ ፤ ሠላሳ አምስት ሳንቲም ብቻ ነበረችው ። በስሙኒዋ ሊፈርድባት አሰበ ። ግን ወዴት ? ራቅ ብሎ ስለ ነበር ፥ የት ብለው ታክሲውን እንዳስቆሙ መስማት አልቻለም ነበር ፤ በሸቀ ። ታክሲዋ ከዐይኑ እስክትርቅ ተከተላት ። ቤተ ልሔምና ማርታ ከኋላ ወንበር ላይ ፥ ትዕግሥትን ከመሐከላቸው ነበር ያስቀመጧት ።

“ሌቦች!” አላቸው በልቡ ፥ ንብረቱን ሠርቀውበት እንደ ሔዱ ሁሉ ።

ወደ ዩኒቨርስቲው ግቢ ተመልሶ መግባት አልፈለገም ። ግቢው አስጠላው ። ቀጥታውን መንገድ ይዞ ሔደ ። የካቲት 12 ሆስፒታል ሲደርስ ለአፍታ ያህል ቆም ተመለከተ ፤ እጁን በኪሱ አርጎ በመገረም ዐይነት እንቅስቃሴውን ቃኘ ።

ሆስፒታሉ በር ላይ ትርምስ ነው ። አዳሪ አስታማሚዎች በጋቢ ተጀቡነው ፥ በእንቅልፍ እጦት ተዳክመው ዐይናቸው ቀልቶ ይወጣሉ ፤ ጎብኚዎች ስንቅ ይዘው ወደ ውስጥ ይገባሉ - ዶፍ ዶፍ እያሉ ፤ መግባት ያልተፈቀደላቸው ደግሞ በሩ ላይ ተኰልኩለው ዘበኛውን ይለማመጣሉ ። ሆስፒታሉ በር አጠገብ ባለችው የፍራፍሬ መደብር መስኮት ላይ ብርቱካንና ሙዝ ገዥው ደርቷል ።

“ቁርጡ ታውቆለት ‘ሕመምተኛ’ የተባለ ሰው የታደለ ነው ” ሲል አሰበ አቤል ። እንደዚህ ጎብኚዎች ይጎርፉለታል ። የሕመሙን ዐይነት ይጠይቁታል ፤ መድኃኒት ይፈልጉለታል ፤ ብቸኛ እንዳይሆን ወዳጅ ዘመዶቹ በፈረቃ

አጠገቡ ያድሩለታል ፤ ይውሉለታል ። ሕመሙ ያልታወቀለት ሰው ግን ብቻውን ነው የሚሠቃየው ፤ የሚቃጠለው ፤ የሚንገበገበው . . . የትዕግሥትን ነገር ያለኔ ማን ያውቅልኛል ?. . ”

እስክንድር በድንገት ከኋላው መጥቶ ፣ ‘ ታዲያ ለምን ሕመምህን አትነግረንም ? ለምን መድኃኒቱን እንፈልግልህም ? እኛ አንተን ለመርዳት አንሰን ነው?’ የሚለው መሰለውና ከሐሳቡ ባነነ ። አጠገቡ ማንም ሰው አልነበረም ። ከራሱ ጋር እየተነታረከ ወደ አራት ኪሎ የሚወስደውን ቀጥታ መንገድ ይዞ ሔደ ።

“ ለመሆኑ ” ሲል ሐሳቡን ቀጠለ ። “ ለመሆኑ ፣ የሕመምተኝነት ምልክቱ ምንድነው ? አንድ ሰው ሕመምተኛ ለመባል የግድ መቁሰል ፣ መንፈራገጥ ፣ ማቃሰት ፣ መውደቅ ፣ መድማት ወይም አልጋ ላይ መቅረት አለበት እንዴ? ይህ በግላጭ ካልታየ አይሆንም እንዴ? ከውስጥ መቁሰልም አለ ‘ኮ ከውስጥ መድማትም አለ’ ኮ! ሀአ? ”

ሳያስበው እጁን አወራጨ ። አንዲት አሮጊት በአጠገቡ ሲያልፉ አዩትና ፣ “ ወይ ልጄን ፣ እንደኔ ሐሳብ ገብቶታል ” አሉ ።

አልደነገጠም ። ቀና ብሎ አያቸውና ዝም ብሎአቸው ሔደ ።

አራት ኪሎ አደባባዩ ጋ ሲደርስ ፣ የትራፊክ መብራት እንደ ያዘው ሁሉ ቀጥ ብሎ ቆመ ። ቀጥታ መንገድ ቢሆን እግሩ እስካደረሰው ድረስ ዝም ብሎ ይቀጥል ነበር ። መስቀልኛ መንገድ ላይ መድረሱ ሐሳቡን ከፋፈለው ። ወዴት እንደሚሔድ ግራ ገባው ። ቁርስ ሳይቀምስ መውጣቱ ታወሰው ። እንዲያው ታወሰው እንጂ ሆዱ አልፈለገም ። ‘ ምግብ ምን ያደርግልኛል ? ’ አለ በሐሳቡ ፣ ‘ ወስፋቴ ተከፍቶ ፣ አምሮኝ ካልበላሁ ምን ይጠቅመኛል ? እንዲያው ጥርሴ ንና ጨጓራዬን ማድከም ነው ትርፉ ። ’

ወደ ፒያሳ የሚወስደውን መንገድ መርጦ ወደ ቀኙ ታጠፈ ። ጥቂት እንደ ተጓዘ ከአንድ ቡና ቤት ውስጥ የሆነ



ሙዚቃ ጆሮውን ጠለፈው ፤ ዘው ብሎ ገባ ። ጠዋት እንደ መሆኑ መጠን ያን ያህል ሰው አልነበረም ፤ የመልካሙ ተበጀ ዜማ በአዳራሹ ይንቆረቆራል ።

“ ኧረ መላ ምቱ ወዳጅ ዘመዶቼ
ዐይናፋር ሆኜአለሁ ዐይን አፋር አይቼ
ሰላምታ አልሰጠኋት ፣ አላነጋገርኳት
በዐይን ብቻ እያየሁ አንድ ዓመት ወደድኳት . . ”

አሳላፊዋ በድንገት ከፊቱ ተገትራ ፣ “ ምን ልታዘዝ ? ” አለችው ።

“ ሻይ ፣ ሻይ ! ” አላት አቤል ፣ በሙዚቃው ጣልቃ ስለ ገባችበት ከአጠገቡ እንድትሔድለት ተቻኩሎ ።

“ . . . ዐይኔ ተወርውሮ ፣ ዐይኗ ላይ ካረፈ
ድፍን ዓመታችን መጋቢት አለፈ
ሰላምታ አልሰጠኋት አላነጋገርኳት
በዐይኔ ብቻ እያየሁ አንድ ዓመት ወደድኳት
ኧረ መላ ምቱ ወዳጅ ዘመዶቼ
ዐይናፋር ሆኜአለሁ ዐይናዐፋር አይቼ . . . ”

አሳላፊዋ ሻዩን ይዛ ስትመጣ የመልካሙ ጨዋታ አልቆ የመዝጊያው ዜማ ነበር የቀረው ። ሻዩን አጠገቡ ስታስቀምጥለት አቤል ዐይን ዐይኗን በልመና ዐይነት እየተመለከተ ፣
“ እባክሽ ይሄን ዘፈን ድገሙት በያቸው ” አላት ።

“ ከሬዲዮ እኮ ነው የሚተላለፈው ፤ የእሁድ ጠዋት ፕሮግራም ” አለችው ።

ሽምቅቅ ብሎ በዝምታ ሻዩን እያማሰለ ፣ አሳላፊዋ ተመልሳ ልትሔድ ስትል ጠራትና ፣

“ እሺ ፣ ክሩ እናንተጋ የለም ? ” ሲል ጠየቃት ።

‘ እንጃ!’ በማለት ዐይነት ትከሻዋን ነቅንቃ ፣ ከንፈሯን አጣማ ፣ በቂ መልስ ሳትሰጠው ሔደች ።

‘ ሽርሙጣ!’ አላት በልቡ ፣ ‘ ይሄኔ ውስኪ ቢሆን ኖሮ የመልካሙን ክር ቀርቶ ማጫወቻውን ከነነፍሱ አጠገቤ ታመጣልኝ ነበር ። ሻይ የሚጠጣ ግን ፣ እንግዳ አይደለም ! ደሃ ምንም ነገር መምረጥ አይችልም ማለት ነው?’

አሳላፊዋ ከመጠጥ መደርደሪያው አጠገብ ባንኮኒውን ተደግፋ እንደ ቆመች ፣ አቤል በክፉ ዐይኑ አያት ። እሱ እንደ ዚህ የተናደደበትን ጉዳይ ፣ እሷ በአእምሮዋ ውስጥ ቦታም አልሰጠችው ። እምቢታዋ እሱን እንደ ጎዳው አልታወቃትም ። ይልቅ የሚያያት ለሌላ ነገር ፈልጎአት መሰላትና እሷም ታየው ጀመር ። ድርቅ ብላ ዐይናን ሳትነቅል አየችው ። ይሄኔ አቤል እንደ መሽማቀቅ ብሎ ዐይኑን ሰበረ ። ጥቂት ቆይቶ እንደ ገና ቀና ሲልም ዐይኗን ከሱ ላይ አላነሣችም ። ይኸኛው አስተያየቷ ግን ፈገግታም ታክሎበት ነበር ።

አቤል የአሳላፊዋን የገበያ (ፍለጋ) ፈገግታ በሌላ ተረጎመው ። " የዐይን ፍቅር " ዜማ እንዲደገምለት በመጠየቁ የውስጥ ቁስሉን ዐውቃበት ፣ የምትሥቅበት መሰለውና አፈራት ። አሥራ አምስት ሳንቲሙን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦላት ፈትለክ ብሎ ወጣ ።

ከኋላው ገረመመችው ። በዝግታ የመልካሙን ዜማ እያፏጨ ፣ በልቡ ግጥሙን እየደጋገመና ከራሱ ስሜት ጋር እያያያዘ መንገዱን ቀጠለ ።

" . . . ሰላምታ አልሰጠኋት ፣ አላነጋገርኳት
በዐይኔ ብቻ እያየሁ ሁለት ወር ወደድኳት
ዐይኔ ተወርውሮ ዐይኗ ላይ ካረፈ
ድፍን ሁለት ወሬ ታኅሣሥ ዐለፈ "

አንድ ስሜት ከውስጡ ተሰማው ። የደስታ ወይም የኅዘን ብሎ መተርጎም ያዳግታል ። ብቻ የሚፈጥረው ስሜት ነው ። በሙዚቃ ኃይል የልብ ቁስል ሲፈነቀል እያመመ ፣ እየወጋ ፣ እየቆረጠ ደስ የሚል ስሜት ይሰማል ።

' ሙዚቃ የሕይወት ማዳበሪያ ነው ' ሲል አሰበ አቤል ፣ 'ሙዚቃ ምግብ ነው ። ሙዚቃ የምስጢር ጓደኛ ነው ፤ ሙዚቃ መዝናኛ ነው ። ሙዚቃ ሁሉንም ነው ። '

የሁለተኛ ዓመት ተማሪ በነበረበት ጊዜ ፣ የሚያውቀው አንድ ሰው መንገዱ ላይ አገኘ ። ቀድሞውንም በዕድሜ በሰል ያለ ሰው ነበር ። አሁን ደግሞ ይብስ በኑሮ የተጎሳቆለ ይመስላል ።



" ታዲያስ ጃል ፣ እንደምን አለህ ? " አለ ሰውዬው የአቤልን እጅ አጥብቆ ጨብጦ ። ሁለቱም ስሞቻቸውን ተረሳስተዋል ።

" ደኅና ነኝ ፤ መቼስ " አለ አቤል ፣ በትሰላቸ አነጋገር ።
" ትምህርትስ እንዴት ነው? "

አቤል ይህን ጥያቄ ሲጠይቁት አይወድም ። ነገር ግን ከማንኛውም ሰው የሚቀርብለት የመጀመሪያ ጥያቄ ይሄው ነው ። ሰዎች ለምን ይሄን እንደሚጠይቁ አይገባውም ።

" ትምህርት እያቅለሸለሸኝ ነው እባክህ ! " አለ አቤል፣ ምን ያህል እንደ ተሰማው ለማሳየት ፊቱን ኮሶ አስመስሎ ።

" እንዲህ አትበል እባክህ " አለ ሰውዬው ፣ የውስጥ ስሜቱን በሚገልጽ አነጋገር ። " የሥራ ዓለም እንዴት እንደሚያቅለሸልሽ ባየኸው ። እኔ ትምህርቴን አቋርጬ ሥራ የገባሁበትን ቀን እየረገምኩ ነው ። የዛሬ ገንዘብ እንደ ሆን እንዱንም ቀዳዳ በቅጡ አይሸፍንልህ ። ትርፉ ስም ብቻ ነው ። ኧረ ተማሪነት በስንት ጣዕሙ ! "

' ሁሉም ያለበትን እንደ ረገመ ነው ' አለ አቤል በልቡ ፣ ' ተማሪው ሠራተኛ መሆን ይፈልጋል ፤ ሠራተኛው ደግሞ ፣ ወደ ተማሪነት መመለስ ይሻል ፤ ወጣቱ ያለዕድሜው እንደ አዛውንቱ መጀነንና መከበር ይፈልጋል ፤ ሽማግሌው ደግሞ ፣ እንደ ወጣቶች ጉርድ ሸሚዝ ለብሶ መለወጥ ፣ መታደስ ፣ መሻሻል ይፈልጋል ። ለውጥ የሕይወት ቅመም ናት ይባል የለ ! አዲስ ነገርንና ለውጥን መመኘት መቼም የህልውና ምልክት ነው ። ግን የያዘውን ወዶ ባለበት የሚኮራና የሚመካ ሰው ማን ይሆን? ብርቱ ሰው ማለት እሱ ነው ። '

ሰውዬው ከአቤል ጥያቄም ሆነ መልስ በማጣቱ ፣ " በርታ እንግዲህ እ! ምን አንተማ ግማሽ ' ሴሚስተር ' ነች የቀረችህ ። ተገላገልክ " አለና ለመለያየት ጨበጠው ።

አቤል መርሳት የሚፈልገውን ፣ የሚሸሸውን ፣ የሚርቀውን የትምህርት አርዕስት ስላነሣበት ሰውዬውን ጠላው ። እስኪለያዩ ተቻኩሎ ነበር ። እንደ ፈራውም አልቀረ ። የትምህርቱን ጉዳይ አንሥቶ የገዛ ሕሊናው ይሞግተው ጀመር ።

“ መጨረስ አለብህ ፣ በትዕግሥት ይህችን ስድስት ወር መጨረስ አለብህ ፤ ደግሞም ትንሽ ነው የቀረህ ፤ ያልቃል ።”

‘ አይመስለኝም ! መጨረስ የምችል አይመስለኝም ። ቁም ነገሩ የጊዜው ወይም የኮርሱ ማነስና መብዛት አይደለም ። ትንሽም ነገር ቢሆን ጨራሽ ይፈልጋል ። በራሱ ኃይል አያልቅም ። ፋብሪካ ውስጥ ኤሌክትሪክ ከጠፋ ፣ ምርቱ ትንሽ ትልቅ ሳይል መቆም አለበት ። እኔም በትምህርት ረገድ የአእምሮዬ ኤሌክትሪክ ጠፍቷል ።’

‘ አትቀልድ እባክህ ፣ በራስህ አትቀልድ ። ለማይረባ ጊዜያዊ ስሜትህ ተንበርክከህ አንተንም ወላጆችህንም አትጉዳ ።’

‘አልቀለድኩም ። ለምን እቀልዳለሁ ? ከቶውንም በሕይወትና በፍቅር ቀልድ የለም ። ወላጆችም የራሳቸው ጉዳይ ነው ።’

‘ የራሳቸው ጉዳይ አይደለም ። የአንተም ጉዳይ ነው ። እነሱ በደሃ አቅማቸው ለፍተው ፣ ጥረውና ግረው ፣ እዚህ አድርሰውሃል ። አሁን ሽምግለዋል ። የአንተኑ እጅ ጠባቂዎች ናቸው ። አስብ ፣ ካላንተ ማን አላቸው?’

‘ እንጃ! አላውቅም ! እንጃ ! እንጃ ! እንጃ ! እንጃ !’

“ የማያውቅ ፣ የማያስብ ፣ አንጥሮ የሚመልስ ድንጋይ ብቻ ነው ። ከሙሉ አእምሮ ጋር የተፈጠረ ሰው ‘ እንጃ ’ ማለት አይችልም ።”

‘ እንጃ አላውቅም ! እንጃ ! እሷ ትጠየቅ ! እሷ እሷ !’

‘ ማነች እሷ ? !’

‘ ጠይሟ አጭሯ ልጅ ፣ ስትሥቅ ጉንጮቿ የሚሠረጎዱት ። ትዕግሥት . . . ትዕግሥት . . . ትዕግሥት . . .’

‘ ትዕግሥት ስላንተ ምን አገባት ? ልታስብለት ፣ ልትጨነቅለት ፣ ልታስታምመው የሚገባት እሷም የራሷ ሕይወት አላት ። እና ስላንተ ....’

“ እንዴት አያገባትም ? እንዴት? ! ይሄ ሁሉ ችግር በማን ተፈጠረና ? እኮ እንዴት አያገባትም ? ! . . .”



# ምዕራፍ ሰባት

ዕድምተኞቹ ከወዲያ ወዲህ ይራወጣሉ ፤ ሽር ጉድ ይላሉ ። ዘመድ አዝማድ የቤት ልብሱን ለብሶ ውጭ ውጭውን ያያል ። ከበሮው ከምሽቱ ጀምሮ አልቆመም ። ሌሊቱን አድርበት ፣ ቀኑንም ውሎበታል ። አውራጆቹ ፣ ግጥም ደርዳሪዎቹ ድምፃቸው ቢደክምም ፣ ቢጎረናም አላቋረጡም ። የሙሽራ ቤት ደንብ ነው ። ሙሽሪት ቤቱን ለቃ እስክትሔድ ወይም እስክትወሰድ ድረስ መድመቅ አለበት ። ከዚያ በኋላ ጭር ይላል ። ዘመድ አዝማድ ብቻ ቀርቶ የተሰበረ ብርጭቆ ይቆጥራል ፤ ወጪና ገቢውን ያሰላል ። ክምር ትራፊ እንጀራ ከሰሃን ሰሃን ያገላብጣል ። ቀኑ የትርምስና የደማቅ ትርኢት መድረክ ሆኖ ነው የዋለው ። ድንኳኑ አፉን ከፍቶ ሲያዛጋ ያድራል — ውሾች ያንዣብቡበታል ። ለሙሽሪትና ለሙሽራ ብቻ ተነጥፎ የዋለው የሥጋጃ ምንጣፍ የልጆች መቦረቂያ ይሆናል ። እስከዚያው ግን ከበሮው እየተደለቀ ነው ፤ እንግዶቹ እየተንቻቹ ናቸው ።

“ ምን ዐይነቱ ባለጌ ነው ?” አለች ማርታ ፣ ሙሽራውን በመተቸት ዐይነት ። “ ዘጠኝ ሰዓት ሊሞላ’ ኮ ነው ። እንዴት እስካሁን አይመጣም? ! ” ዘመድም ባትሆን የሙሽሪት ጓደኛ በመሆኗ ተቆርቁራለች ።

“እሷ ትሆናለቻ ያገባችው ! የዘንድሮ ‘ ባል ’ ኮ ችግር ነው ” አለች ቤተ ልሔም ፣ የሙሽራውን መዘግየት በኩራትና ንቀት ተርጉማው ።

“ እንዴት እባክሽ ? ” አለች ማርታ በመቆርቆር ዐይነት ። “ ለዘንድሮ ወንድ ? ይልቅ እንዲህ እያላችሁ የልብ ልብ አትስጡአቸው ። ”

ቤተልሔም ዝም አለች ።

“ ሆሆ ! እንግዶቹ’ ኮ አንቃቃቸው ” አለችና ማርታ በንዴት ራሷን ነቀነቀች ። ሙሽራው ገና ስላልመጣ ፣ ለእንግዶቹ መጠጥ እንጂ ምግብ አልቀረበም ነበር ።

ትዕግሥትን ይህ ሁሉ አላስጨነቃትም፡፡ከነቤተ ልሔም ጋር ወደ አምስት ሰዓት አካባቢ ፣ ወጥ ሠሪዎች ቁርስ ስለ ቀማመሱ ብዙም አልራባትም ፡፡ ሁለቱ ጓደኞቿ ለሙሽሪት ባላቸው ቅርበት የተነማ እንዴ ጓዳ ፣ እንዴ ድንኳን ፣ ሽር ጉድ እያሉ እሷን ብቸኛ ስላደረጓት ፣ ጥላቸው ወደ ዘፈኑ ከተቀላቀለች ቆይታለች ፡፡ የሠርጉ ዘፈን ደስ ብሏታል ፡፡ እንዴ በሐሳብ መርከብ እያንሳፈፈ ወደ ኋላ መልሶ የደብረዘይትን ሙሽሮች ያስቆጥራታል ፡፡ እንዴ ደግሞ የራሷን የወደፊት የቀን ሕልም እያሳለመ ያስቦርቃታል ፡፡ በተለይ ዜማ የሚያወርዱት ጠና ያሉ ሴትዮ ፣ ሁኔታቸው አስገርሞአት ትክ ብላ ታያቸዋለች ፡፡ ሁሉም ከወዲያ ወዲህ "እትዬ ሙቀጫ" ይላቸዋል ፡፡ አጭር ሆነው ደርፎጭ ስላሉ ነው መሰል-ይህ ስም የወጣላቸው ፡፡ በዘፈኑ ቦታ ኮከብ ናቸው ፤ ከበሮውንም ሲይዙት ፣ ዜማውንም ሲያወርዱት ይደምቅላቸዋል ፡፡ እሳቸው ሲያወርዱ እጁን ሰብስቦ የሚቀመጥ ካዩ የፈረደበት ነው ፡፡ ሁሉም ባለ በሌለ ኃይሉ ያጨበጭባል ፡፡

በዚህ ሁሉ ትርኢት መሐል ፣ የከበሮውን ድምፅ አሸንፎ ፣ የአውራጆቹን ዜማ ውጦ ፣ ዕድምተኞቹን በረጋግጾ ፣ በር ላይ የቆመውን የጥሪ ወረቀት ተመልካች ዘብ ጥሶ ፣ አቤል በትዕግሥት ሐሳብ ውስጥ ከተፍ አለ ፡፡

ዐይኗን በዘዝ እንዳረገች ፣ ከሠርጉ ቦታ ወደ ካምፓስ ተጓዘች . . . ከጓደኞቿ ጋር ተቀምጣ የምታጠናበት ዋርካ ፣ ለምለሙ ሣር በሐሳቧ ታያት ፡፡ የአቤል ዐይን ፍቅር በየሔደችበት ሲነግባት — በመኝታ ክፍል ፣ በምግብ አዳራሽ — አቤል . . . አቤል ፣ አቤል ! በተለይ ማርታ ፡፡ ማርታ ያለሱ ወሬ የላትም ፡፡ "እኔ እሱን ብሆን ኖሮ ፣ እንደሱ ጭንቅላት ቢኖረኝ ፣ ሜዲሲን ወይም ኢንጂነሪንግ ነበር የማጠናው" ያለቻት ትዝ አላት ፡፡ ማርታ ግን ለምን እንዲህ አለች ፡፡ አቤልን ሁልጊዜ ማድነቅ ለምን ደስ ይላታል ? በልቧ'ኮ ሳትወደው አትቀርም . . . ትንሽ ትንሽም ቢሆን ሳይናፍቃት አይቀርም ፡፡ አለዚያ ለምን ደጋግማ ታነሣዋለች ? ይገርማል ! እንዲያው ነገሩን አልኩ እንጂ ፣ የሰው ሁናቴ ገርሞኝ ነው እንጂ ፣ እኔማ ምን ጨነቀኝ ? ታዲያ አቤል ማርታን አይወዳትም ፡፡ ራሷው ናት ደሞ አይወደኝም እምትለው ፡፡ መቼም እርግጠኛ ነኝ ፣ አፍ አውጥቶ አልወድሽም አላላትም ፡፡ እሱ



ለራሱ መቼ ይናገርና ! እንዳይናገር የማለው ገና ሾንጣውን ይዞ እዚህ ግቢ ሲመጣ ነው ፡፡ ደሞ ማርታ የባጡን የቆጡን ስትለፈልፍ የሌሎቹ ማጋነን ፣ የሌሎቹ አብሮ ከበሮ መደለቅ ምን ይባላል ? . . . "ጥሩ ጭንቅላት አለው . . . ሌክቸረሮቹን ቻሌንጅ ያደርጋል . . . ከአራት ጂ.ፒ.ኤ. ስለወረደ ሊሰቀል ነበር . . ." ቅብጥርሴ ፡፡ ይሰቀላ ከፈለገ ! አለሱ ጎበዝ ተማሪ የለም እንዴ ? ! ደሞስ በቀደም ዕለት ፣ አዜብና አስገዶች ፣ ማርታ ስታወራላቸው ግማሽ ሰዓት ሙሉ አፋቸውን ከፍተው ከማዳመጥ ይልቅ ፣ አሳይሜንታቸውን አይሠሩም ነበር ? አስገዶች የማስረከቢያውን ቀን አሳልፋ ጋሼ ኤርምያስ አልቀበልም አላት ፡፡ እሱ ለራሱ ሴሪየስ ነው ፡፡ አዜብ ግን ተስፋ የላትም ፡፡ ከአባት ጦሮች ጋር ፀሐይ እየሞቀች ማን ያውራላት ? ! ማርታስ ብትሆን መቼ ከነሱ ትሻላለች?እሷ እምታውቀው አቤልን ማድነቅ ብቻ ! ጎበዝ ተማሪ ማድነቅ-ጎበዝ የሚያደርግ ይመስል ፡፡ አፍ ኮርስ ብሩሌያንት ነው ፡፡ እሱ የታወቀ ነው . . . ግን ነገሩን ሲያስቡት ደሞ ፣ "አቤል ብሎ ሲኒየር ፣ የመጽሐፍ ብሪሊያንት ! አቤል ብሎ ወጣት ! ስሙ ራሱ ደስ አይልም ! ! . . ."

ትዕግሥት ወደሚዘፍኑት ሴቶች ተመለከተች ፡፡ በሆዷ ለራሷ እምታወራውን የሰማች ይመስል-ግራና ቀኝ ወዳሉት ሰዎች አማተረች ፡፡ አንዳንዶቹ ወዲያ ወዲህ ይሯሯጣሉ ፡፡ አንዳንዶቹ እያጨበጨቡ ዘፈኑን ከሩቅ ያደምቃሉ ፡፡ ዐልፎ ዐልፎ እጅዋን ለከፍ ማድረጓ ባይዘነጋትም፣እንማርታን ስታይ በውጉ ማጨብጨብ ጀመረች ፡፡ ቤተ ልሔምና ማርታ ጥቂት ቆይተው ከሁለት ወንዶች ጋር ፈጠን ፈጠን እያሉ ሲያልፉ አየቻቸው ፡፡ ወደሷ ቀረብ ሲሉ ፣ ከማርታ ጋር እሚያወራው ቀጠን ያለ ወጣት ላይ ዐይኗ ዐረፈ ፡፡ 'ማርታ ከሰው ጋር የመግባባት ችሎታ አላት ፣ በተለይ ከወንዶች ጋር' ስትል አሰበች ፡፡ ማርታ ፣ "ወንድ ደስ እሚለኝ ቀጠን ሲል ነው" እያለች ብዙ ጊዜ እምትናገረው ነገር በሐሳብዋ እየደጋገመ ተሰማት ፡፡ ወዲያው በድንገት አቤል ከፊቷ ላይ ድቅን አለባት ፡፡ መልኩ መስሎ በምናቧ መንቀሳቀስ ጀመረ ፡፡ አቤል ጠይም ነው — ቀጠን ዘለግ ያለ ፡፡ ከሲታ ሳይሆን ፣ ሁሌ እሚለብሰው ጃኬቱ ጠባቃ ባያደርገው ፣ በአቋቋሙ ሚዛኑን የጠበቀ ነው ፡፡ አረማመዱ ኮራ ያለ ዐይነት ነው—እሷን ሲያይ

መርገጫውን እማያውቅ ከመምሰሉ በስተቀር ። አቤል ዐይኖቹ ተለቅ ተለቅ ያሉ ናቸው ። ስልካካ አፍንጫው የተመጠነ አወራረድና ለግንባሩ ገጥታ ተስማሚ አቀማመጥ አለው ። ዞማ ጠጉሩ በደንብ ተበጥሮ እሚያውቅ አይመስልም ። ይሁን እንጂ ፥ ለራስ ቅሉ እንደ ቆብ በልክ እንደ ተሰፋ ሁሴ ክርክም ያለ ዐይነት ሆኖ ድምቀቱ ከጥቁር ከፋይ ይወዳደራል ። እስካሁን ጥርሶቹን በደንብ ለማየት አልቻለችም ። አቤል መች ይሥቃል ? ! እንዳይሥቅ ተገዝቶ ነው ካምፓስ የመጣው ። እንዳውም አራት ዓመት ሙሉ በጭራሽ ሥቆ አያውቅም ። ጨፍጋጋ !ጨፍጋጋ ፊት ! እስቲ ምን ይባላል ፥ በጨፍጋጋ ሰው መታማት ? ! ቢሆንም ግን ፥ ላመል ፈገግ ሲል በጨረፍታ አይታዋለች- አንድ ቀን ፥ ከእስክንድር ጋር ቆሞ ሲያወራ ። ከዛም በፊት ሳታየው አትቀርም ፥ ማስታወሱ ይቸግራል እንጂ ። ስንቱ ነገር ይታወሳል ? አቤል ዝርዝር ያሉ ናቸው ጥርሶቹ — በጠይም ፊቱ ላይ እንደ ወተት ነጭ መሆናቸው ነው ዐይን እሚስበው ። ድምፁ ግን ምን ዐይነት ነው የአቤል ? መቼም በዚህ ጥርስ አቀማመጥ በትንሿ ኮልተፍ ቢል ሳያምርበት አይቀርም ! ግን በየት በኩል ? እሱ ለራሱ ዲዳ ነው — አይናገር አይጋገር ። ይቺ ማርታ ግን ዋና ናት — ጥርሰ ፍንጭት ነው እያለች ማውራቷ ። ቀድሞ ነገር የት ታውቀውና ያው እንደኔ ነው ከሩቅ የምታየው . . .

ትዕግሥት ይሄን ስታስብ ቆይታ ፥ ‘ እስቲ በደንብ እየዋለሁ ’ አለች በልቧ ። ግን ደሞ ወዲያው ፥ እስክስታው ላይ ተተክሎ የነበረው ዐይኗ ቦዘዝ ብሎ ወደ ካምፓስ አዘገመ ።

‘ ለምንድነው ጠዋት እንደዚያ የተቆጣው ? ’ ስትል አሰበች ። አቤል ከደረጃ ወርዶ ፊት ለፊት በተገጣጠሙበት ሰዓት ፥ ከፊቱ ላይ ያየችው ቁጣ እንደ ገና ታያት ። የሱ መቆጣት ብቻ ሳይሆን ፥ የራሷም መሸማቀቅ ነበር ያስገረማት ። ንግግር የለ ! ሰላምታ መለዋወጥ የለ ! ተቀራርቦ መጫዋወት



የለ — እንዲያውም እንደ ዲዳ ፥ እንደ ደንቆሮ በዐይን ብቻ መግናኘት ምንድነው ?

ዕንቆቅልሽ ሆነባት ። ዓይኗን ከድንኳኑ አሻግራ ወደ ማዶ ወረወረችው ፤እጅዋ ቀስ ቀስ እያለ ማጨብጨቡን አቋረጠ ። ትምህርቷን መከታ አድርጋ ልትሸሽ የምትታገለው የዐይን ፍቅር እንደ ውሃ ጠብታ ቀስ ቀስ እያራሳት መሆኑ ተሰማት — መጨረሻዉ ናፍቋት ።

‘ እሺ እንግዲህ ፥ መቼ ነው ታዲያ አፍ አውጥቶ የሚያናግረኝ ወይም አፍ አውጥቼ የማናግረው?’ ስትል ማሰቧን ቀጠለች ። ‘ ዛሬ ያናግረኛል ’’ ብላ ያሰበችበት የአንድ ቀን ጥሩ አጋጣሚ ታወሳት ።

የትምህርት ቀን ነበር ። ነገር ግን ፥ ቀትር ሰዓት ላይ ስለሆነ የሚንቀሳቀስ ሰው አልነበረም ። አብዛኛው ምሳውን በልቶ በየክፍሉ ጋደም ብሎአል ። ጥቂቱ መጻሕፍት ቤት ገብቶ ያንኑ መጽሐፍ የሙጥኝ ብሏል ። ትዕግሥትን ከዶብሬ ዘይት የመጣ ዘመድ አስጠርቶአት ወደ ውጭው በር ስትሔድ ፥ አቤል ቡና ጠጥቶ ከውጭ ሲመጣ ተገጣጠሙ ። እሷ ፈጥና ነበር የምትራመደው ። እሱም እሷን ባየ ጊዜ ፥ እጆቹን ከኪሱ አውጥቶ ፈጠን አለ ። የተገጣጠሙበት መንገድ ወደ ግራም ወደ ቀኝም መታጠፊያ አልነበረውም ። ሊቀራረቡ ጥቂት እርምጃ ሲቀራቸው የሁለቱም ልብ ትርታ ጨመረ ። ትዕግሥት ወደ ግራዋ ሰረቅ አርጋ አየችው ። እሱ መሬት መሬቱን ነው የሚያየው ። አጠገቡ ስትደርስ ገልመጥ አረገችው ፤ ግልምጫዋ ለክፋት ያለችው አልነበረም ። ምናልባት አቤል ለሰላምታ ጭንቅላቱን ሰብሮላት ፥ ፈገግ ብሎላት ወይም በግንባሩ ምልክት ሰጥቷት እንደሆን አጠፌታውን ልትመልስለት ነበር ። አቤል ግን አጠገቧ ሲደርስ በልቡ እንዳልከጀላት ፥ ፈጽሞ እንዳልፈለጋት ፥ ጭራሽ እንደማያውቃት ዐይነት አንገቱን ደፍቶ ፥ ግንባሩን አኮማትሮ ቅርቅር አድርጎአት ዐለፈ ።

ሁኔታው ትዕግሥትን ረበሻት ። በተለይ ችግሩን አስልታ ከትምህርቱ ጋር በተመለከተችው ጊዜ ዓይኗ እንባ አቀረረ ። “ እንቅፋት ነው — እንቅፋት!” ስትል ለራሷ ተነፈሰች ። ከዚያ ቀን በኋላ ከአቤል ዐይን ለመሸሽ ሞከ

ረች ። ግን ለማንም አላማከረችም ። በዕለቱ ከደብረ ዘይት ድረስ የመጣውን ዘመዷን እንኳ ፤ በቅጡ ሳታጫውተው ነበር የተለየችው .....

“ ታዲያ ከዚያ ቀን የበለጠ አጋጣሚ ከየት ይገኛል ? ” ብላ በሐሳብ ስትወራጭ የድንኳኑ ግርግር አባነናት ።

ከውጭ ተከታታይ የመኪና ጥሩንባ ስለ ተሰማ ፤ በድንኳኑ የተሰበሰበው ተጋባዥ ሁሉ ሙሽራውን ለማየት የመቻቻል ስሜት ይታይበታል ። የቤቱ ዘመድ ሽር ጉድ ማለትና መንቻቻት ግሏል ።

ማርታ ወደ ዘፋኞቹ ስትንደረደር መጥታ የትዬ ሙቀጫን ትከሻ ነካ ነካ አረገችና ፡ “ እትዬ ሙቀጫ ፤ ከበሮውን ይዛችሁ ውጡ እንጂ ! ሙሽራው እኮ መጥቷል ። ቶሎ በሉ እንጂ! ” አለቻቸው ።

ዘፋኞቹ ወደ በሩ ግልብጥ ብለው ሔደው ከበሮውን ሞቅ አድርገው እየመቱ ይዘፍኑ ጀመር ።

“ እናስገባም በሩን ፤ ሰርገኛውን
በሩን . . .
ሰርገኛውን . . . .
እናስገባም ሠርገኛ — እደጅ ይቶኛ
ሰርገኛ — እደጅ ይቶኛ . . . ”

ማርታ ደስ አላት ። በሙሽራው ላይ እልሏን እንደ ተወጣች ሁሉ ፤ ብሽቀቷ በርዶላት ፤ ፊቷ ፈክቶ ፤ ዳር ሆና ታጨበጭብ ጀመር ።

ሙሽራው ገብቶ ብፌ በሚዘረፍበት ሰዓት ቤተ ልሔም አንድ ሰው አየች ። ለማ ካብት ይመር ነበር ። ከግርግሩ መሐል ለይታ እንድታየው ያስቻላት ፤ ጸጉር ሸሽቶት የተጋለጠው ግንባሩ ነው ። ልክ እንዳየችው በደስታ ደነገጠች ። ብፌውን ዘርፎ ወደ ቦታው ሔዶ እስኪቀመጥ ድረስ በዐይኗ ተከተለችው ። በሙሽሮቹ መደዳ ትንሽ ራቅ ብሎ ነበር የተቀመጠው ።

‘ አጃቢ ይሆን?’ ስትል አሰበች ፤ ‘ እንዲያማ ቢሆን መታደል ነበር ’ አለች ፤ የግንኙነት ጊዜው እንደሚረዝም በመገመት ።



ብዙም ሳትቆይ እሱ በተቀመጠበት አካባቢ ዐለፈች ። እንዲያያት ፈልጋ ነበር ። እሱ ግን ምግቡ ላይ አቀርቅሮ ስለ ነበረ ቀና ብሎ አላያትም ። እንዴት ሰላም እንደምትለው ግራ ገብቷታል ። የቀድሞ ግንኙነታቸው ያው የአስተማሪና የተማሪ ስለሆን ፤ ከአንገት ሰላምታ አላለፈም ። ስለሆነም አሁን ፊት ለፊት ሔዳ ሰላምታ መስጠት አልደፈረችም ።

“ ብሉ እስቲ ፡ ምን ጎደለ ? ” አለች ፡ በሱ መደዳ ላሉት ሰዎች ፤ ድምጿን ከፍ አድርጋ ።

ለማ ቀና ሲል አያት ። ተማሪው መሆኗን ለያት ። እሷም በዝግታ ዐይኗን ቀልሳ አየችውና ሰላም የማለት ያህል ፤ ፈገግ ብላ አንገቷን ሰበር አደረገች ። ምላሹን ሰጣትና የሚጠጣውን ነገር ከጠርሙሱ ወደ ብርጭቆው ማንደቅደቅ ጀመረ ።

ቤተ ልሔም በልቧ እንደ መብሸቅ አለች ። የሰላምታው ምላሽ የጠበቀችውን ያህል ሞቅታ አልነበረውም ።

ድርቅ ብላ ከፊቱ ቆመችና ፤ “ ምን ጎደለ ታዲያ? ምን ላምጣ ? ” አለችው ፤ ከአስተናጋጅነት ይልቅ ቅርብነት በጎላበት ጣፋጭ አነጋገር ። በጎልማሳነት ክልል ውስጥ ቢሆንም ፤ ከዚህ በፊት ቀርባ አነጋግራው ስለማታውቅ ፤ አንተ ወይም አንቱ ለማለት ቸግሮአታል ። ነገር ግን ለማጥመድ ያሰበችውን ሰው አንተ ማለት የሚያስከትለውን ውጤት ታውቃለች ። ኋላ አባትና ልጅ ወይም ወንድምና እኅት ሆኖ ቁጭ ነው ። እናም ደፍራ አንተ ለማለት ወሰነች ።

“ ሁሉም አለ ። ግሩም ነው ” አላት ለማ ።

“ እውነቴን ነው ፤ የምትመርጠውን ነገር ላምጣልህ ” አለችው ፤ በዐይኗ ከሰሐኑ ላይ የተቀመጠውን የምግብ ዐይነት እየፈለገች ። “ ጭኮዋን ወደሃታል አይደል?! እሷን ላምጣልህ” አለችውና ከእሱ መልስ ሳትጠብቅ ልታመጣለት ሔደች ።

ለማ የዶሮ ወጡን እንቁላል እየፈረከሰ ቤተ ልሔምን ከኋላዋ ቃኛት ።

ሰፋ ያለ ጃፖኒ ቀሚስ ነበር የለበሰችው ። ውፍረቷ ያንኑ መጠነኛ ቁመቷን ቢውጥባትም ለጊዜው በረኸኛ ታከ

ሜማ ተንሥታለች ። ስትራመድ ዳሌዋ ግራ ቀኝ ይረግጣል ። የሚዛኗ አጠባበቅ ብዙ ልምምድ እንደ ተደረገበት ያስታውቃል ።

ቤተ ልሔም የጭኮውን ሰሐን ብፌው ከተዘረጋበት ጠረጴዛ ላይ ስታነሣ ማርታ ተመለከተቻት ። እንደ ደንቡ ከሆነ ለድጋሚ ዙር የምግቡ ዐይነት ከተዘረጋበት ጠረጴዛ ተነሥቶ በየገበታው የሚዞረው ተጋባዡ ሁሉ ብፌ ዘርፎ ከጨረሰ በኋላ ነው ። ቤተ ልሔም የጭኮውን ሰሐን ስታነሣ ግን ገና ብፌ ዘረፋው አልተጠናቀቀም ። ስለዚህም ማርታ ልቧ የሆነ ነገር ጠርጥሮ በዐይኗ ተከተለቻት ፤ ጭኮውን ወስዳ ለማ ሰሐን ላይ ስትዘረግፍለት በቅናት ስሜት ተመለከተቻት ።

"ኧረ በቃ ! በቃ ! " አለ ለማ ፣ የምትጨልፍበት እጅዋን ለማስጣል በግራ እጁ ይዞ ።

" እሺ ፣ በል ያመጣሁልህን ብላ " አለችና ዐይኗን አስለምልማ አየችው ። ሳያስበው የእሽታ ፈገግታ ሰጣት ። ፈገግታው ካመለጠው በኋላ በቅልጥፍናዋ ተደነቀ ።

እሷም አይታዋን አልደገመችውም ። ተቀባይ ልብ ላለው ሰው የአንዴው በቂ እንደሆነ ታውቃለች ። በምላሽ ፈገግታውረክታ ፣ ነገሩን ለማድበስበስ ያህል በአቅራቢያው ላሉትም ሰዎች ፣ " ብሉ እንጂ " እያለች ከጭቆው ጨመረችላቸው ።

ለማ ጸጉር በከዳው ግንባሩ በኩል ላብ ሲንቸፈቸፍ ተሰማው ። ወንድነቱ " ዘራፍ " እያለ መጣበት ። ምግቡ ላይ እንዳቀረቀረ ቤተ ልሔምን በልቡ ተመለከታት ። ጉሮሮውን ምንም ነገር ሳይኮሰኩሰው ጣለ ። ለአፍታ ያህል ትንፋሹን አምቆ ቆየና በረዥሙ ተነፈሰ ። በድንገት የሚስተር ራህማን ምስል ከፊቱ ተደቀነበት ።

ሚስተር ራህማን ፣ ለለማ የሥራ ባልደረባው ናቸው ። እሱ ተመርቆ ዩኒቨርስቲ ማስተማር ከጀመረ ገና አራተኛ ዓመቱ ነው ። ሚስተር ራህማን ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ዩኒቨርስቲ ሲያስተምሩ ዘጠኝ ዓመት አላቸው ። ነገር ግን ስማቸው በዩኒቨርስቲው ውስጥ የዚያን ያህል ጠፍቷል ። በሴት ጉዳይ ተማሪው ብቻ ሳይሆን መምህራኑም ጭምር ያሚቸዋል ። የትም ይሁን የትም ዐይናቸው ከሴት ላይ አይነ



ቀልም ። ቆንጆ ልጅ ታክሲ ውስጥ ካጋጠመቻቸው ካልክ ፈልኩልሽ በማለት ብቻ አይመለሱም — " አይቲንክ አይ ኖው ዩ ሳምዊር " ብለው ወሬ መክፈት ልማዳቸው ነው ። የመኖሪያ ቤታቸውን አቅጣጫ እየዘረዘሩ ቀጠሮ መለዋወጥ ከጀመሩ ግን ፣ ከታክሲ ነጂው ጋር መጣላታቸው አይቀርም ። ሚስተር ራህማን በወሲብ ፍላጎታቸው ራሳቸውን መቆጣጠር አይችሉም ። ለምሳሌ ካምፓስ አካባቢ ከሴት ጋር ቆመው ሲያወሩ ቢታዩ ፣ ሠራተኛ ለመቅጠር እየተነጋገሩ ነው ማለት አይደለም ። ወይም አማርኛ እየተለማመዱ ነው ብሎ አሚያስብ ተሳስቷል ። ሚስተር ራህማን በዚያን ሰዓት ያጠኗቸውንም ያላጠኗቸውንም ውብት ማድነቂያ ቃላት አንድ ባንድ እየቦረቦሩ በማዥጎድጎድ ላይ እንደሚሆኑ አይጠረጠርም ። እንዳውም በል ካላቸው የሴትዮዋን እጅ በጃቸው ጥርቅም አርገው እንደ ያዙ ፣ አደባባይ በመዞር ላይ ያለ የሞላ ታክሲ ወዲያውኑ ካላስቆምኩ ሲሉ ይችላሉ ።

የሚያወጧቸው ሴቶች እያወሩባቸውም ። " A " በእጃቸው እንደ ኀባች አረጋግጠው ድምፃቸውን አጥፍተው ቁጭ ነው ። ነገር ግን የራህማንን ጥያቄ የማይቀበሉ ጥቂት ጠንካራ ሴቶች ያጋጥማሉ ። እኒህኞቹ ለቅርብ ጓደኞቻቸው ፣ " አንቺዬ ይሄ ሽማግሌ ሕንድ'ኮ ላውጣሽ አለኝ! አያፍርም እንዴ በናትሽ ? ምን ቅሌታም ነው!" ሲሉ ይሰማል ። ወሬው እንዲህ እያለ ይራባል ። ወንዶች ይህን " ዕድል " ባይታደሉትም ፣ አንዳንዶቹ በአገናኝነት በማገልገል የበኩላቸውን ሚና ይጫወታሉ እየተባለ ይወራል . . .

" ከዚህ አድነኝ ! " በማለት ዐይነት ለማ ግንባሩን ቋጥሮ ራሱን ነቀነቀ ። ከራሱ ጋር ቅራኔ ውስጥ ገባ ።

ቤተ ልሔም የጭኮውን ሰሐን ከጠረጴዛው ላይ መልሳ ፣ እየተፍነከነከች ሙሽራዋ ስትለባብስ ወደ ቆየችበት ክፍል ሔደች ። ማርታም አይጥ እንዳየች ድመት በዐይኗ ስትከታተላት ቆይታ ፣ ወደ ገባችበት ክፍል ዘው ብላ ገባች ።

" ውይ ! ኮቴሽን ሳልሰማ ። እንዴት አስደነገጥሽኝ ! አለች ቤተ ልሔም በደስታ የሚሥቁ ዐይኖቿን ማርታ ላይ ተክላ ። በቁም ሳጥኑ መስታወት እያየች ጸጉሯን ስታስተካክል ነበር የደረሰችባት ።

" እሰ ነገር ! " አለች ማርታ ፣ ከፊል ቀልድ ከፊል ቅናት በተደባለቀበት ሞዛዛ አነጋገር ። " ከግብዣ መሐል እስነሥቶ ጸጉር የሚያስበጥር ። እሰ ነገር! እሰ ነገር ! "

" መች አጣሽው ማርትዬ ፣ እሰ እንጂ ጥብቅ ነገር ! ሠርግና ምላሽ መሐል ከመምህሬ ጋር ስገጣጠም " አለች ፣ ዜማ ቀረሽ በሆነ ድምፅ ።

" መምህርሽ ነው እንዴ?" ስትል ፣ በቁም ነገር ቃና ጠየቀቻት ።

"አይተሽዋል እንዴ ? " ስትል ፣ ቤተ ልሔም ጥያቄ ውን በጥያቄ መለሰች ።

" አይቼዋለሁ ። ያ ራሰ በራው ሰውዬ አይደለም? "

" ጸጉሩ የሸሸው በዘር ሊሆን ይችላል እንጂ ፣ እሱስ ገና ወጣት ነው "

" ማለቴ ፣ ምልክቱን ነው እንጂ ፣ ስለ ዕድሜው መግ ለጼ አይደለም ። "

" አዎ እሱ ነው ። ግን ከምኔው አየሽው ? አይ አንቺ ! " አለችና በምስጢር ዐይነት ድምጿን ዝቅ አድርጋ ፣ " አንድ ኮርስ ያስተምረኛል " አለቻት ።

" ታዲያ እንዴት ነው ? " አለች ማርታ ከንፈሯን ነከስ አድርጋ ።

" እንዴት ይመስልሻል ? " አለችና ቤተ ልሔም ፣ የግራ ጎን ዳሌዋን በመስታወቱ ውስጥ እየተመለከተች ፣ " ጠብ ነዋ ! " አለቻት ።

' ለማንኛውም ነገር ዕድልና አጋጣሚ ያስፈልጋል ' አለች ማርታ በልቧ ፣ ' አሁን ምናለበት ፈጣሪዬ አንዱን መምህሬን አምጥቶ እዚህ ሰርግ ላይ ቢጥልልኝ !'

ፊት ለፊት ቆማ ፣ በጎን በኩል ሆና ፣ ከኋላ በኩል አን ገቷን አዙራ ፣ ባለችበት ራመድ ራመድ እያለች ቤተ ልሔም ራቧን በመስታወት ውስጥ ተመለከተችና ፣ " ምን ይወጣል ኛል ! " በማለት ዐይነት በኩራት ፈገግ አለች ።



ውፍረቷ አያስጠላባትም ። በአለባበስ ትሸፍነዋለች ። የትኛው ልብስ ከየትኛው ጫማና ሹራብ ጋር እንደሚሔድ ጠንቅቃ ታውቀዋለች ። ሱሪ አታዘወትርም ። ከሰውነቷ ሁኔታ ጋር አዛምዳ ነው የምትለብሰው ። ጉንጮቿ የተላጠ ብርቱካን ነው የሚመስሉት ። ነገር ግን በምቾት አበጥ ስላሉ ጓደኞቿ " ለጉንጮችሽ የጡት መያዣ ያስፈልጋቸዋል " እያሉ ይቀልዱባታል ። ፎርሟን ለማስተካከልና ውፍረቷን ለመቀነስ አንዳንድ ሰሞን ቁርስ መብላት ትተዋለች ። ነገር ግን ምሳ ላይ ደርሳ ነው የምትበላው ። የዩኒቨርስቲው ምሳ አይስማማትም ። እንዲያው ነካ አድርጋ ነው የምትተወው ። ከዚያ በጓሮ በር የምትገባባቸው ቤቶች አሏት ። የሆድ ነገር ከሆነ የቅርብ ጓደኛዋንም አታስጠጋ ። ሹልክ ብላ ነው የም ትሔደው ።

" በቃሽ እንግዲህ ፣ ኤፍ! ደሞ ለአስተማሪ ይህን ያህል !" አለች ማርታ በመሰላቸት ዐይነት ።

ቤተ ልሔም በልቧ ፣ ' ባይሳካልሽ ነው ' አለችና ሽቶ ከቦርሳዋ አውጥታ ጡቶቿ መሐል አርከፈከፈች ። ከነጋ አራተኛ ጊዜዋ መሆኑ ነው ።

ተያይዘው ወደ ድንኳኑ ሲወጡ ፣ ቤተልሔም እንደ ልማዷ ወደ ሽንት ቤት ሔደች ። ማርታ ነገሩ ገባትና ሣቅ አለች ።

ከዚህ ሁሉ ትርኢት ርቃ ዘፈኑ አካባቢ የቆየችው ትዕ ግሥት ፣ ማርታን ፈልጋት መጣችና ፤

" አንቺ ማርታ ፣ እረ እንሔድ " አለቻት ።

" የት ? " አለች ማርታ ፣ ፈጽሞ የማይታሰብ ነገር እንደ ጠየቀቻት ሁሉ ተደናግጣ ።

" ወደ ካምፓስ ነዋ! ምን ማለትሽ ነው? " አለቻት ፣ የተከመረውን ጥናትና የተቃረበውን ፈተና በሚገልጽ ስሜት ግንባሯን ኩምትር ፣ ፊቷን ትክዝ አድርጋ ።

ትዕግሥት ሰርግ ቤት መቆየቱን አልጠላችም ። ብታ ድርም በወደደች ነበር ። ነገር ግን ሐሳቧ ተረጋግቶ መቀመጥ አልቻለችም ። እሷ ከዚህ ሙሽራ አጅባ ስታጨበጭብ ካም

ፓስ ውስጥ ተማሪው ጥናቱን ሲፈልጠው ፡ የታሪክ ትምህ
ርቱን ሲለበልብው ፤ የፍልስፍና ትምህርቱን ሲሰነጣጥቀው ፤
የሒሳብ ትምህርቱን ሲያላምጠው በሐሳቧ ቁልጭ ብሎ እየ
ታያት የመበለጥ ስሜት ተሰማት ። ከዚህ ሌላ ደግሞ አቤል
በምሳ ሰዓት ምግብ አዳራሽ ውስጥ በዐይኑ እንደሚፈልጋት
ታውቃለች - ከሄደችበት ተመልሳለች ወይስ አልተመለሰ
ችም በሚል የቅናት ስሜት ። እና ወደ ካምፓስ መመለሷን
እንዲያውቅ ራት ላይ እንኳን ልትታየው አሰበች ።

" እሺ ቆይ ፡ ለማንኛውም ሙሽራ ይውጣ " አለች
ማርታ ። " ከዚያ መኪናም አይጠፋ ፤ ካምፓስ ድረስ እንሸኝ
ሻለን ። "

ትዕግሥት እነሱ ወደ ካምፓስ እንደማይመለሱ ተረዳ
ችና ፡ " ኧረ ግድየለም ፡ እኔ በአውቶቡስ እሔዳለሁ "
አለቻት ።

" እሺ ! " አለች ማርታ ፡ ትዕግሥት የተናገረችውን
ሳትሰማ ። ሐሳቧ ዐይኗን ተከትሎ ለማ ወደ ተቀመጠበት
ሔዶ ነበር ።

ለማ ሊተወሰኑ ደቂቃዎች ቤተ ልሔም ከዐይኑ ጠፍታ
በት አዳራሹን ግራ ቀኝ ሲማትር ፡ ድንገት ከጀርባው በኩል
ከተፍ አለችበት ።

" ብሉ እስቲ ። ምን ጎደለ ? እዚህ አካባቢ ጠፋሁባችሁ
አይደል ? " አለች ገና ከመድረስዋ ፡ በሌላ መደዳ ስታሳልፍ
የቆየች ለማስመሰል ።

አብዛኛዎቹ መብላት አብቅተው ወደ መጠጡ አዘን
ብለው ነበር ። የተደጋገመው መስተንግዶ አስደንቆአቸው ፤
እሷን በሙሉ ዐይናቸው ፡ እሱን ደግሞ በስርቆት ተመልክ
ተው ፡ ግብዣዋን በማመስገን ዐይነት እጅ ነሡ ።

የቤተ ልሔም ሙዚቃ መሳይ ድምፅ ጆሮውን ብቻ ሳይ
ሆን ልቡን ጭምር ቢነካውም ፡ ለማ ወደ ኋላው ዞር ብሎ
አልተመለከታትም ። መኩራቱ ሳይሆን መቆጠብ ነበር ።

ብርጭቆውን እንዳጎደለ ተመለከተችና እጅዋን በማጅ
ራቱ በኩል አሳልፋ ከጠርሙሱ እየቀዳችለት ፡

" በጀርባህ በኩል በመቅዳቴ ይቅርታ ! " አለችው ።



ምላስ እንደ ሌለው ሁሉ " ምንም አይደለም " በማ
ለት ዐይነት ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። ደረቷ ለአፍንጫው በጣም
ስለ ቀረበ የሽቶዋ መዓዛ ክፉኛ አወደው ። አሁምን ወን
ድነቱ የሽቶውን መዓዛ እያማገ ከእሱነቱ ውስጥ " ዘራፍ ! "
ሲል ተሰማው ።

" ምናባቷ ትፈታተነኛለች ! " አለ በልቡ ።

ብርጭቆው ቶሎ እንዳይሞላ ቀስ ብላ እየቀዳች ፡ " ትቆ
ያለህ ወይስ ትሔዳለህ ? " ስትል ሹክ አለችው ። ልቡ ክፉኛ
ነጠረበት ። ለእሷ መልስ በመስጠት ፈንታ ቀስ ብሎ አጠ
ገቡ የተቀመጡትን ሰዎች ማተረ ። እሷ ድምፅዋን ዝቅ አድ
ርጋና ፈጥና ሌሎች እንዳይሰሙ አድርጋ ነበር የጠየቀችው ።
እሱ ቀና ሲል ከፊት ለፊቱ የተቀመጡት ሁለት ሴቶች አቀ
ርቅረው ሲንሾካሾኩ ተመለከተ ።

' ምኗ ይሆን ? እንዴት ብትወደው ነው ? እያሉ ይሆ
ናል የሚንሾካሾኩት ' ሲል አሰበ ። እጁ ሳይታዘዝ በራው
ላይ ያቻፈቻፈውን ላብ ጠረገለት — ሲያሳጣው ።

" ማለቴ " አለችው ቤተ ልሔም ፡ መልሱ ስለ ቆየባት ፡
ጥያቄዋ ያደናገረው መስሏት ። " ማለቴ ፡ እጃቢ ሆነህ ነው
የመጣኸው ወይስ ተጋብዘህ ? "

" ኧረ ተጋብዤ ነው " አላት ።

" ቶሎ ሕያጅ ነሃ ? " ብላ መጠጡን ቀድታለት ጨርሳ
ቀና ስትል ፡ ፊቷ ዕዝን ብሎ ነበር ። በዚያች ቅጽበት ዐይኗ
ውስጥ የሆነ ነገር አንብቦ ' በርታ ልቤ ! ' እያለ ፡ ግን ' ምን
ዐይነት ዐይን ነው ያላት ! ' ሲል ተደነቀ ።

ቤተ ልሔም በቆመችበት ተቁነጠነጠች ። ፊቷ ተለዋ
ወጠ ። ለማ ቶሎ የሚሔድ ከሆነ የተጀመረው ነገር አሁኑኑ
ማለቅ አለበት ። ከአስተማሪነቱና ከተማሪነቱ ውጭ የሚገ
ናኙበትን ቀጠሮ ማበጀት አለባቸው ። ቤተ ልሔም ነገሩን
በይደር መተው አልፈለገችም ። ምናልባት ፡ ይህ አሁን
በለማ ውስጥ ያበበው የስሜት ተስፋ ፡ ነገ ዩኒቨርስቲ ውስጥ
ሐሜትን ፈርቶ ፡ ቁጥብነትን ፈልጎ ወይም በሌላ ምክንያት
ሊጠወልግ ይችላል ። ይህ ከሆነ ደግሞ ወጥመዷ መክሸፉ
ነው ። እና አሁኑኑ በአስቸኳይ ፡ ልቡ ሳያጋድል ፡ የስሜት

እሳቱ ሳይበርድ ቀጠሮ ከአፉ ከወጣች ለመቼም ቢሆን ግድ የለም ። ቃሉን አጥፎ ወደ ኋላ እንደማይል ታውቃለች ። ካወሩት እንዳደረጉት ይቆጠራል ፣ ነገሩ !

እንደ ደስታዋና እንደ ድንጋጤዋ ጊዜ ሁሉ ፣ አሁንም ለጉዳዩ አስቸኳይ መፍትሔ ለመስጠት ስሜቷ ስለ ተቁነጠነጠ ፣ ሽንቷ የመጣባት ፣ ውጥር አርጎ የያዛት መሰላትና እግሯን አኮራምታ ቆመች ።

የለማ ልብ ዐርፎ አልተቀመጠም ነበር — ይንፈራገጣል ። ከጥያቄዋና ከገጽታዋ ስሜቷን በሚገባ ተረድቷል ። አንዳች ሰይጣናዊ ስሜት ልቡን ገፋፋለትና እጅዋን ጎተት አርጎ ፣ ዝቅ ባለ ድምፅ ፣

" ልሔድ ስል አነጋገርሻለሁ " አላት ።

" እ ? " — ሳትሰማው ቀርታ ሳይሆን ፣ ጆሮዋን ማመን አቅቷት ነበር ።

አልደገመላትም ።

ቶሎ የከፋው ልቧ ቶሎ ተደሰተ ፤ እየተፍንከነከች ከሩጫ ባላነሰ እርምጃ ወደ ሽንት ቤት ሔደች ።

ጠረኗ ግን እዚያው ለማጋ ቀርቶ ነበር ። ወትዋች ጎሊናው ደረቱን ገልብጦ ፣ ቡጢ ጨብጦ ፣ ግንባሩን አኮማትሮ ፣ የቤት ልሔምን ጠረን ላለማሽተት አፍንጫውን ደፍኖ ፣ እሱነቱ ውስጥ ግትር ብሎ ቆሞ ተመለከተው ። ሁለት ለማዎች !

'ምንድን ነው ነውሩ ? መምህር የሚያስተምራትን ልጃገረድ ቢወድ ፤ ከሚወዳት ተማሪው ጋር ቢዳራ ፣ ምንድነው ነውሩ ?'

' መውደድማ ባልከፋ ነበር ። ነገር ግን የወደደ ችግር ነው ። እና ማርክ አሰጣጥ ላይ . . . ደሞም የወደደ ልብ ወዳጅ ሲወድቅ ዝም ብሎ አይመለከትም ። '

' እና ታዲያ? '

' እናማ ምርጫው ሁለት ነው ! '

' ኤጭ ! '



# ምዕራፍ ስምንት

በገለጻው አዳራሽ የተሰበሰቡት ተማሪዎች ከትከት ብለው ሣቁ ። አቤል ግን ሌክቸረሩ የተናገረውን ቀልድ ስላላዳመጠ ለመሣቅ ዕድል አላጋጠመውም ። በአዳራሹ ሣቅ ተኮርኩሮ ከሐሳቡ ከነቃ በኋላ ፣ አጠገቡ የነበረውን ተማሪ ስለ ሁኔታው እንዲያስረዳው ጠየቀው ።

" ምንድነው? " አለው ድንግርግር ባለ ስሜት ።

" አልሰማኸውም እንዴ ? " ብሎ ተማሪው ቀልዱን ሊነግረው ቢሞክርም ሣቁን መግታት አልቻለም ነበር ። አቤል ደግሞ የተማሪውን ሣቅ አስጨርሶ ቀልዱን ለማዳመጥ ትዕግሥት አልነበረውም ። በተሰላቸ ስሜት ችል ብሎ ተወው ።

ሰኞን አይወደውም ። " ብላክ መንዴይ " ይለዋል ። ቅዳሜና እሑድን መንፈሱንም ባይሆን አካሉን አሳርፎ ፣ ሰኞ ደብተሩን ይዞ ወደ ትምህርት ክፍል ሲገባ ፣ አንዳች የጥላቻ ስሜት ያድርበታል ። እንዲያው ለስሜቱ ይቅርታ ለመስጠት ያህል ቀናቱን በመውደድና ባለመውደድ ይከፋፍላቸዋል እንጂ ፣ ልቡ ውስጥ ለትዕግሥት ቦታ ከሰጣት ጊዜ ጀምሮ የመምህሮቹን ገለጻ በሙሉ ስሜት ያዳመጠበት ጊዜ የለም ። ሐሳቡ ውጭ እየከነፈበት አካሉ ብቻ ነበር - ክፍሉ ውስጥ የሚቀመጠው ።

ከሌሎቹ ሁሉ ይህን ክፍለ ጊዜ ይወደው ነበር ። የፍሎስፍና ተማሪዎቹ ሳይወስዱ ያለፉትን አንድ የሳይኮሎጂ ኮርስ ከሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ጋር የሚወስዱበት ክፍለ ጊዜ በመሆኑ ፣ ከትምህርቱ ይልቅ አዳራሹ ሞልቶ ማየቱ ያስደስተዋል ። ምክንያቱም ሌሎቹን ኮርሶች የሚወስደው ከስድስቱ ተማሪዎች ጋር ብቻ ነው ። በቁጥር ማነሳቸው ደግሞ መምህሩ የተማሪዎቹን ስሜትና ሁኔታ በቀላሉ እንዲከታተል ይረዳዋል ። በዚያ ላይ ጥያቄ መጠየቅ አለ ። አቤል

ይሆን ነው ያልወደደው ፤ አካሉን ክፍል ውስጥ አስቀምጦ በስሜቱ ወደ ውጭ የመብረሩን ነጻነት ያሳጣዋል ፤ በቀላሉ ይጋለጣል ።

ዛሬ ግን ስኖ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ሌላም ስሜቱን ያቁነ ጠነጠው ጉዳይ ነበር ። ትዕግሥትን ማየት አለበት ። የሁለት ቀን ናፍቆት ላለበት አፍቃሪ የአንድ ሰዓት ሌክቸር በጣም ረጅም ነው ። እናም ከክፍሉ ሮጦ ለመውጣት የደወሏን ድምፅ ነበር የሚጠባበቀው ።

" ምን መሰለህ ? " አለው አጠገቡ የተቀመጠው ተማሪ ጣቱን እንደ ጨረሰ ፥ የመምህሩን ቀልድ ለአቤል ለመ ንገር ጓጉቶ ፥ "ሃይማኖታዊ ቀልድ ነው'ኮ የተናገረው ። "

" እኮ ምን? " አለ አቤል ፥ በተሰላቸ ድምፅ ።

" ሰዎቹ ከሞቱ በኋላ ፥ ወደ ሰማይ ቤት ሔደው መንግ ስተ-ሰማያት ለመግባት ሽሚያ ተፈጠረ ። የገነት በታ ጠባብ ነበር ። ስለዚህ ጻድቃኖቹ ተወዳድረው ይግቡ ተባለና መመዘኛው በምድር ላይ ለደሃ የመጸወቱት ገንዘብ ብዛት ሆነ ። በዚህም መሠረት ለደሃ ብዙ የመጸወቱት ወደ ገነት ሲገቡ ፥ አምስት ሳንቲም ብቻ የመጸወተው ጻድቅ ግን አምስት ሳንቲሙ ተመልሶለት ወደ ገሀነም ይግባ ተባለ ።"

አቤል ቀልዱ ብዙም ስላልኮረኮረው ፥ ጥርሱን ትንሽ ብልጭ አድርጎ ፥ " ሰዓትህ ስንት ትላለች ? መውጫችን አልደረሰም እንዴ? " ሲል ጠየቀው ።

ተማሪው ሰዓቱን ተመልክቶ ፥ " ሁለት ደቂቃ ይቀራል " አለው ።

ሁለት ዓመት ይቀራል ያለው ይመስል-አቤል ፊቱን ኮሶ አስመስሎ በልቡ ሴኮንዶቹን ሲያባርር ቆየ ።

ልክ የደወሏን ድምፅ ሲሰማ ፥ አንዳች ነገር መቀመጫ ውን እንደ ወጋው ሁሉ ቶሎ ብድግ አለ ። ነገር ግን አልተቶ ኮረበትም ። ሌሎቹም ለመመገቢያ አዳራሹ ሰልፍ ለመሽቀ ዳደም ደውሉን ተከትለው ግልብጥ ብለው ስለ ተነሡ ፥ ክፍሉ ትርምሱ ወጣ ። ቀድሞ ለመውጣት በሩ ላይ ጭን ቅንቅ ተፈጠረ ።



' ምናለበት ቅድሚያ ቢሰጡኝ ? ! , አለ አቤል በልቡ ፥ ለመውጣት እየተጋፋ ፥ ' እነሱ የራባቸው ሆዳቸውን ነው ። የእኔው ግን የዐይን ረሀብ ነው ። '

' ታዲያ ከዐይን ረሀብና ከሆድ ረሀብ ለየትኛው ነው ቅድሚያ የሚሰጠው ? ' ሲል የገዛ ኅሊናው ያፋጠጠው መሰለው ።

' እንደ ረሀቡ ጥንካሬ መሰለኝ ። '

' አይደለም ። ጅል አትሁን ። ሆድህ ሳይጠግብ ዐይንህ አይራብም ። '

" እረ አይመስለኝም ። አያድርስ ነው ። የዐይን ረሀብ ራሱ ከሆድ ረሀብ ይብሳል ። አያድርስ ነው ! እረ እንዲያው መቃጠል ነው ! '

' ምነው የዐይንን ረሀብ እንዲህ አጋነንከው ? የማያው ቁት ዐይነ ሥውራን አሉ አይደለም እንዴ ? '

' ሀሀ ! እነሱም ' ኮ ጆሮአቸው የሚራብ ይመስለኛል ። ጆሮአቸው የዐይናቸውን ያህል ያገለግላቸዋል ። ለምሳሌ እኛ ዐይናማዎቹ የምንወዳትን ሴት በየጊዜው ለማየት እን ደምንራበው ሁሉ ፥ እነሱም የሚወዱትን ሴት ኮቴ ወይም ድምፅ ለመስማት ጆሮአቸው የሚራብ ይመስለኛል ። '

' ድንቅ የሆነ የመከላከያ ሐተታ ነው ። እስቲ እንግዲህ አንድ ሁለት ቀን ምግብ ሳትበላ ቆይና ፥ ከዐይንህና ከሆድህ የትኛው ቅድሚያ እንደሚኖረው ትረዳዋለህ ። '

አቤል ወትዋች ኅሊናውን " ወግድልኝ ! " ብሎ የማ ረር ያህል እጁን አወራጭቶ ፥ ' ሰው ኅሊናን ያህል ባላንጣ ባይኖረው ምንኛ እንደ ልቡ በሆነ ነበር ! ' ሲል አሰበ ።

' እንዴት እባክህ ? እንደ ከብት ? እንደ እንስሳ? ' እያለ ኅሊናው እንደ ገና ከተፍ ።

መንገዱን በምን ዐይነት ርምጃ እንደ ጨረሰው ለፊ ሱም እየገረመው ከመኝታ ክፍሉ ደረሰ ። ደብተሩን አልጋው ላይ ወረወረና በመጣበት ፍጥነት ተመልሶ ደረጃውን ወረደ ። በሩጫ-ቀረሽ ርምጃ ወደ ምግብ አዳራሽ አመራ ።

ከገለጻ ፍሉ ለመውጣት የነበረው ችኮላ ፣ ያ ሁሉ የዐይን ረሃብን የተመረኮዘ ግላዊ ሙግት ፣ ይህ ሁሉ ሩጫ ትዕግሥትን ለማየት ነው ። ትላንት ጠዋት ወደ ሰርጉ ከሔደችበት ጊዜ ጀምሮ አላያትም ። እሔደችበት አድራለች ብሎ ነው የገመተው ። እሷ ግን አውቶቡስ አጥታ አምሽታ ነበር እንጂ ካምፓስ ነው ያደረችው ። ጠዋት ደግሞ እሱ ራሱ እንቅልፍ ተጫጭኖት ስላረፈደ ፣ እንደ ወትሮው ወደ ቁርስ ክፍል ስትሔድ ወይም ወደ ትምህርት ክፍሏ ስትገባ ለማየት ዕድል አልገጠመውም ። በዚህ ምክንያት ገለጻ ክፍሉ ውስጥ ሁሉ ነገሩን እያብላላ ሲበሽቅ ነው ያረፈደው ።

አሁንም ከምግብ አዳራሹ አካባቢ ደርሶ የምሳ ሰልፍ እንደ ያዘ ፣ መላ ሰውነቱ በቅናትና በእልህ ነበልባል ይንቀለቀል ነበር ። ትዕግሥት ሰልፉ ውስጥ የለችም ። ቀድማ ገብታ ይሆን ? ሰልፍ መጠበቁ አስመረረው ። ወደ ውስጥ ለመግባት ቸኮለ ። ነገር ግን ተራ መጠበቅ ግዴታ ነው ። በውዴታ — ግዴታ የተሳሰረች ዓለም !

ተራው ደርሶ ውስጥ ከገባ በኋላ ፣ እንጀራ ሳይቀበል ወጥ ጨላፊው ጋ ሔዶ ትሪውን ዘረጋለት ። መሳሳቱን ያወቀው ሲሥቅበት ነው ። ድርሻውን ተቀብሎ መቀመጫ በሚፈልግበት ጊዜም ዐይኑ አዳራሹን ዙሪያ ገብ እየማተረ ነበር ። በተለይ ሴቶች የተቀመጡበትን አካባቢ እሳት በጎረሱ ዐይኖቹ ቃኘ ።

‘ ዛሬም አልመጣችም ማለት ነው ? ’ አለ በልቡ ሳያስበው ጥርሶቹን እያንቀጫቀጨ ።

ከኀሊናው ጋር እንደ ልቡ ለመሟገት ፣ ተናግሮ ከሚያናግር ለመሸሽ ፣ ከታዛቢ ለመራቅና ግላዊ ነጻነቱን ለማግኘት ፣ አብዛኛውን ጊዜ በምግብ አዳራሹ ውስጥ ብቻውን ተቀምጦ መብላት ይመርጣል ። ሰላምን ከብቸኝነት ሊያገኛት ይጥራል ። ይህ ዐይን ፍቅር ላይ ከመውደቁ በፊትም የነበረው ጸባይ ነው ። በእርግጥ ፣ በዐይን ፍቅሩ ሳቢያ ደረጃው ከፍ ብሏል ። አሁንም ከወደ ጥግ በኩል ባዶ ጠረጴዛ ተመልክቶ ወደዚያው ሲያመራ ትዕግሥት ተመለከተችው ። የጐረሰችው አፏ ውስጥ ተንቀዋለለባት ። ቶሎ ብላ ዐይኗን ልትሰ



ብር ስትል ማርታ ቀለበቻት ። ቤተ ልሔም ሁለተኛዉ ምግብ አዳራሽ ስለምትመገብ አብራቸው አልነበረችም ።

“ ኤጭ ! እንዲያው ይሄ የማሽላ እንጀራቸው ! ” አለች ማርታ ፣ ትዕግሥትን ላለማሳፈር ብላ ። በእርግጥም የእሔዱ ግብዣ ገና ከውስጧ ስላልጠፋ ፣ ሽሮው አልዋጥ ብሏት እየታገለች ነበር ።

ትዕግሥት ምንም አላለችም ። ከዚያ በኋላ ቀናም አላለች ።

አቤል መቀመጥ የፈለገበት አካባቢ ሲደርስ ድንገት አየችው ። የቅናት እሳት የሚተፉት ዐይኖቹ በድንገተኛው አይታ ከማርታ ጋር በመገጣጠማቸው ድንግጥግጥ አለ ። እግሩ የተሳሰረ መሰለው ። ዐይኑን ሳይሰብር ከድንጋጤው ለማምለጥ ራመድ ሲል የአንዱ ወንበር እግር ጠለፈው ። በሁለት እጁ የምግብ ትሪውን ይዞ ስለ ነበር ፣ ተንገዳግዶ ሚዛኑን ጠብቆ መዳን አልቻለም ። አሳዛኝ ትርኢት ሆነ ። እሱ ከታች ፣ ያድነኛል ብሎ የተደገፈው ወንበር እግሩ ላይ ሲወድቅ ፣ የትሪው እንጀራና ወጥ ተገልብጦ ደረቱ ላይ ተደፋ ። የትኩሱ ወጥ ፍንጣቂ የደረሰባቸው በአካባቢው የተቀመጡ ተማሪዎች ተቆጥተው እየተፈናጠሩ ቢነሡም ፣ ትርኢቱ ቁጣቸውን ወደ ሣቅ ለወጠው ። ካካታውን ሰምቶ የአዳራሹ ቊመጋቢ ሁሉ ግልብጥ ብሎ ተነሣ — በአንዱ ውድቀት ሌላዉ ሊሥቅ ። የሳምንቱ መሣቂያና መሣሣቂያ ሆኖ የሚቆየው ወሬ ከሌላ አፍ ከመስማት ይልቅ በዐይኑ በብሌኑ ለማየት አንዱ ባንዱ ላይ መንጠራራት ራሱ ሌላ ትርኢት ሆነ ።

እስክንድርም እንደ ሌሎቹ ተንጠራርቶ ሲያይ ፣ ተዋናዩ አቤል መሆኑን በተመለከተ ጊዜ ዐይኑን ማመን አቃተው ። ገፊያውን እየበረጋገደ ዐልፎ አጠገቡ ሲደርስ ፣ በወጥ የተጨማለቀ ልብሱን እየጠራረገለት “ አቤል ፣ ” አቤል ምነው ? ምን ነካህ ? ” አለው ።

አቤል ምንም አልመለሰለትም ። ከወደቀበት ተነሥቶ ቢቆምም በድንጋጤ ክው ብሎአል ። ከዚያ አዳራሽ ተፈትልኮ መውጣት ነበር ፍላጎቱ ። ግን በየት በኩል ? የዚያ ሁሉ ተማሪ ዐይን አንድ ርምጃም እንደማያራምደው ገመተ ። ሆኖም እስክንድርን አጠገቡ በማግኘቱ ትንሽ ቀለል አለው ።

ትዕግሥት በዚች ደቂቃ ውስጥ መሬት ቁልቁል ተሰንጥቃ ብትውጣት ምንኛ በወደደች ! ካካታውን ሰምታ ቀና ስትልና አቤል ከያዘው ትሪ ጋር ሲወድቅ ስትመለከት ፣ ሽምቅቅ ብላ አንገቷን ጠረጴዛው ላይ እንደ ደፋች ቀረች ። የሚቀጥለውን ትርኢትም ለማየት ቀና አላለችም ። ተማሪው ሁሉ ወደ ወደቀው ወጣት ሳይሆን ወደ እሷ የሚያይ መሰላት ። እንባዋ ድንገት ሊመጣባት ሲል ገታችው ።

አቤል በምግብ አዳራሹ በር ከእስክንድር ጋር ሲወጣ ማርታ ተመለከተች ። እሷም በድንጋጤ የምትገባበት ጠፍቷታል ። ተደናግጦ ለመውደቁ ምክንያት የሆነው ከእሷ ጋር ዐይን ለዐይን መገጣጠማቸው ስለ መሰላት ፣ የኃጢአተኝነት ስሜት ተሰምቷታል ።

" ት . . . ትዕግሥት " አለቻት ፈራ ተባ በሚል ድምፅ ።

" ወዬ ! "

" እንሒድ ፣ እንውጣ ። "

ትዕግሥት እንባዋ እንዳይመጣ እንደ ምንም እየተጠነቀቀች ቀስ ብላ ቀና አለች ። እንደ ፈራችው አልሆነም ። አዳራሹ ውስጥ ያሉት ተማሪዎች በሁኔታው እየሣቁ ምግባቸውን ከማጣጣም በስተቀር እነትዕግሥትን ልብ ብለው አልተመለከቷቸውም ።

የበሉበትን ትሪ ሳያነሡ ፣ ግራ ቀኝ ሳይመለከቱ ፣ ሁለቱም አንገታቸውን አቅርቅረው ፈትለክ ብለው ወጡ ።

ከቀትር በኋላ ወደ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ፣ እስክንድር ከመኝታ ክፍሉ ተጠራ ። አልጋው ላይ ጋደም ብሎ እያነበበ ነበር ።

" ማን ነው የፈለገኝ ? " አለው ፣ ተልኮ የመጣውን ተማሪ ።

" አንዲት ልጅ ናት ። ወደዚህ ስመጣ አይታኝ አንተን እንድጠራላት ጠየቀችኝ ። "

" ስሜን የምታውቅ ናት ? "

" እሷ ፣ ስምህን ጠርታ ነው ንገርልኝ ያለችኝ ። "



በፈጣን ርምጃ ከመኝታ ክፍሉ ወጥቶ ፣ ደረጃውን ወርዶ ፣ ወደ ውጪ ብቅ ሲል ፣ ማርታ ደመቁን ቆማ ተመለከታት ። ግር አለው ። ከአሁን በፊት ግቢው ውስጥ መታየት ካልሆነ በስተቀር ንግግር አልነበራቸውም ።

ማርታ እሷ እንዳስጠራችው እንዲያውቅ ፈገግ አለችለት ። ዝብርቅርቅ ባለ ስሜት ልቡ እየነጠረ ቀረባት ።

" እኔ ጋ ነው? " አላት ፣ የውስጥ ስሜቱን በሚገልጽ ጣፋጭ ቅላጼ ።

" አዎ ! ስለ አቤል ልጠይቅህ ነው " አለችው ፣ ዕዝን ብላ ።

' የአቤልንም የእኔንም ስም እንዴት ዐወቀች ? ' ሲል አሰበ ። ወዲያው ግን ፣ ' ለምን ጅል እሆናለሁ ? እኔ እራሴ የእሷንና የትዕግሥትን ስም አጣርቼ ዐውቅ የለም እንዴ ! የእነሱ ማወቅ ያስደንቃል ? እንዲያውም ለወሬ ሴቶች ያብሳሉ ' አለ ፣ ባይነጋገሩም በዐይን እየተገራረፉ የተላለፉበትን ቀን በልቡ እያስታወሰ ።

እንደ ሴትነቷ ስማቸውን ዐውቃ እንዳላወቀች ለመሆን አለመሞከሯ አስደነቀው ። እመጣጧ ብዙ ነገር ጭንቅላቱ ውስጥ አተረማመሰበት ። የተጠቀለለ ነገር ይዛለች ።

' ትዕግሥት ራሷ መምጣት ፈርታ ልካት ይሆን?' ሲል አሰበ ። በምግብ አዳራሽ ውስጥ ለአቤል መውደቅ መንስኤው ከእነሱ ጋር እንደ ተያያዘ ፈጽሞ አላወቀም ነበር ።

" ምግብ ቤት ውስጥ ሲወድቅ ነበርሽ እንዴ ? " አላትና ፣ ከእሷ መልስ ሳይጠብቅ ፣ " የትኩሱ ወጥ ፍንጣቂ እጁን ትንሽ ጠበሰው እንጂ ሌላ ቦታ አልተጎዳም " አላት ።

ከንፈሯን መጠጠች ።

" እምልሽ ፣ መቼም እዚያ ሁሉ ተማሪ መሐል መውደቁ ራሱ ሕመም ነው ። አለ አይደል ! የአጋጣሚ ነገር ቢሆንም ያሳፍራል ። እና በድንጋጤ ትንሽ ተረብሾ ፣ ምሳውንም ባመጣለት ሊበላ አልቻለም ። አሁን ተኝቷል ። ድንጋጤው ሲያልፍለትና ሁኔታው ሲረሳው ደኅና ይሆናል " አላት ።

እንደ ገና ከንፈሯን መጠጠችና “ ውይ በናትህ ፥ አወ ዳደቁ እንዴት ስቀጠጠኝ መሰለህ ! ብቻ እንኳን ተረፈ ” አለችው ።

እስተዛዘኗ ልቡን ነካው ። ‘ ምነው እኔ በወደቅኩና እንዲህ ባዘንሽልኝ ! ’ አለ በሐሳቡ ።

ልቡ ስለተረጋጋ ዐይኖቹ ውበቷን ከላይ እስከ ታች ማስ ተዋል ይዘው ነበር ። አፍንጫውም ከትከሻቷ ጋር የሚተን ውን ሽቶ መቀበል ጀምሯል ። ስትናገር ትንፋሿ ራሱ ሽቶ መሰለው ። ከእሑድ የሥርግ አለባበሷና አኳኋኗ ከፊሉ ላይዋ ላይ ቀርቶ ነበር ። በአንገተ-ክፍቱ ሹራቧ በኩል የተላጠ ሽንኩርት መሰለው ብቅ ያሉት ጡቶቿ ከእስክንድር ዐይን ጋር ተፋጠጡ ። ጡት መያዣ አላደረገችም ነበር ።

“ ይህንን ለአቤል ነው ያመጣሁለት ” አለችና ፥ ይዛው የነበረውን የተጠቀለለ ነገር ሰጠችው ። ኬክ ገዝታ ለት ነበር ።

እስክንድር የባሰውን ድንግርግር አለው ። ‘ ይህን ለሚ ያህል ውለታ የሚያበቃ ግንኙነት ነበር ማለት ነው ? ’ አለ በልቡ ።አቤልን ጠረጠረው ። ሆኖም ከማርታ ጋር አቀራርቦ ያነጋገረውን ይህን አጋጣሚ ወደደው ።

ኬኩን ሰጥታው ጥቂት መንገድ ከሔደች በኋላ ፥ በአን ዳች ግፊት ተስባ ዘወር ስትል ፥ እንዳጋጣሚ እስክንድርም የዞረባት ቅጽበት ስለ ነበረች ዐይን ለዐይን ተገጣጠሙ ። ሁለቱም ተፋፍረው ፊታቸውን ወደ መንገዳቸው መለሱ ።

እስክንድር ኬኩን ይዞ ወደ መኝታ ክፍሉ ሲመለስ ፥ ‘ጆኒ ለካ የዋህ ስትመስል ፥ ውስጥ ውስጡን ጉዳይዋን አጠና ክራለች ’ እያለ አቤልን በልቡ እያማው ነበር ።

ከክፍሉ እንደ ገባ አቤልን እስነሣውና ፥ “ ቀና በል እባክህ ፤ ጣፋጭ ምግብና ጣፋጭ ወሬ አምጥቼልሃለሁ ” አለውና ፥ በችኮላ እሽጉን ፈትቶ አንድ ኬክ አውጥቶ ለራሱ ገመጠ ።

አቤል ለምንም ነገር ባልጓጓ ስሜት ፥ “ ተወኝ እባክህ ፥ እስክንድር ፥ ምንም አልፈልግም ። ብተኛ ይሻለኛል ” አለው ። ፊቱን ትራሱ ላይ እንደ ደፋ ነበር ።



እስክንድር ሌላ ኬክ አውጥቶ ፥ ጓደኝነት በተሞላው ስሜት ፥ “ ኤጭ ! አንቺ ደሞ እንዲያው በቀላል ነገር ሙብ ሽቅ ይቀናሻል ። ተደናቅፎ መውደቅ በማንም ላይ ሊደ ርስ የሚችል አጋጣሚ ነው ። ይልቅ ተነሽና ይህችን ነገር ግመጭ፥ ” አለው ።

አቤል ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ፥ ዝም !

እስክንድር ነገሩን ለማቅለል ያህል ብቻ ሳይሆን ፥ በጊዜው ያስደንግጥ እንጂ በእርግጥም ቀላል ነው ብሎ ነው የገመተው ። የአቤል ምላሽ ግን ጠነከረበት ።

ትንሽ ቆዩና ፥ ዘዶ ያገኘ ወይም አቤልን ከመጥፎ ስሜቱ ያዘናጋ መስሎት ፥ “ እረ ሌላው ቢቀር ውቃቢዋ ያይሃል ! ይበላልኛል ብላ ደክማ አምጥታልህ — ” አለና ሳይጨርስ ፥ አቤል አቋረጠው ።

“ እንዴ ኬኩን ማነው ያመጣው ? ” አለ አቤል ፥ ጉጉት ባዘለ ደካማ ድምፅ ፥ ቀስ ብሎ ፊቱን ከደፋበት ትራስ አነሣ ። ምሳውን አልበላ ስላለው ኬኩን እስክንድር ራሱ ገዝቶ ያመጣለት መስሎት ነበር ።

“ ማርታ ‘ ኮ ናት ያመጣችልህ ” አለ እስክንድር ፥ ስሟን ሲጠራ አንዳች ነገር ሽምቅቅ እያረገው ።

“ እ? ! ” የድንጋጤም ፥ የመገረምም ነበር ።

“ ማርታ የ-የአንትና ጓደኛ ”

የትዕግሥትን ስም በአቤል ፊት መጥራት አልፈለገም ። አቤል ግን ወዲያው ገባው ። ሥሮቹ ተገታትረው ዐይኑ ደም መሰለ ።

“ በናትህ ስሟን አትጥራብኝ ! ” አለው ፥ ምርር ባለ አነጋገር ፥ “ እሷን ልጅ ላለማየት ስል ይህን ዩኒቨርስቲ ሳል ለቅ አልቀርም ። ”

እስክንድር ነገሩ ተምታታበት ። ‘ ትዕግሥትን ወይስ ማርታን ? ማንኛቸውን ላለማየት ? ’ አለ በልቡ ። የቀድሞ ጥርጣሬው የተሳሳተ መሰለው ። የሚናገረው ነገር ጠፍቶት ዝም አለ ።

ክፉኛ የቀሉት የአቤል ዐይኖች የታመቀ እንባ ተዘርግፎ እንዳይፈስ ትንቅንቅ መያዛቸውን እስክንድር ገመተ ። ግቢ ነፍስ ፣ ውጪ ነፍስ ! ክፉኛ አሳዘነው ። የሆነ ነገር ልደብቅ ብላ ከውስጥ የምትቃጠለው ፣ የምትብከነከነውና ነዳ የምትጨስው ሕይወቱ ውስጥ ውስጡን አምርራ ስታለቅስ በስሜቱ ታየው ። ትካዜው ተጋባበት ። እናም ዝም ብሎ መቆየት አልቻለም ።

" ስማ ፣ አቤል ! ልረዳህ የምችለው ነገር ካለ ፣ ስሜትህን ሳትደብቅ በንጹሕ የጓደኝነት መንፈስ ንገረኝ ። ስትጨነቅ ማየት አልፈልግም ። የፈለገው ነገር ይሁን ፣ እሠዋልሃለሁ ! "

እስክንድር ከአቤል ጋር ከተዋወቀበት ጊዜ ጀምሮ እንዲህ አምርሮና በትካዜ ተመስጦ ሲናገር ፣ የመጀመሪያ ጊዜው ነበር ። ከማርታ ጋር መተዋወቂ ከትዕግሥት ጋር አስተዋውቆኝ ፣ የአቤልን ችግር እፈታለት ይሆናል የሚል እምነት ስላደረበት ፣ ' እሠዋልሃለሁ ' ያለው ከዚህ ተነሥቶ ነበር ።

የእስክንድር ወንድማዊ የንግግር ቃና ፣ የአቤልን ልብ ክፉኛ ኰረኰረው ። በተለይ ' እሠዋልሃለሁ ' የምትለዋ ቃል ከእስክንድር አፍ የወጣችው እንባ በተናነቀው ስሜት ስለነበር ፣ የልቡን አንጀት በኀዘን ፍላጻ ወጋችው ። የሆነ ነገር ሊነግረው ፈለገ ። ግን ምን ? አፉን ከማጥፋት በስተቀር እስክንድር መፍትሔ የሚያገኝለት አልመሰለውም ።

ምንም አልተናገረም ። መልሶ ፊቱን ከትራሱ ላይ ደፋው ።

" አንተ ከባድ አርገህ የወሰድከው ነገር ይሄኔ በቀላሉ የሚፈታ ይሆናል " አለው እስክንድር ።

አቤል አልመለሰም ።

" ስማ እንጂ ፣ አቤል ! እባክህ ንገረኝ ፤ ዝም ብለህ ራስህን አታስጨንቅ ። ሐሳብን ለሰው ማካፈል ራሱ ከሕመም ያድናል ። መጥፎ ተፈጥሮ ነው ያለህ ። ለምን ሁሉን ነገር በግልህ ለመወጣት ትሞክራለህ ? ሰው ያስፈልግሃል ! እንግዲያው የጓደኝነት ትርጉሙ ምንድነው ? ነገር ሆድ ውስጥ



አምቆ መጨነቅ መጥፎ ነው " አለው ፤ በእርግጥም የሚያስከትለው መጥፎ ውጤት እየታየውና መምህር ዮናታን የነገሩት እየታወሰው ።

ስለ እሱ ሕመም እስክንድር ይህን ያህል መጨነቁ ሆዱን ስላባባው ፣ አቤል ቀና ብሎ ፣ " ተወኝ እባክህ እስክንድር ፣ ስለ እርዳታህ አመሰግናለሁ ። የእኔ ሕመም ግን መፍትሔ የለውም ። አትድከም " ሊለው ፈልጎ ነበር ። ነገር ግን እንባው ቀድሞ ዝርግፍ ስላለ መናገር አልቻለም ። ፊቱን ትራሱ ላይ እንደ ደፋ አለቀሰ ። ትዕግሥት ከፊቱ ቆማ በንቀት ፣ " አልቃሻ ወንድ ! " የምትለው መሰለው ። ማርታ በእንባው የምትቀልድበት ፣ ከት ከት ብላ የምትሥቅበት መሰለው ።

" ስማ ፣ አቤል . . . ! " እስክንድር ቢቸግረው ትከሻውን ነቀነቀው ።

መልስ የለም

" አቤል . . . "

ዝም !

እስክንድር በሽቆ ሲጋራውን አውጥቶ ለኮሰና ፣ በልቡ ' ቤቨቲያ ! የራስህ ጉዳይ ነው ! ' ብሎ ጥሎት ወጣ ።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

አንድ የተፈጥሮ ሳይንስ ምሩቅ መምህር ለድኅረ-ምረቃ የሚያበቃውን የጥናት ጽሑፍ መዘክር ከማቅረቡ በፊት አማካሪው ዶክተር አጥናፉ የስንዴ ተክሉን እንዲጎበኙለት ጋበዛቸው ። ፕሮጀክቱን የሚሠራው በስንዴ ተክል ነበር - የተለያየ አፈር በስንዴ አበቃቀል ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ አጥንቶ ለማቅረብ ።

ዮናታን ጉዳዩ ባይመለከታቸው ፕሮጀክቱን አቅራቢው መምህር በግል ወዳጅነቱ እንዲ ያዩለት ስለ ጋበዛቸው ከዶክተር አጥናፉ ጋር ሔደው ነበር ። ለጥናት ተክሎች ከተሠራችው ጎጆ ውስጥ እንደገቡ በጣሳ ጉች ጉች ብለው የተቀመጡትን የስንዴ ተክሎች አትኩረው መጐብኘት ጀመሩ ። ከመስታወት ቤቷ ላይ አረንጓዴው ቀለም ሙልጭ ብሎ ስለጠፋ ቃጠሎው ሌላ ከተማ የገቡ ይመስል ነበር ።

" ለምን የዚህች ጎጆ ስም ተቀይሮ ' ኋይት ሀውስ ' አይባልም ! " አሉ ዮናታን በቀልድ ዐይነት - ነገር ግን ወቀሳን ባዘለ አነጋገር ። አረንጓዴው ቀለም ከጠፋ በኋላ ፣ " ግሪን ሀውስ " ማለቱ ትርጉመ-ቢስ መሆኑን ለመጠቆም ነበር ። ' ኋይት ሀውስ' እንዳይባልማ የተክሏን ጎጆ ከአሜሪካን ቤተ መንግሥት ጎን ማስቀመጥ ይሆናላ ! " አሉ ዶክተር አጥናፉ ፣ ቀልድን በቀልድ በመመለስ ።

ምንም አስተያየት ሳይሰጡ ስምንት የተክል ቆርቆሮዎች ማለፋቸው አስጎብኚውን ሳያበሽቀው አልቀረም ። ከኋላ ከኋላቸው እየተከተለ ፣ " ግሩም ነው ! " የሚል ድምፅ ይጠብቅ ነበር ።

" ይህ የየት አገር ዐፈር ነው ? " አሉ ዶክተር አጥናፉ ፣ ዐፈሩ በደንብ ተስማምቶአቸው ከሁሉም ፋፍተው የበቀሉትን ዐምስት ያህል የቆርቆሮ ተክሎች እየተመለከቱ ።

“ የደብረ ዘይት ዐፈር ነው ” አለ አስጎብኚው ፣ ቆርቆሮው ላይ የጻፈውን ኮድ ተመልክቶ ፤ “ ይገርምዎታል ! በአገራችን የስንዴ ተክል ርዝመት ውስጥ ከፍተኛውን ደረጃ ሳይዝ አይቀርም ” ብሎ ፣ የዕድገቱን ፍጥነትና ርዝመት የላከበትን ሰነድ ፍለጋ ማኅደሩን ያገላብጥ ጀመር ።

“ ፎቶግራፍ አስነሥተኸዋል ? ”

“ አላስነሣሁትም ። የጅማው ዐፈር ላይ የተተከሉት ፍጥነትም ባይኖራቸው ዕድገታቸውን ስላላቋረጡ ፣ ትንሽ ልጠብቃቸውና አንድ ላይ አስነሣቸዋለሁ ብዬ ነው ” አለ አስጎብኚዉ ፣ ፊቱ ብቻ ሳይሆን ልቡም ፈክቶ ። የፎቶግራፍ ጥያቄ ለፕሮጀክቱ ፍጻሜ መቃረቢያ ስለሆነ ፣ ዶክተር አጥናፉ ይህን ማንሣታቸው በተዘዋዋሪም ቢሆን በውጤቱ እንደረኩ ለመገመት አስችሎታል ።

“ አሁኑኑ ብታስነሣው የሚሻል ይመስለኛል ። ካለበለዚያ የጅማውን ስትጠብቅ ዕድገቱን የጨረሰው የደብረ ዘይቱ ሊተኛና ፍሬው ሊረግፍ ይችላል ” ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጡት ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ዮናታን ምንም ሳይተነፍሱ ዐይናቸውን ከአንዱ ቆርቆሮ ተክል ላይ እንደ ተከሉ ቀርተው ነበር። እያንዳንዱ ቆርቆሮ የያዘው ስምንት ፍሬ ነው ፤ የዮናታንን ዐይን የጠለፈችው ቆርቆሮ ሰባቱን ፍሬዎች ጅፍ አርጋ አብቅላ አንዷን እቅጭጯ አስቀርታታለች ። ዮናታን በመቀጨጭ ላይ ያለችውን የስንዴ ዘለላ አትኩረው ሲመለከቱ አቤል በሐሳባቸው መጣባቸው ። ስለዚህ ነበር ከአስተያየት ተቆጥበው የቆዩት ። ‘ አቤል ራሱ እንደ ስንዴዋ ዘለላ በመቀጨጭ ላይ ያለ ሎጋ ወጣት ነው ’ አሉ በልባቸው ።

ትንሽ ቆይተው ፣ “ ይህችን ነገር ታያታለህ ? ” አሉ ፣ ፊታቸውን ወደ ዶክተር አጥናፉ መልሰው ።

“ የቷን ? ”

አስጎብኚዉም “ ምን ተገኘ ? ” በሚል ስሜት ወደ ቆርቆሮው አተኩረ ።



“ ይቺ ፣ በመቀጨጭ ላይ ያለችዋ ” አሉ ዮናታን ፣ ወደ ቆርቆሮው ውስጥ በጣታቸው እየመለከቱ ።

“ እም ፣ አዎ ከእንግዲህ የምታድግ አትመስልም ” አሉ ዶክተር አጥናፉ ፣ ብዙም ባልተደነቀ ስሜት ።

“ ከምን የመጣ ይመስልሃል ? ” አሉ ዮናታን ፣ ዐይናቸውን ወደ አስጎብኚው እያሸጋገሩ ።

“ አካባቢው አልተስማማት ይሆናላ ! ” አሉ ዶክተር አጥናፉ ፣ በቀልድ ዐይነት ! “ ወይም ደግሞ ፍሬዋ ከጓደኞቿ ተለይታ በተለየ ዐፈር ውስጥ መብቀል ፈልጋ ይሆናል ። ”

ከት ብሎም ባሥይቅ አስጎብኚው ፈገግ አለ ። ዮናታን ግን የተቋጠረው ግንባራቸው አልተፈታም ። ይብሱን ነገሩን አጠንክረው ፣

“ የአካባቢም ተጽዕኖ ሆነ ፣ የዐፈሩ አለመስማማት ፣ ወይም ሌላ ችግር ፣ የስንዴዋ መቀጨጭ ከአያያዝ ግድየለሽነት የመጣ ነው ። ገና ከእንጭጭነቷ ችግሯን አስተውሎ አካባቢዋን ወይም አፈሯን መለወጥ ቢቻል ኖሮ ለዚህ አትደርስም ነበር ። ግን አንድ ነች ። አንድ ነገር አንድ ነውና አብዛኛውን ጊዜ አናስብበትም ። አናስተውለውም ። ጣሳው ሙሉ ተክል ሊበላሽ ቢሆን ኖሮ ግን ወዲያው መፍትሔ በተፈለገለት ነበር ። ”

አስጎብኚው በድንጋጤ ክው ብሎ ቀረ ። “ አምርረዋል ፣ ወይስ ይቀልዳሉ ? ” አለ በልቡ እሱም ። አማካሪው ዶክተር አጥናፉ ችል ያሉትን ነገር ዮናታን አምርረው መያዛቸው ምክንያቱ አልገባህ አለው ። “ ምነው ባልጋበዝኳቸው ! ” አለ በልቡ ። አነጋገራቸው ዶክተር አጥናፉን ይለው ጥብኛል ብሎ ስለፈራ ዮናታንን በጥላቻ እያያቸው ።

“ ይህ’ኮ አብዛኛውን ጊዜ ሊደርስ የሚችል አጋጣሚ ነው ። ደግሞስ የአንዷ መቀጨጭ ምን ያህል ይጎዳል ብለህ ነው ? የዐፈሩ ተጽዕኖ በአብዛኛው ስንዴ ዕድገት ሊለካ ይችላል ” አሉ ዶክተር ፣ አሁንም ለነገሩ ክብደት ሳይሰጡት ።

“ ይጎዳል እንጂ ፣ እንዴት አይጎዳም ? ” አሉ ዮናታን አምርረው ። “ የቆርቆሮውን ተክል’ኮ ስምንት የምታስኘው

ይሆች እንዲ ስትጨርስ ነበር። ስትጉድል ግን ሰባት ታረገዋለች። አንድ ሳንቲም "ዋጋ የለውም" እንላለን። ግን "ዋጋ እንዳለው የምንረዳው አራት ሳንቲም ይዘን ስንቀር ነው።"

እስጐብኝው የባሰውን በጥላቻ ገላመጣቸው። እሳቸው ግን ልብ አላሉትም። እሱን መጉዳታቸውም አልታወቃቸውም። ዶክተር አጥናፉ ራሳቸው፣ "ሰውዬው አበደ እንዴ?" በማለት ዐይነት በሆዳቸው እየሣቁ፣ ምንም ሊጠይቁ ወይም ሊናገሩ ስላልቻሉ ዝም አሉ።

ከጥቂት ዝምታ በኋላ ዮናታን ልምጭምጭ ፈገግታ እያሳዩ፣ በምጸታዊ አነጋገር "አየህ፣ የአቤልም ነገር እንዲሁ ነው" አሏቸው።

ዶክተር አጥናፉ የዮናታን ውስጣዊ ስሜት እንዲህ የተለዋወጠበት ምክንያት ያው ገባቸው። ስለ አቤል ጉዳይ ደጋግመው አነጋግረዋቸው ነበር። ነገር ግን፣ ለጉዳዩ ብዙም ክብደት ወይም አትኩሮት ባለመስጠት ችል ብለውት ስለቆዩ አሁን ጥያቄም ይሁን መልስ ማንሣት አልፈለጉም። ሐሳባቸውን ሁሉ ወደ ተክሉ በመሰብሰብ ዐይነት ከአስጐብኝው ጋር ሐሳብ በመለዋወጥ ዮናታን የተነሡበትን ሐሳብ ለማዘናጋት ሞከሩ። ይሁን እንጂ፣ ዮናታን ውስጥ የሚንቦገቦገው ሐሳብ በቀላሉ የሚበርድ አልነበረም። ጉብኝቱን ጨርሰው ከተክሉ ቤት ሲወጡ እንደ ገና አነሡባቸው።

"ሁላችሁም የዚህን ልጅ ጉዳይ ችል ማለታችሁ ነው? ያቤልን?! እንዴት ነው? አሁንም አልተሻለው?" አሉ ዶክተር አጥናፉ ሸሽተው የማያመልጡት ነገር መሆኑን ገምተው።

"ይሻለዋል? ጉንፋን'ኮ አይደለም ያመመው።" ይህኛው አነጋገራቸው ቁጣ ብቻ ሳይሆን ተስፋ መቁረጥም ነበረበት።

የዮናታን አነጋገር ዶክተር አጥናፉን አላስቆጣቸውም። የቅርብ ጓደኝነት ስላላቸው አንዳቸው የአንዳቸውን ጸባይ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ዮናታን ከውስጥ ሥቀው ከላይ ጥርሳቸውን ማሳየት አይችሉም። የተማረሩበትን ወይም የበሸቁበትን ነገር ማንም ፊት ይሁን ከማንም ጋር፣ ፊትለፊት በቁጣ ተናግረው ነው የሚወጡት። ከዚያ ንዴቱ ቢበርድላቸው ያው



ሰው አክባሪነታቸው፣ ፍቅር የተሞላበት ስላምታቸው፣ ዮናታንነታቸው ይመለሳል። ነገር ግን የዚህ ልጅ ጉዳይ ይህን ያህል ለምን እንዳንገበገባቸው ዶክተር አጥናፉ ጥርት ብሎ ሊታያቸው አልቻለም።

"ችግሩ'ኮ!" አሉ ዶክተር አጥናፉ፣ የዮናታንን ቁጣ ማስታገሥ በሚችል ለዘብ ያለ አነጋገር።፣ "ችግሩ የሁሉም አለመተባበር ነው። ከአሁን በፊት በዩኒቨርስቲው ውስጥ እንዲህ ዐይነት ጉዳይ ትልቅ አትኩሮት ተሰጥቶት ስላልተሠራ አሁንም ..."

ዮናታን አላስጨረሳቸውም።

"እኔም እኮ የምለው ይህንኑ ነው። ለምን አትኩሮት አይሰጠውም? በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ካሉት ችግሮች አንዱ አይደለም ወይ? አየህ! ፍቅር ሲሠምር፣ ሲገኝ ሲያብብ ደስታ ፍሥሐ ነው። ከመገኘቱ በፊት ወይም ተገኝቶ ሲጠፋ ኃይለኛ ጥማት፣ ሥቃይ፣ ሕመም ነው፣" አሉና፣ ነገሩን ከውሉ ጋር እንደማያያዝ ትንሽ ካሰቡ በኋላ፣ "እዎ! እና፣ ምንም ይሁን ምን፣ ግለሰብን ከዓላማው ወይም ከግቡ የሚያዘናጋ ወይም ራሱን የሚያስጠላ ሁኔታ እስከሆነ ድረስ፣ መድኃኒቱ መፈለግ አለበት። አሁን አቤል በዚህ ሁኔታ ተጨናግፎ ትምህርቱን ቢያቋርጥ ወይም ተደባብሶ ቢመረቅ፣ ሁለተኛ ወደ ትምህርትና ምርምር ዓለም ፊቱን እንደማይመልስ አታውቅም?"

"እሱ እንኳን በጤናቸው የሚመረቁትም የአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ጸባይ ነው። ሺ አስመርቀናል፤ ነገር ግን ምንም ተአምር የሠራ አላየንም" አሉ ዶክተር አጥናፉ በንቀትና ተስፋ በቆረጠ ስሜት።

"ይህ የሚሆነው ለምን ይመስልሃል?! በእኔ ግምት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቶቻቸውን በፍቅር እንዲጀምሩ ስለማናደርጋቸው ነው።"

ሳያስቡት ዶክተር አጥናፉ ቢሮ ስለ ደረሱ፣ በሩን ለመክፈት ቁልፉን እየጠመዘዙ አሁንም በተስላችና ነገሩን ቶሎ ለመቁረጥ በዳዳ ስሜት፣ "ብቻ ሁሉም ነገሩን እንዳንተ

ቢያስብበት ምናልባት ውጤት ያገኝ ይሆናል ። ግን እንዳየሁት ፡ ይህን ጉዳይ ብሎ ኮሚቴ ላይ አቅርቦ መፍትሔ ለመፈለግ የሚሻ ሰው ! እንጃ ”

“ ይህ ከምን የመጣ ይመስልሃል ? ” አሉ ዮናታን ፡ ተከትለዋቸው ወደ ቢሮ ውስጥ እየገቡ ፤ “ ይህ ራሱ ምሁርነታችን የሚያስከትልብን በሽታ ነው ። ራሳችንን በጣም ከፍ አድርገን ስለምንገምት ፡ ከኛ በኋላ ሰው የሚፈጠር አይመስለንም ። ዐይናችንን ገልጠን ከተማሪዎቻችን መሐል ታላላቅ ሰዎች ሊበቅሉ እንደሚችሉ ማየትና መገመት አለብን ። ይህ ስሜት ሲኖረን ብቻ ነው-ተማሪዎቻችን እንቅፋት እንዳይመታቸው ልንጠነቀቅላቸው የምንችለው ”

“ ስደበና ! ” አሉና ዶክተር አጥናፉ በቀልድ ፡ “ ለማንኛውም እስኪ ቁጭ በል ” ሲሉ ዮናታንን ጋበዟቸው ።

“ አልቀመጥም ” አሉ ዮናታን ፡ ሰዓታቸውን እየተመለከቱ፡፡ “ አ! እንዲያውም ሰዓት አሳለፍን ። በዐሥር ሰዓት አንድ ተማሪ ቀጥሬ ነበር ”

“ እሺ እስቲ ፡ እንግዲህ በሚቻለን መንገድ እንታገላለና ! ” አሉ ዶክተር አጥናፉ ፡ ጉዳዩ ከውስጥ ባይፈነቅላቸውም ዮናታንን ለማስደሰት ያህል ።

“ በውነት ፡ እንዲያው በሚቻለን መንገድ ይህንን ልጅ መርዳት አለብን ። እባክህ ቸል አትበል ” አሉ ዮናታንም ፡ ረጋ ባለ አንደበትና ረዳት በሚፈልግ ስሜት ።

ከዚያ ፡ ወዲያው ወጥተው በመኪናቸው ወደ ስድስት ኪሎ በረሩ ። ከቢሮአቸው ሲደርሱ እስክንድር መዝጊያውን ተደግፎ ቆሞ አገኙት ።

“ ሶሪ ፡ ዘገየሁብህ አይደለም ? ” አሉት በሩን ለመክፈት እየተቻኮሉ ። ዐሥር ደቂቃ አሳልፈውበት ነበር ። ጠዋት ገለጻ ክፍላቸው ውስጥ ክፍለ-ጊዜአቸውን ጨርሰው ሲወጡ ነበር በዚህ ሰዓት እንዲያገኛቸው የቀጠሩት ። የፈለጉት ለአቤል ጉዳይ መሆኑን ፈጽሞ አልተጠራጠረም ። ምክንያቱም አቤል ከእሳቸው ገለጻ ክፍለ — ጊዜ ሦስቱን ቀን ቈተከታታይ አልገባም ። ክፍሉ ውስጥ ቢጠይቋት እስክንድር የሰጣቸው መልስ ፡ “ ራሱን ትንሹ ስላመመው ነው ”



ብሎ ነበር ። ነገር ግን ደጋግሞ መቅረቱ ከዚህ የከፋ ሁኔታ ቢያጋጥመው ነው ብለው ስላሰቡ ፤ ስለሱ ሊጠይቁት ነው የቀጠሩት ።

“ ስለ አቤል ልጠይቅህ ነበር'ኮ ” አሉት ዮናታን ገና ቁጭ ከማለታቸው ፤ “ በእርግጥ በጤናው ነው ? ”

እስክንድር የተጠየቀው ያው የጠበቀውን ነገር ቢሆንም ፡ ስለ አቤል መስማትም ሆነ መናገር የማይፈልግበት ወቅት ነበር ። ሁኔታው ያበሽቀዋል ። ምንም ግልጽ የሆነለት ነገር የለም ። እንደ ጓደኝነቱ ቀርቦ ቢያዋየው ፡ አባትነት በተሞላው ሁኔታ ቢያስታምመውም ፡ ቢያሻሽውም ፡ ቢኮረኩረውም ከአቤል ጠብ ያለ ነገር የለም ። አቤል አይናገርም ። አቤል ታፍኖ መሞት የሚፈልግ ሰው ነው ።

“ ስለ እሱ ሊጠይቁኝ መሆኑ ገብቶኛል ” አለ እስክንድር ። “ በቀደም ዕለት ምግብ አዳራሽ ሲገባ የሆነ ነገር አደናቅፎት ወድቆ ነበር ። ያን ያህል ጉዳት እንኳ አሳገኘውም ፤ ግን እንጃ ! ክፍልም አልገባም አሉ ፡ ተኝቶ ነው የሚውለው የመንፈስ መረበሽ መሰለኝ ። ”

“ እህ ! እንዲያ ነው ? ” አሉ ዮናታን ፡ ነገሩ ልባቸውን ቢከብደውም ኀዘናቸውን ለመደበቅ ሞክረው ። “ ምን መንፈሱ የተጐዳ ሰው'ኮ ዕንቅፋትም ይበቃዋል ። ”

“ እንደዚያ ሆኖ ነው መሰለኝ ። ”

ዮናታን ለደቂቃ ያህል ዝም አሉ ። ብዙ ነገር ሐሳባቸው ውስጥ እየተተራመሰባቸው ነበር ። እስክንድር የዮናታን ስሜት ምን ያህል በጭንቀት እንደ ተወጣጠረ ከገጽታቸው ላይ ማንበብ ችሏል ። ‘ ይህን ያህል ለአንድ ተማሪ መጨነቃቸው ለምንድነው? ’ ሲል አሰበ ። ነገር ግን የአቤል ሁኔታ እሱን ራሱን እንዳስጨነቀው ባሰበ ጊዜ ዮናታንም ተመሳሳይ ስሜት ሊያድርባቸው እንደሚችል ገመተ ። ሐቀኛ ምሁር ነገ የሚተካውን ጠንካራ ተማሪ በጥቃቅን ማኅበራዊ ችግር ተደናቅፎ ሲቀር ማየት አይፈልግም ።

የዮናታን ሁኔታ ፡ በእስክንድር ስሜት ውስጥ እንዳች ግፊት ፈጠረበት ። ‘ ማንኛውንም መሥዋዕትነት ከፍሎ አቤ

ልን ማዳን !' . . . ግን እንዴት ? መፍትሔ ከመፈለግማ እስከ አሁንም አልቦዘነም ነበር ። ' በቅርቡ ከማርታ ጋር መተዋወቁ ምናልባት ለመፍትሔው ጥርጊያ መንገድ ይሆናል ' ብሎ ገመተ ። በሳምንቱ ውስጥ ከማርታ ጋር በሩቅ አንገት ከመስበር አልፈው ፤ ሞቅ ያለ ሰላምታ መለዋወጥ ጀምረዋል። እንዲያውም ፈገግታዋ እየሞቀው ዐይኗ ወንድነቱን እየተፈታተነው ፤ በዳሌዋ ላይ በልቡ ዝቶባታል ። ' በእሷስ ድርብ ሚና ነው የምጫወተው ' ብሎ አስቧል ።

ባገኘችው ቁጥር ስለ አቤል ትጠይቀዋለች ። አቅልሎ ይመልስላታል ። ትዕግሥትንም ከእሷ ጋር ስለሚያገኛት ሰላም ይላታል ። ሰላም ትለዋለች ። ስለ አቤል ግን ጠይቃውም አታውቅ ። ለአፍታ ያህልም ቢሆን ከማርታ ጋር ጨዋታ ሲያነሣ እንኳ አብራቸው አትሳተፍም ። ፈንጠር ብላ ቆማ ትጠብቃታለች ። ይሁን እንጂ ፣ እሷም ፍቅሯን አምቃ እንደምትሠቃይ እስክንድር የሰውነቷን መክሳትና መላ አኳኋኗን በማስተዋል መገመት ችሏል ። መጀመሪያ ላይ ዝምታዋ አስፈራርቶት ነበር ። በኋላ ግን አቤል በማርታ ላይ ያለውን ዐይነት መጥፎ ስሜት ፤ ትዕግሥት በእሱ በእስክንድር ላይ እንደ ሌላት ከሰላምታ አለዋወጧ ገብቶታል ።

" ታዲያ እንዴት ይደርሳል ? ብዙ ገለጻ አምልጦታል ። ሳምንት ቀላል ጊዜ አይደለም " ሲሉ ዮናታን የጸጥታውን አየር አደፈረሱት ።

" እሱ እንኳ እኔ የወሰድኩትን ማስታወሻ እያነበበ ከመጻሕፍት ጋር ሲያገናዝብ ይደርስብናል " አለና እስክንድር ፤ መናገር የፈለገውን ሳይጨርስ ፤ አንድ ነገር ራሱን መታው ። ይህን መናገር የደፈረው የቀድሞው አቤል በጭንቅላቱ ውስጥ ስለ ተቀረጸ ነው ። በርግጥም አቤል በተለይ የቀለም ትምህርትን ለመረዳት ፈጣን ነበር ። ብሩህ አእምሮ ነበረው ። አሁን ግን የብሩህ አእምሮው ዐይኖች በሆነ ነገር ተሸፍነዋል ። የብሩህ አእምሮው ልብ በሆነ ነገር ተደፍኗል ። እናም እስክንድር ይህ ሐሳብ ድንገት በታየው ጊዜ ለዮናታን አጉል ቃል እንዳይገባ ፈርቶ ፤ " ብቻ እንጃ " አላቸው ፤ በሚያመነታ ስሜት ።

" እንዴት ? " አሉ ዮናታን ።



" ማለቴ ፤ በአሁኑ ጊዜ እንኳ ሳምንት ወደ ኋላ የቀረባቸውን የትምህርት ዐይነቶች ለማሟላት ብዙ መጽሐፍ ያገላብጣል ብዬ ቃል መግባቱ ያስፈራኛል " አላቸው ።

ዮናታን ነገሩ ስለ ገባቸው ደብዛዛ ፈገግታ አሳዩ ። ግን ብዙም ሳይቆዩ ፈገግታው ጭልም ብሎ ጠፍቶ ፊታቸው ተለዋወጠ ። ግንባራቸው ላይ ትልቅ የደምሥር ተምዘግዝጎ ወጣ ፤ ቅጽበታዊ ውሳኔ ከአእምሮአቸው ታዞ ምላሳቸውጋ ደርሶ ነበር ።

ቃላቱን ከመወርወራቸው በፊት ያለምክንያት መነጽራቸውን አወለቁ ። እንደ ወትሮአቸው ዐይናቸውን ሳያሹ መልሰው አደረጉት ። ወደ ኋላቸው ተለጥጠው ተቀመጡ ። እናም ተነፈሱ ።

" ይህን ዓመት ትምህርቱን ማቋረጥ ይኖርበታል ፤ በኔ ግምት ።

እስክንድር ግር አለው ፤ ዝም ብሎ እያያቸው ፤

' እና በምን ዐይነት መንገድ ልንመክረው እንችላለን ?' አለ በልቡ ።

' ምን ዐይነት ምክር ነው ፤ ትምህርትን አቋርጥ ብሎ ምክር ? '

" እህሳ ፤ ምነው ዝም አልክ ? " አሉት ።

ትንሽ ሲያመነታ ቆየና ፤ " ግን ይህችን ዓመት እንደ ምንም ጨርሶ ቢገላገል አይሻልም ? " አላቸው ።

" ትምህርት የሚገላገሉት ዕዳ ነው እንዴ ? "

" ማለቴ " አለ እስክንድር ፤ ሐሳባቸው ስለ ገባው ቶሎ ብሎ በማደናገር ዐይነት ። " ሌላ ዓመት መጨመሩ ራሱ የበለጠ ሊረብሸው ይችላል ብዬ ነው ፤ ጓደኞቹ ሥራ ይዘው ሲያይ ። "

" ይሄ ጊዜያዊ ሁኔታ ነው ። ጊዜያዊ ችግር ነው ። እኔ የማስበው ግን ከዘላቂ ሕይወቱ አንጻር ነው ። በእኔ ግምት አቤል ከጤናማ አእምሮው ጋር መመረቅ አለበት ። ከዚያ በኋላ ሥራ ይዞ ገንዘብ ማግኘት ሳይሆን ለዓለም አንድ ነገር ማበርከት ይሆናል ሕልሙ " አሉና ዮናታን ፤ ከመጽሐፍ

መደርደሪያቸው ላይ እንድ ጥራዝ እንሥተው ገለጡ ። አቤል በድጋሚ ሠርቶ የሰጣቸው የጥናት ጽሑፍ ነበር ።

" ይኸውልህ " አሉት ፣ የጽሑፉን መግቢያ ዐልፈው መሐል ገጾቹን እያሳዩት ፣ " ከዚህ እስከዚህ ያለው ጽሑፍ የተቀዳው ፣ 'እንቲ ዱሪንግ' ከሚለው የኤንግልስ መጽሐፍ ውስጥ ነው ። ሐሳቡን ማለቴ እንዳይመስልህ ፤ ዐረፍተ ነገሩን ቀርቶ ቃላቱን እንኳ አልቀየረውም ። ከመስላቸትም አልፎ ትምህርቱን የመጥላት ምልክት ነው ። አቤል እንዲህ ዐይነት ተማሪ አልነበረም ። እንዳለች ከመጽሐፍ ቀድቶ ማምጣት ቀርቶ ታላላቅ ምሁራን በደረሱዋቸው ታላላቅ ሥራዎች ላይ የሚያቀርበውን ሐሳብ ለመፍታት እንኳ ያስቸግር ነበር ። እምና በእንዲት ዲያሎግ ሸንጡን ገትሮ ይዞን ዐሥራ አምስት ቀን ሙሉ እንዳንጫጫን ትዝ አይልህም ?! እኔ ያኔ እሱ ባነሣት ጥያቄ የራሱን ምሁራዊ ብቁነት ተጠራጥሬ እንደገና መጻሕፍት ሳገላብጥ የከረምኩበት ጊዜ ነበር ። አሁን ግን የዚያን ጊዜው አቤል አይደለም ። ችሎታው አለው ። ግን እንዳች ችግር ደርሶበታል ። ስለዚህ ችግሩ ከተገለጠ በኋላ ነው ትምህርቱን በሚገባ ሊያጠናቅቅ የሚችለው እንጂ ፣ አድበስብሰው ቢያሳልፉት ምንም ጥቅም የለውም ። "

እስክንድር የጥናት ጽሑፉን ወረቀት እያየ ፈዞ ቀረ ። እንዳለ የመጽሐፍ ግልባጭ ነበር ። አቤል ይህን የጥናት እርዕስት ወስዶ እንደገና እንዲሠራ ዮናታን በመከሩት ጊዜ ፣ መልሶ ወስዶ ሊያምጥበት ዐሥራ አምስት ቀን ያህል እስቀመጠው ። በመጨረሻም ከጠቀሱት መጽሐፍ ውስጥ እንዳለ ገልብጦ ሰጣቸው ። አያውቁም ብሎ አልነበረም ይህን ያረገው ፤ ከእጁ እንዲወጣለት ብቻ እንጂ ።

" እና አሁን ትምህርቱን እርም ብሎ ከመተዉ በፊት እንዲያቋርጥ በዘዴ ብንመክረው " አሉ ዮናታን ።

" ለዚህማ ምን ምክር ያስፈልገዋል ? " አለ እስክንድር ። " እሱ ራሱ ለመተው በቋፍ ነው ያለው ። "

" የለም ። እሱ የራሱን ውሳኔ ወስዶ ከተወማ ፣ አሁን ባለበት ሁኔታ ፣ ለእንጁም ለሁሌም ነው የሚተወው ፤



ጭራሽ ወደ ትምህርት ፊቱን አይመልስም ። ምክሩ የሚያስፈልገው ጤናማ በሆነ አመለካከት ትምህርቱን አቋርጦ አእምሮው ሲረጋጋ እንዲመለስበት ነው " አሉና ዮናታን ፣ እንድ ሐሳብ ድንገት ስለ መጣባቸው ፣ " ደግሞ አይምሰልህ ፤ ለማቋረጥ ድፍረት የሚኖረው አይምሰልህ ። ማለቴ ፣ ትምህርቱን ለመተው ድፍረት ባያጣም ዩኒቨርስቲውን ለመልቀቅ ድፍረት አይኖረውም " አሉ ።

" አልገባኝም " አለ እስክንድር ፣ ግር ብሎት ።

" በዐይኑ ያፈቀራት ልጅ ያለችው እዚሁ ግቢ ነው አላልከኝም ? "

" አዎ ፣ መቼም በግምቴ ይመስለኛል ። "

" ታዲያ እሷ ያለችበትን ግቢ እንዴት ችሎ ይለቃል ?!"

" እ ? "

" እንዳው ስታስበው ችሎ እሚለቅ ይመስልሃል ወይ ?"

" እህ ! . . . "

## ምዕራፍ ዐሥር

"ራስ ግሪል" የምትል ዓርማ ከዶረቱ ላይ የለጠፈ አስተናጋጅ፣ "ምን ልታዘዝ?" ሲል ከፊቱ መጥቶ ቆመ።

"እስቲ ቀዝቃዛ ቢራ" አለ ለማ ሰዓቱን እየተመለከተ ።

ዘጠኝ ከዐሥር ሆኖ ነበር ። 'ቦታው ጠፍቷት ይሆን እንዴ?' ሲልአሰበ፣ ምናልባት ዋናው ራስ ሆቴል ሔዳ እን ደሆን በሚል ግምት ። ነገር ግን ቀጠሮአቸውን በደንብ ያስታውሳል ። "ራስ ግሪል፣ ቅዳሜ በዘጠኝ ሰዓት" ሲላት፣ ጥቂትም ግር ሳይላት ነበር፣ ቀጠሮውን የተቀበለችው ።

'እንዴት አባቷ ቀጠሮው ቦታ ቀድማ አትገኝም?' የሚል ትምክህት ተሰማው ። ለጊዜው ተፈላጊ በመሆኑ ዐሥር ደቂቃ አሳልፎ የመጣው ቀድማ ትጠብቀኛለች በሚል ግምት ነበር ።

አሳላፊው ቢራውን ይዞለት መጣ ።

ለማ የቢራውን ቅዝቃዜ ለመገመት ጠርሙሱን በእጁ ጠበቅ አርጎ ከጨበጠ በኋላ አስከፈተ ። ሁለቴ ተጉንጭቶ ግማሽ ወገቡ ላይ አደረሰው ። የዕለቱ ወበቅ ሌላ ጉዳይ ነበር ። ኮቱን አወለቀ ። ከፊት ለፊቱ በከረባት ታንቀው የተቀመጡትን ወፍራም ሰውዬ ተመልክቶ፣ ሙቀት በመቋቋም ችሎታቸው ተደነቀ ።

ደቂቃዎቹ ወደፊት ተራመዱ ። ወፈር ያለች አጭር ልጅ ግን ብቅም አላለች ። አምስት ደቂቃ ሳይሆን ሙሉ ቀን የጠበቃትን ያህል ስሜቱ ተቁነጠነጠ ። ከአሁን በፊት ሁለት ጊዜ ሴቶች በቀጠሮ ቀጥተውታል ። ብዙ ሴቶች በመጀመሪያ ቀጠሮ ላይ እንዲህ እንደሚያረጉ ያውቃል ። ርካሽ እንዳይመስሉ የሚያደርጉት መፍጨርጨር ነው ። ይሁን እንጂ በቤት ልሔም ሲቀጣ አይፈልግም፣ መቅረት ሳይሆን መዘግየቷ ራሱ ምን ሲደረግ!

ቢራውን ጭልጥ አድርጎ ተነሥቶ ሊሔድ ፈለገ ። ነገር ግን እግሩን አላንቀሳቀሰም ። ነገር የጠፋው የዚያች የሠርግ ዕለት ነው ። ' አፌን ካጠፋሁ አይቀር ፣ ማስጨረስ አለብኝ ' የሚል ስሜት አደረበት ። የቤቱ ልሔም ግምት ልክ ነበር ። የተዘበራረቀ ስሜቱን ተመርኩዞ መከረኛ ጎሊናው የፈዘ ጥርሱን እያሳየ ከተፍ አለበት ። እንደ ገና ሁለት ለማዎች ሙግት ጀመሩ ።

' ምነው ቢቀርብህ ፣ ለማ?'

' ምኑ? '

' መዝቀጡ ፣ ያለቦታህ መዋሉ ! '

' መምህር የሚያስተምራትን ኮረዳ ቢያወጣ መዝቀጥ አይደለም ። ማነው እንዲህ ያለው? ማነው እንዲህ ዐይነት ሕግ የደነገገው ? አላየሁም ። አላነበብኩም ። እስካሁን ጅል ሆኜ ቆይቻለሁ ። ቁጥብነቴ በሕይወቴ ላይ ምን ጨመረ ልኝ ? ፍራፍሬ ቀርቦ አትብሉ ብሎ የሚያግድ ሕግ ካለ አል ቀበልም ። '

' መታገድ ሳይሆን መቆጠብ ያስፈልጋል ። '

' መቆጠብ ! መቆጠብ! ከአመጋገብ መቆጠብ! ከወሲ ባዊ ግንኙነት መቆጠብ ! ቁጥብነትን የሰውነት መለኪያ ያደረገው ማነው ? '

'አመዛዝን እንጂ ! ቁጥብነት ከሌ ለማ የሰው ልጅሕይ ወት ከእንስሶች ባልተለየ ነበር ።እንደእንስሶች በተገናኙበት መዳራት ፣ ባገኙበት መብላት መጠጣት ፣ በደረሱበት መተ ኛት ፣ ያገኙትን ማንሣት ፣ የጠሉትን መጣል ቢሆንማ ፣ ታላቅ የስሜት ግጭት ስለሚፈጠር ፣ የሰው ልጅ እርስ በርሱ ይተላለቅ ነበር ። ቁጥብነት በስሜት ሳይጋጩ ተባብሮ መኖ ርን በሚፈልግ ኅብረተሰብ ውስጥ ያለ ማኅበራዊ ሕግ ነው . .

' እና ፣ የአካባቢውን ሕግ ብጥስ ምን ይመጣብኛል ? '

' መተፋት ነዋ ! በኅብረተሰብ መተፋት ፣ መናቅ ፣ ከአውሬ ወይም ከእንስሳ መቆጠር ! መዝቀጥ !'

ለማ ድንገት ዘወር ቢል ፊቱን ከሕንፃው ጋር ከተሠራው ረዥም የቁም መስታወት ውስጥ ተመለከተ ። በውን ከጠላቱ



ጋር እንደሚሟገት ሰው ግንባሩ ተኮማትሮ ፣ ፊቱ የውስጥ ስሜቱን በግልጽ ያሳይ ነበር ።

' ከጎሊና የበለጠ ጠላት ምን አለ ? '

' አዎ ! ጠላትህ ነኝ ። ከሰውነት ውጭ ስትሆን ገና የባሰ ጠላትህ እሆናለሁ ። ሕይወትህ የአንዱ መሆን አለበት ፤ የውጭያዊ እንተነትህ ወይም የውስጣዊ እንተነትህ! '

' እፍ ! በቃኝ ሙግት አልፈልግም ! '
' እንዴት ? ''

' እንዲህ ነዋ ! ትዳር መመሥረት አልቻልኩም ። ምን ተይዞ ጉዞ ! '

'እና የአሁኑ ተግባርህ ለዚህ ሁሉ መካካሻ ነው ?!
" ከረሜላ ካልተገዛልኝ ብርጭቆ እሰብራለሁ " እንደሚል ሕፃን ፣ ወይም ደግሞ ፣ " የሲኒማ ፍራንክ ካልሰጠሽኝ እናቴ አይደለሽም ! " ብሎ ደሀ እናቱን እንደሚያስፈራራ ጎረምሳ ሆንክ ! ነው ፣ አይደለም? አልቤርጎ እየኖሩ ክብር የለም ። "

' ምንም ሆነ ምን በቁጥብነት ራሴን አላስርም ። ካለመ ቆጠቤ የሚቀርብኝ ክብሬ....'

' ለማኅበራዊ ችግር መፍትሔው ፣ ማኅበራዊ ትግል እንጂ ካሉበት በታች ሆኖ መገኘት አይደለም !'
' እፍ ! '

በቀይ እጅጌ-ጉርድ ቀሚስ ደምቃ ጽጌረዳ አበባ የመሰለች ኮረዳ ወደ ምግብ ቤቱ ስትገባ በተመለከተ ጊዜ ፣ ሲወተውተው የቆየው ጎሊናው የጓሊት ፈረጠጠለት ። „ጉሽ ፣ ገላገልሽኝ'' በማለት ዐይነት ለማ በረዥሙ ተንፍሶ ተመቻችቶ ተቀመጠ ። ነገር ግን የውስጥ ስሜቱን በፈገግታ ሊገልጽ አልፈለገም ። ቅሬታውን በሚያንጸባርቅ አስተያየት ተቀበላት ።

" ሶሪ ፤ ብዙ አስጠበቅሁህ አይደል?" አለችው ቤተ ልሔም ፣ ቁና ቁና እየተነፈሰች ። " አፍ አገኝሃለሁ የሚል ግምት አልነበረኝም ። ተስፋ ቆርጬ ነበር "

እንዳለችውም ፣ ገና በሩን ስትገባ ዐይኖቿ ከወንዶቹ መሐል አነጣጥረው ለማን ባገኙት ጊዜ ፣ ልቧ በደስታ ከው ስጧ ዘሎ ሲወጣ ምንም አልቀረው ። በመዘግየቷ ጥፋተኛነት እየተሰማት ነበር የቀረበችው ። ለማ መቆጣት አልቻለም ። መላ ሰውነቷን የተርከፈከፈችው ሽቶ መዓዛ ስሜቱን አደን ዝዞት ፣ ቅሬታውን እንዲውጥ አስገደደው ።

“ ምንም አይደለም ፣ በይ ቁጭ በይ ። ግን ምነው ? ” አላት ፣ ግንባሩን አላልቶ ሰዓቱን እያየ ። ዘጠኝ ተኩል ሆኖ ነበር ።

“ አንድ ደረቅ ባለታክሲ አጋጥሞኝ ’ ኮ ነው ” አለች ቤተ ልሔም ፣ ከአቀማመጧ እየተመቻቸች ። “ እኛን ውስጥ አጉሮ ነዳጅ ለመቅዳት አይገተር መሰለህ ? ”

“ጥላችሁት በሌላ ታክሲ አትሔዱም ነበር ?! ” አላት ፣ በመቆርቆር ስሜት ።

“ መጥፎ አካባቢ ነበራ ! ታክሲ እንደ ልብ የማይገኝበት ። ”

አንድ አሳላፊ መጥቶ ከፊታቸው ቆመ ።
“ የብርቱካን ጭማቂ አለ ? ” ስትል ጠየቀች ።
“ ምነው ? ቢራ ጠጭ እንጂ ” አላት ለማ ።

“ ኤ ፣ አልጠጣም ። በዚህ በፀሐይ ቢራ ራሴን ይፈል ጠዋል ” አለችውና ፊቷን ወደ አሳላፊው መልሳ ፣ “ ጭማ ቂውን አምጣልኝ ” ስትል አዘዘች ።

“ በል ለእኔም ቢራ ድገመኝ ” አለ ለማ ።

ፀሐዩን ፈርታ ሳይሆን ቢራ እጅግም ነች ። ቦርጭ ያወጣል እያሉ ጓደኞቿ ስለሚያስፈራሯት ትታዋለች ። ሌላው ችግሯ ደግሞ ፣ ቢራ ከጠጣች ሽንት ቤቱ ለእሷ ብቻ መለቀቅ አለበት ። በጉሮሮዋ ከመውረዱ ፣ ሽንቷ ይመጣባ ታል ። ውስኪ ሲሆን ነው ደስ ብሎአት የምትጠጣው ።

“ውይ ! ምን ዐይነት ቃጠሎ ቀን ነው ?” ስትል ጨዋታ ከፈተች ። ስስ ተካፋች ሹራቧን አውልቃ ትከሻና ደረት



ዋን ገላልጣ ነበር-የተቀመጠችው ። የቆዳዋ ጥራት በሞግዚት ተንከባክበው የያዙት እንጂ በዩኒቨርስቲ ትምህርት የማቀቀ አይመስልም ።

“ ጉድ ነው እንጂ ” አለና ለማ ወበቁን በማጋነን ዐይ ነት ፣ ወዲያው መለስ አርጎ ፣ “ እኔስ ቦታውን ወይም ቀጠ ሮውን ረስተሽዋል ብዬ ነበር ” አላት ።

አሳላፊው ቢራውንና ጭማቂውን አቅርቦላቸው ተመ ለሰ ።

“ እንዴ ! ምን ማለትህ ነው ? ” አለችው ፣ ልቡ ውስጥ ገብታ ለመጉዝጉዝ ዐይኗን እያስለመለመች ። “ እንዴት እረሳዋለሁ ?! ”

እውነትም ቤተ ልሔም አትረሳም ። ከዚህ ቀደም የም ስት ቦይፍሬንዶቿን ቀጠሮ እያወጣች እያወረደች ስታማርጥ ውላ ፣ የአንድ ትልቅ መሥሪያ ቤት ኃላፊ ወደ ሆነው ዘንድ ወስና ብትሔድ ፣ ግማሽ ሰዓት በመዘግየቷ ፣ ወፍራም ገቢ ያስገኝልኛል ብላ የተማመነችበትን የክረምት ሥራ ሳታገኝ ቀርታለች ።

ከዚያን ዕለት ወዲህ ቤተ ልሔም ቀጠሮ አትረሳም ። እንዳውም ጥቅም ያለበት ዐይነት ከሆነ ዝግጅቷን የምትጀም ረው ገና በዋዜማው ነው ። ልብሷንና የሽቶዋን ዐይነት ስት መራርጥ ታመሻለች ። አነጋገሯን ፣ ቅልጥፍናዋን ስታስብ በት ታድራለች ። ባዶ የፍቅር ዜማ እያንጎራጎረ የሚጠብ ቃትን ወንድ አውቶቡስ ፌርማታ ጥግ ገትራ ሲኒማ ቤት የምትዝናናውን ያህል ፣ መልካም ዝና ወይም ገንዘብ ያለውን ላለማስጠበቅ በጥድፊያ ሁለት ታክሲ የምታስቆምበት ጊዜ አለ ። ያም ሆነ ይህ ፣ ያን ‘ ሴታ አልያዘላትም ። ስለዚህ እማ ይደገም ዕድል አመለጣት ። ሰውዬውን በሌላ ቀን አገኘው ይሆናል ብላ ብታስብም ከአዲስ አበባ መንገዶች አጣችው ።

ቤተ ልሔም ከቀጠሮ ይበልጥ የማትረሳው ሌላው ነገር የዛሬ ዓመት ‘ ፍሬሽሟን ’ ሆና የደረሰባት ነው ። ፈገግታ እማ ይለየው አንድ ወጣት የኢኮኖሚክስ ሌክቸረር ነበር ። ታዲያ ትምህርቱ እየከበዳት ሔደና በሱ ኃይል ለማለፍ ፈለገች ።

በመጀመሪያ ተማሪዎቹን ዘፍ ብሎ እንደሚያነጋግርና ፊት እንደማይነሣ አጠናች ። ቀጠለችና ጥያቄ ሲጠየቅ መመለስ እንደማይሰለች አስተዋለች ። ከዚያ በኋላ በሙሉ ልብ ተገፋፍታ ትከታተለው ጀመር። ብቻዋን የምትሆንበትን አጋጣሚ እየፈለገች የምታውቀውንም የማታውቀውንም አስረዳኝ እያለች የልቡን ትርታ ማዳመጥ ቀጠለች ። በኋላ አንድ ቀን ሳያስበው አንዱን ቴዎሪ ሊያስረዳት ከቃላቱ ጋር ሲታገል ፣ “ እንዴት በዚህ ዕድሜህ ማስትሬት አገኘህ ? ! አለችና በጣፋጭ ዜማ አቋረጠችው ። ምን እንደሚመልስላት ግራ ገባው ። እሷ ግን ከዚያን ዕለት ወዲህ ነገሩ ሠመረላትና ልቡ ጓዳ ሰተት ብላ ገባች ። አጠመድኩት ብላ ፎከረች ። ከማለፍ ጉጉቷ አልፋ “A” በጄ ገባች ብላ ተማመነች ።

በእርግጥም ሌክቸረሩ ከዚያን ቀን ጀምሮ ለቤተ ልሔም ተማረከላት ። ከደንበኞቿም አንዱ ሆነ ። ይሁን እንጂ የፍቅሩን አመጣጥ በኮስታራ መንፈስ ነበር የተቀበለው ። ገና እንደ አጀማመሩ ሰሞን እንዳትከፋ በማሰብ ፣ ለዘብ አድርጐ ፣ “ የሚያጠግብ ፍቅርና ትምህርት በአያያዙ ያስታውቃል ” እያለ እንደ ቀልድ ሲነግራት ካንጀቱ አልመሰላትም ነበር ። ይልቁንም ፣ “ እስቲ እንተያያለን ” እያለች ቀልዱን በቀልድ መለሰች ። በኋላ ፣ ቀስ እያለ ፣ “ ፍቅርና ትምህርት ለየብቻ ናቸው ” ማለት ጀመረ ። አሁንም እውነት አልመሰላትም ። እና ወደ ሁለተኛ ዓመት ተንጠልጥላ በማስጠንቀቂያ እንድ ታልፍ ያደረጋት የኢኮኖሚክሱ “D” መሆኑን አትረሳውም ። እንዳውም ፣ “ ደርሶ ፈረንጅ ! አትል ሲሪየስ ልሁን ባይ !” እያለች መስከረም እስኪጠባ ረግማዋለች ። “ እንደ ጂሰስ ሐቀኛ ልሁን ሲል የፕሮቤሽን መሥዋዕቱ አደረገኝ !” እያለች ስታማው ሴሚስተሩን አጋምሳለች ።

ታዲያ አንዳንዴ ያ ሁኔታ ትዝ ሲላት ፣ “ ለማም እንደሱ ይሆንብኝ ይሆን ?” እያለች ዐልፎ ዐልፎ ማሰቧ አልቀረም ።

ለማ ፣ “ ያንተን ቀጠሮ እንዴት እረሳዋለሁ ?” ሲባል በርግጥ ደስታ ተሰምቶታል ። ነገር ግን አንድ የሆነ ነገር እንደ ከነከነው ያስታውቅ ነበር ።

“ የምልሽ ፣ የሰርጉ ዕለት ቀጠሮ የተሰጣጠነው በግርግር መሐል ስለሆነ ሊደናገርሽ ይችላል ብዬ ነው ። ከዚያ



በኋላ ደግሞ ክፍል ... ” አለና ፣ ሊናገር የፈለገውን ቶሎ ብሎ በውሸት ሳል ሸፋፍኖ አሳለፈው .....

ለማና ቤተ ልሔም ቀጠሮ የተሰጣጡት የሰርጉ ዕለት ነበር ። በሰባተኛ ቀናቸው መገናኘታቸው ነው ። በዚያ መሐል በነበሩት ቀኖች ውስጥ ለማ የሚያስተምረውን የትምህርት ዐይነት ቤተ ልሔም በሳምንት ሦስት ፒርየድ መከታተል ሲኖርባት ፣ የሰኞውን ክፍል-ጊዜ ብቻ ገብታ ፣ ሁለቱን ክፍል-ጊዜ አልገባችም ነበር ። ለማ ሊናገር ፈልጐ ከአፉ የመለሰው ይህን ጉዳይ ነበር ። ነገሩ አላማረውም ። ገና ምኑም ሳይጀመር መቅረት ካመጣችማ ፣ ግንኙነታችን ከጠበቀ ጭራሽ ሳትገባ ነው የሚል ሥጋት አድሮበታል ። ሆኖም በዚች ዕለት ያንን ዐይነት ችግር አንሥቶ በሁለቱም ዐይን ውስጥ የሚንቀለቀለውን የወሲብ እሳት እንዳያጠፋ ስለፈራ አደባብሶ አለፈው ።

ቤተ ልሔም ሁለቱን ክፍል - ጊዜ ያልገባችው ሆን ብላ ነው ። ከቀጠሮ ቀን በፊት ደጋግሞ መተያየቱ ሁኔታውን ሊያበላሸው ይችላል የሚል ሥነ - ልቡናዊ ግምት ስላደረባት ፣ እንዴ እስኪያወጣትና ጅማሬው መልክ እስኪይዝ ድረስ ከለማ ጋር ላለመተያየት ፈልጋ ነው ። ለማ “ ክፍል ... ” ብሎ ገና ሲጀምር ነገሩ ቢገባትም ቅሉ ፣ እሷም በዚች ደቂቃ እንዲነሣ የማትፈልገው ጉዳይ ስለሆነ እንዳልሰማች ሆና አሳለፈችው ።

“ ምንስ ቢሆን ያንተን ቀጠሮ እንዴት እረሳዋለሁ ? ” አለችና ፣ ደማቅ ፈገግታ አሳይታው ዐይኖቹ ላይ ተክለቻቸው ፤ እነዚያ የሰርጉ ዕለት ምላሱን ያሳሰሩት ዐይኖችዋ አሁንም አዩት ። ‘ ለመሆኑ ፣ ኃይለኛ ዐይን እንዳላት ለእሷም ይታወቃት ይሆን ? ’ ሲል ተደነቀ ። ለአስተያየቷ ግን ምንም መልስ አልሰጣትም - ደካማ ፈገግታ ብቻ !

“ ስለ ዘገየሁብህ ቅሬታ ተሰምቶህ እንደሆን እክማለሁ ” አለችው ።

“ ምን ዐይነት ካሣ ! ” አላት ፣ የልቡ ቁልፍ ፍጹም ላልቶ እየተበረገደ ።

" ካሣ ነዋ ፤ የተጠየኩትን ። "

ከአቀማመጡ ለመመቻቸት ዳሌዋን ነቅነቅ ስታረገው የእሱም ልብ አብሮ ከቦታው ተነቃነቀ ። እንደ አውሬ ተሸ ክሞአት ቢወጣ በወደደ ነበር ።

በድንገት አንድ ሰው ወደ ሆቴሉ ሲገባ በተመለከተ ጊዜ ሁለቱም ተደናገጡ ። አንድ የዩኒቨርስቲ ባልደረባ ነበር ። ከለማ ጋር በዐይን ይተዋወቃሉ ። የት ክፍል እንደ ሚሠራ ግን አያውቅም ። ከሩቁ ሰላም ብሎአቸው ፤ ሰው ፈልጎ እንዳጣ ዐይነት ወደ ኋላው ተመለሰ ።

አጓጉል ቦታ እንደሆኑ ለማ የተሰማው ይህን ጊዜ ነበር ። ቀጠሮው ራሱ የመዋከብ ዐይነት ስለ ነበር ነው እንጂ ፤እንዲህ ብዙ ሰው የሚገባበት ቦታ ለሽምቅ ውጊያ አመቺ እንዳልሆነ ቀድሞም አላጣውም ነበር ።

" ብንሔድ ምን ይመስልሻል ? " አላት ፤ ያወለቀውን ኮት መልሶ እየለበሰ ።

" እንሒድ እንዴ ? " አለችው ፤ ለመቃረን አስባ ባይ ሆን ፤ መልስ መስጠት ስላለባት ብቻ ።

" አይመስልሽም ? " አላት ፤ ቢራውን ለመጨረስ ከተ ጎነጨ ፤ በኋላ ሒሳቡ እንዲመጣለት እንዘዘ ።

እሷም ጭማቂውን ግማሹን ትታ ሹራቧን አጥልቃ ተነሣች ። ሒሳቡን ከፈለና ወጡ ።

ታክሲ ተሳፍረው ወደ ቴዎድሮስ አደባባይ ሲያመሩ ምንም ቃል አልተለዋወጡም ። ወዴት እንደሚወስዳት አል ነገራትም ። እሷም አልጠየቀችውም — ብቻ ጸጥ ብሎ ወደ መሐል አራዳ !

" ቤቱን ላሳይሽ ብዬ ' ኮ ነው " አላት ከታክሲ ከወ ረዱ በኋላ ።

" በደስታ ! "

ትንቀኛለች በሚል ፍራቻ መኖሪያው አልቤርጎ መሆ ኑን ሊገልጽላት አልፈለገም ነበር ። ታክሲ ውስጥ ሆኖ ሁኔ



ታውን አስልቶታል ። ለጊዜው እንደ ተከራየው አልቤርጎ አስመስሎ ሊያስተዋውቃት አሰበ ። ነገር ግን ክፍሉ ውስጥ በርካታ የግሉ ዕቃዎች ስላሉበት የማያዋጣ ሐሳብ መሆኑ ገባው ።

በሲኒማ ኢትዮጵያ ጀርባ ታጠፉ ።

" ግን እዚህ አካባቢ ነው እንዴ ሰፈርህ ? "

" አዎን ! "

" ታድለህ ! መሐል አራዳ ! "

' መታደል አልሽው ? ' አለና በልቡ ፤ " እስቲ ገምቺ ፤ የትኛው ይመስልሻል የኔ ቤት ? " አላት ፤ በአንድ መልኩ በቀልድ ፤ በሌላ መልኩ ደግሞ ስሜቷን ለመገመት አስቦ ።

ግራ ቀኝ የምታየው ቡና ቤት ብቻ ነበር ።

" እኔ እንዴት ዐውቀዋለሁ ? " አለች ፤ ይኸ ነው ለማ ለት ፈርታ ።

" እንዲያው በግምትሽ ? " ሲል አፋጠጣት ።

በስተግራዋ በኩል አንድ አፓርትመንት አየችና ፤ "ምና ልባት እዚህ ውስጥ ? " አለችው ።

ማቀና አፓርትመንቱን ዐልፎ ወደ ሌላ ግቢ ይዞአት ገባ ። በጓሮ በር ስለ ገቡ ምን ሆቴል እንደሆነ ልታውቅ አልቻለችም ።

" ይኸውልሽ ፤ ቤት ለመከራየት ከተመዘገብኩ ሦስት ዓመት ሆነኝ " አላት ፤ በሩን ከፍቶ ወደ ውስጥ ሲገቡ ።

እንደ ገባች አጠገቧ ያገኘችው ደረቅ ወንበር ላይ ልትቀመጥ ስትል ፤ ለማ ክንዷን ይዞ ፤

" እረ አልጋው ላይ ተቀመጭ " አላት ።

" አይ ፤ ነውር ነው " አለች ፤ ለመግደርደር ያህል ።

" እባክሽ ተይ ! ነውር ድሮ ቀረ ! " አላት ፤ በልቡ ' ነውር ብትፈሪ መጀመሪያውኑ መቼ መኝታ ክፍሌ ድረስ ትገቢ ነበር ? ' እያለ ።

መኝታው ላይ ተመቻችታ ከተቀመጠች በኋላ ፣ የክፍሉን ዙሪያ ገብ መማተር ጀመረች ። ግድግዳው ላይ ሦስት ሥዕሎች ተለጥፈዋል ። ንብረቶቹ ለቁጥር አያስቸግሩም ። ሁለት ደረቅ ወንበሮች ከአንዲት አነስተኛ ጠረጴዛ ጋር ፣ እናቱ ላይ የጉዞ ሻንጣ የተሰቀለበት አንድ ቁም ሳጥን ፣ መኝታውና አጠገቡ ያለችው ኮሞዲኖ ፣ እንዲሁም ሙሉውን በመጻሕፍት የተገጠገጠ አንድ መደርደሪያ ናቸው ።

“ ምግብ የት ትበላለህ ? ” አለችው ፣ ከልቧ አዝና ።
“ ሆቴል ነዋ ! ” አላት ፣ ከአፉ አምልጦት ። ከአፉ ባያመልጠውም ሌላ መልስ አልነበረውም ።

ምንም ሳያስቀምጥ ወይም ሳያነሣ ፣ እንዲያው ክፍሉ ውስጥ በሽሚዝ በመንጕራደድ ላይ ነበር ።

ቤተ ልሔም የቤቱን አኳኋን እየተመለከተችና የለማን አኗኗር በልቧ እየገመተች ኀዘን ስለ ተሰማት ፣ የወሲብ ስሜቷ እየቀነሰ ፣ የእኅትነት ዐይነት አስተያየቷ እየጐላ ሔዶ ፤ ብርሃን ሲረጭ የቆየው ፊቷ መዳመን ጀመረ ።

ቤተል ሔም ምቾት ትፈልጋለች ። የስሜት ሕዋሳቷ ከላይ እስከ ታች የሚግሉት ምቾት ስታገኝ ብቻ ነው ። ወንድ ልጅ የሚያሸንፋት ፣ ልቧን ጥሶ የሚገባው ምቾቷን የጠበቀላት እንደሆነ ነው ። አሁን የተሰማት ለእንገቱ ማስገቢያ እንኳ መሥራት አለመቻሉ ነው ። ግን እሷ ከለማ ቤቱን ፣ ውበቱን ወይም ገንዘቡን አይደለም የምትፈልገው ። ከእሱ የምትፈልገው ማርከ ብቻ ነው ። ድህነቱ ማርከ ከመስጠት አያግደውም ። ነገር ግን እሷ ከወላጆቿ ጋር በምትኖርበት ጊዜ አሁን ለማ ካለበት በእጥፍ ምቾት ትኖር እንደ ነበር ስታስታውስ ከልቧ አዘነችለት ።

“ ታዲያ ምን ይምጣልን ? ” አላት ለማ ፣ የሚያቀርብላት ነገር ግራ ገብቶት ። ለግድያው ምንም ዝግጅት አላደረገም ነበር ። ከቡና ቤቱ አልኮል ማስመጣት የታየው ገና አሁን ነው ።



“ ምን ? ከየት ? ” አለችው ፣ ግር ብሎአት ።
“ የሆቴሉ ቡና ቤት አለ'ኮ ! የምንጠጣው ነገር ላስመጣ ? ምግብም ከፈለግሽ ሊመጣ ይችላል ።”

“ አሁን ምንም አልፈልግ ። በኋላ ስንወጣ ይሻላል ።”
“ እውነት ? ”
“ እውነት ! ”

የመስኮቱን መስታወት ከፍቶ ዕንጨቱን ዘጋው ፤ መብራቱን አበራ ፤ በሩ በቅጡ መቆለፉን አረጋገጠ ።

“ ሽንት ቤታችሁ የት ነው ? ” አለችው ቤተ ልሔም ፣ አዝማሚያው ስለ ገባት ቅድመ ዝግጅቷን ለማጠናቀቅ አስባ ።

“ ነይ ላሳይሽ ” አላት ፣ የተበላሸው የሆቴሉ ሽንት ቤት በሐሳቡ ታይቶት ! ልቡ እየተሸማቀቀ ። መከልከል የማይቻል ሆኖበት ነው እንጂ ፣ ከአጠገቡ እንድትነቃነቅ አልፈለገም ነበር ። በወጣችበት ሸልካ የምታመልጠው መሰለው ።

“ ሩቅ ነው እንዴ ? ” አለችው ፣ በጣቱ ወደሚያመለክታት አካባቢ እያየች ። እሷ የገመተችው ከመኖሪያ ክፍሉ ጋር ባይያያዝም እንኳ አጠገቡ ይሆናል ብላ ነበር ።

“ አይዞሽ ! በዚህ በኩል ሰው አይመጣም ” ብሎ አጽናንቶ ላካት ።

ከሽንት ቤት እስክትመለስ ጫማና ካልሲውን አውልቆ ጠበቃት ።

“ እህስ ፣ ሰው ነበር ? ” አላት ፣ የፍርሀት ፈገግታ እያሳየ ።

“ አልነበረም ” አለችውና ፣ አልጋው ላይ ሔዳ እንደ ሕፃን ልጅ ዘፍ አለች ። እጆቿን ይዞ ወደ ደረቱ ሳባት ። አንገቷን ጭምቅ አርጐ አቅፎ ከንፈሩን ከንፈሯ ላይ ሊያሳርፍ ሲል እመር ብላ ተስፈንጥራ አመለጠችው ።

" ምነው ? " አላት ፣ ደንገጥ ብሎ ። በወሲብ ግለት በበራው ላብ መንቸፍቸፍ ጀምሮአል ።

" ቆይ ሊፕስቲኩን ልጥረግልህ " አለችው ።

እሷ ከቦርሳዋ ሶፍት አውጥታ የከንፈሯን ቀለም ስትጠርግ እሱ በነጠላ ጫማ ሒዶ በሩን ቆልፎ ተመለሰ ። የልቡ ትርታ ፍጥነት ለራሱም አስፈራው ። ትልቅ ተራራ የወጣ ያህል ነበር - ሽቅብ ሽቅብ የሚነጥረው ።

ቀሚሷን ስታወልቅ ምራቁን በደረቀ አፉ አሁንም አሁንም እየዋጠ ለአፍታ ያህል በልብሶቿ ጥራት ተደነቀ ። ከጡት መያዣዋ ጀምሮ ያደረገቻቸው ልብሶቿ ሁሉ አዲስ ነበሩ ። ይሁንና ይህን በሰፊው ለማድነቅም ሆነ ለመመራመር ጊዜ አልነበረውም ።

ገና አንድ ጉኗን አልጋው ላይ እንዳሳረፈች በስሜት እሳት እጋለ ሰውነቷ ውስጥ አስገብቶ እቅፉ ውስጥ አቀለጣት።

" መብራቱን ሳጥፋው ? " አላት ፣ በጣም በደከመ ድምፅ ።

" እንዳሻህ " በማለት ዐይነት ትከሻዋን ነቀነቀች ። ስሜትና ወበቅ ስላፈኗት መተንፈስ አልቻለችም . . .

ሁለቱም በድካም ስመመናዊ እንቅልፍ አሸለባቸው ። ለማ በሰመመን በቀጥታ ወደ ዩኒቨርስቲው ተጓዘ ።

ያ ራስ ሆቴል ተቀምጠው ያያቸው ሰውዬ ይመስለዋል ። በስብሰባ መሐል ፣ " አጀንዳ ይያዝልኝ " እያለ ደጋግሞ እጁን ያወጣል ።

" እሺ ፣ አጀንዳህ ምንድነው? " ይለዋል የስብሰባው ሊቀ መንበር ።

" ከልጃገረድ ተማሪዎቻቸው ጋር ስለሚቀብጡ መምህራን ጉዳይ ነው " ይላል ሰውዬው ፣ መላ ሰውነቱን በብስጭት እያወራጨ ።

ለማ ፊቱ ቀልቶ ፣ በራው ላብ እንቸፍችፎ ፣ ያጋለጠው ይመስለዋል ።



አንድ ተማሪ ደግሞ እጁን አውጥቶ ለሰውዬው ድጋፍ ይሰጣል ። ይህ ወጣት ፣ ለማ ክፍል ውስጥ በጣም የሚያደንቀውም ፣ የሚፈራውም ጠንካራ ተማሪ መስለው ።

" አዎ ! እንዲያውም ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ አጀንዳ ነው " ይላል ተማሪው ገንፍሎ ።

" እሺ ፣ በል አጀንዳህን አብራራው " ይላል ሊቀ መንበሩ ።

" በጣም የሚያሳዝን ተግባር ነው " ይላል ሰውዬው ፣ " በጣም የሚያንገበግብ ነው እንጂ ! " ይላል ተማሪው ተደርቦ ።

"በሥነ ሥርዓት ተናገሩ" ይላል ሊቀ መንበሩ በቁጣ ። ሰውየው ብቻ ንግግሩን ይቀጥላል ።

" በውነቱ በዩኒቨርስቲያችን ውስጥ እንዲህ ዐይነት ድርጊት ሲፈጸም ያሳዝናል ። የዩኒቨርስቲዉን ሥርዓት ማበላሸት ነው ። አንድ መምህር የሚያስተምራትን ተማሪ አውጥቶአት ፣ ' ግሪል ' ጋብዞአት ፣ ከሲኒማ ኢትዮጵያ በስተ ጀርባ ከሚገኝ አንድ ስውር መኝታ ቤት ይዞአት ሲገባ እኔ ራሴ በዐይኔ በብሌኔ አይቻለሁ ። ሊቀ መንበር ፣ ይህን ጉዳይ ከግላዊ ነጻነት አኳያ አይተው እንዳይዘጉት አደራ እላለሁ ። መታየት ያለበት በዩኒቨርስቲዉ ውስጥ ከሚያስከትለው የአሠራር ብልሽት አኳያ ነው ። እጅ ወዳጁ ላይ ሊሰነዘር አይደፍርም ። ደካማ ተማሪውን አቅፎ መምህርም ዐይኑ እያየ ፈተናውን አይጥላትም ። እንዲህ ከቀጠለ ደግሞ ዩኒቨርስቲዉ ውስጥ የሚያስፈልገው ጭንቅላት መሆኑ ቀርቶ ወሲብ ሊሆን ነው ። "

ለማ ፣ ላቡ በጀርባው ሲንቆረቆር እየተሰማው ብቸኛ ላለመሆን በዐይኑ ሚስተር ራህማንን ፍለጋ አዳራሹን ያማትራል ። ሚስተር ራህማን የሉም ።

" ተጨማሪ . . . . ያልተጠቀሰ ነጥብ " እያለ ተማሪው ጣቱን ያወጣል ። ሊቀ መንበሩ እንዲናገር ይፈቅድለታል ።

“ እዎ ! በተጨማሪም ጉዳዩ መታየት ያለበት ከዩኒቨርሲቲዉ የአሠራር ስልት ጋር ነው ። ዩኒቨርስቲዉ የተማሪዎችን የፈተና ወረቀት አርሞ ማርክ የሚሰጠው በስኬል ሲስተም ነው ። ስለሆነም አንድ መምህር የሚወዳትን ደካማ ተማሪ ከውድቀት ለማዳን የአንድ ጎበዝ ተማሪውን ዕድል እንደሚያበላሽ ፣ ምናልባት ባይጥለውም እንኳ ደረጃውን እንደሚቀንስበት አብሮ መታየት አለበት ። ”

“እሺ ፣ እንግዲያ ! ቤቱ ይነጋገርበት” ይላል ሊቀመንበሩ ። በአዳራሹ ውስጥ ታላቅ ማዕበል የተነሣ ይመስል - ሁሉም ጸጥ ረጭ ይላል ። የለማ ነፍስ በማዕበሉ ክፉኛ የተንገላታች ያህል ድምፅ የሌለው ጩኸት ትጮሃለች ። ውስጥ ውስጡን ብቻዋን ትንፈራገጣለች ።

ከረዥም ጸጥታና እርስ በርስ መፋጠጥ በኋላ ፣ ከተሰበሰቡት ተሳታፊዎች አንዱ ተነሥቶ ፣

“ አጀንዳ ያስያዙት ግለሰብ ጥፋተኛውን ሊጠቁሙን ይችላሉ ? ” ሲል ይጠይቃል ።

“ በሚገባ ነዋ ! ያው መሐላችሁ ፣ ለማ ካብት ይመር ” እያለ በጣቱ ያመለክታል ።

“ማ ? ! ” ብሎ ለማ ሲባርቅ ፣ በእርግጥ ድምፅ ስላወጣ ከሰመመናዊ እንቅልፍ ባንና ቤተ ልሔምንም አባነናት ።

“ ውይ ፣ ምን ነካህ ? ” አለችው ቤተ ልሔም ፣ በድምፁ ደንግጣ ።

“ እ ? ምንም ። ቅዠት ነው ” አላት ፣ ሥራ ሥሮቹ በጭንቀት ተገታትረው ፣ ፊቱን አጨፍግገውት ።

በጭንቀት በተጨናበሰው ስሜቱ ሲያያት ፣ አጠገቡ የተኛችው ከረዳ ሰይጣን መሰለችው ። እሷን ያቀፈበት እጁ ዘገነነው ፤ ቀስ ብሎ ክንዱን ከአንገቷ ሥር አወጣው ።

ቤተ ልሔም ደንግጣ ፣ ዐይኖቿን በሚያስፈራው የለማ ፊት ላይ አንከባለለቻቸው ።



“ በዚህች ደቂቃ የዐይኖቿ ውበት አልታየውም ።

“ ሁለተኛ እኔ ከማስተምርበት ክፍል እንዳትቀሪ ፣ እሺ ? ” አላት ፣ በመቆጣትም በማባበልም ዐይነት ። ምናልባት ሊያስጠረጥሯቸው ከሚችሉት መንገዶች አንዱን መጥረጉ ነበር ።

ቤተ ልሔም ምንም አልመለሰችለትም ። ለማ ዐይን ውስጥ ቀንዳቸውን አሹለው በተጠንቀቅ የቆሙ ሰይጣኖች ተመለከተች ። የሴትነት ኃይሏን የተሸከሙት ዐይኖቿ እኒህን ሰይጣኖች ማሸነፍ አለባቸው ። እናም ሰይጣናቱን በቆሙበት ብቸኛ መሣሪያዎቿ ዐይኖቿን — ዐይኑ ላይ ማንከባለሏን ቀጠለች ። እንዲያ ሲንከባለሉ የሚታዩ እንጂ የሚያዩ አይመስሉም ።

የዐይኖቻቸው ፍልሚያ የሁለቱንም ምላስ አሳሰረው ....

# ምዕራፍ ዐሥራዐንድ

"... እረ መላ በሉ ወዳጅ ዘመዶቼ
ዐይን አፋር ሆኘአለሁ ዐይን አፋር አይቼ

ሰላምታ አልሰጠኋት አላነጋገርኳት
በዐይን ብቻ እያየሁ ሦስት ወር ወደድኳት ...."

አቤል መተከዥያውን ሙዚቃ በለሆሳስ እያዜመ መኝታው ላይ ጋደም እንዳለ በዐይኑ ማፍቀር የጀመረበትን ጊዜ ርቀት ይለካ ጀመር ። ለወጉ ያህል ዐይኑን መጽሐፍ ላይ ተክሏል ፤ ነገር ግን በፊደላት ፈንታ በርካታ የትዕግሥት ምስሎች ነበሩ-መጽሐፉ ውስጥ የሚነበቡለት ። ሳያስበው እርሳስ ከኪሱ አውጥቶ ስሌት ጀመረ ።

'ሦስት ወር፣ ዐሥራ ሁለት ሳምንት፣ ዘጠና ቀን፣ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ስድሳ ሰዓት፣ አንድ መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ደቂቃ ፤ ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሴኮንዶች . . . እንዴት በዚህ ሁሉ ጊዜ አንዲት ቃል እንኳ ሳልተነፍስላት እቆያለሁ ? እንዴት ይህን ያህል ጊዜ በዐይን ፍቅር ብቻ እንገላታለሁ ?! አንድ ወንድ እንዴት ይህን ያህል ጊዜ ልቡን ለሴት ልጅ ይሰጣል ?' እያለ ሲያስብ፣ ድንገት ሳምሶን 'ጉልቤው' የመኝታ ክፍሉን በር ከፍቶ ዘው አለ ።

ከፀሐይ ላይ ስለ መጣ በስፖርት የዳበረው ጡንቻው ያብለጨልጭ ነበር ። አብዛኛውን ጊዜ በካኔቴራ ወይም በጉርድ ሸሚዝ ነው የሚውለው ።

"ተነሥ፣ ደብዳቤ መጥቶልሃል ። ስምህ ተለጥፎአል" አለው አቤልን ። አስገምጋሚ ድምፅ አለው ። ልማድ ሆኖበት፣ ረጋ ብሎ መናገር አይችልም ። ባይቆጣም የተቆጣ ይመስላል ። አቤልን ይወደዋል ። አቤል ግን አጸፋውን አይ

መልስለትም ፤ ሁሌ ዝም ነው ። ይህንን ጸባዩንም ቢሆን ሳም ሶን ' ጉልቤው ' የመኝታ ክፍል ጓደኛው እንደ መሆኑ መጠን ይረዳለታል ።

አቤልን ሁለት የዩኒቨርስቲዉ ወጣቶች በዐይን ፍቅረ ኛነቱ ሲያሙት ሰምቶ ፤ ካልተደባደብኩ ብሎ በግድ ነበር የተገላገለው ። ፈጽሞ ጥቃቱን አይወድም ።

" እውነትክን ነው ? " አለው አቤል ፤ የደብዳቤውን መምጣት በመጠራጠር ። የደብዳቤ መምጣት ማንንም ስለ ሚያጓጓ ተማሪዎች አንዳንዱን ሳይመጣለት ፤ " መጥቶል ሃል " እያሉ ልብ መስቀል የተለመደ ነበር ።

" እውነቴን ነው ። ይልቅ የፖስታ ማደያው ቢሮ ሳይ ዘጋ ቶሎ ሒድ " አለውና ሳምሶን በአክብሮት ፤ ዘሎ አል ጋው ላይ ወጣ ። መኝታው ላይ በርጋታ ወጥቶ አያውቅም ። የአልጋውን የጠርዝ ብረት ተመርኩዞ ሽቅብ ካልዘለለ አይ ሆንለትም ። ' ድብርትን ' ከሚያበሽቁት ነገሮች አንዱ ሳምሶን መኝታው ላይ ሲወጣ የሚሰማው የአልጋው መን ገጫገጭ ነው ። ተኝቶም ከሆነ ያባንነዋል ።

አቤል በነጠላ ጫማ በፍጥነት እርምጃ የመኝታ ቤቱን ደረጃ ወርዶ ፤ በሐሳቡ „ ማን ይሆን የጻፈልኝ ? " እያለ በጉጉት ከደብዳቤ መቀበያው ቢሮ ደረሰ ።

" የላኪው አድራሻ " በሚለው በኩል የተጻፈው የእ ናቱ ስም ነበር ። የአራተኛ ዓመት ትምህርቱን ከጀመረ ከቤ ተሰቡ ደብዳቤ መጥቶለት አያውቅም ነበር ። እሱም ልኮ አያውቅም ።

ደብዳቤውን ለማንበብ ተቻኩሎ በመጣበት ፍጥነት ተመልሶ ገና ከመኝታ ክፍሉ በር ላይ ሲደርስ እሹሩን ቀደ ደው ።

" እ ፤ ከየት ነው ? " አለው ሳምሶን ፤ አልጋው ላይ እንደ ተንጋለለ ።

" ከቤተሰቦቼ ነው " አለውና አቤልም ከመኝታው ጠርዝ ላይ ቁጭ ብሎ ያነብ ጀመር ።



" እንደምን አለህ ልጄ ? ይህ ጽሑፍ የእኔ የእናትህ መሆኑን አትጠራጠር " ይላል ፤ የደብዳቤው መግቢያ ። አቤል በእርግጥ የእናቱ ጽሕፈት መሆኑን ሊያምን አልቻ ለም ። ነገር ግን ከቤተሰቡ ውስጥ እንደዚያ ዐይነት የእጅ ጽሑፍ ያለው ሌላ ሰው እንደሌለ ገመተ ። በቅርቡ ከማይም ነት የተላቀቀ ጣት እንዳረፈበት በፊደል አጣጣሉ በመጫን የተጎዳው ወረቀት ያስታውቃል ። አቤል የሁለተኛ ዓመት ትምህርቱን እንደ ጨረሰ ወላጆቹን ሊጠይቃቸው ሔዶ በነበረበት ጊዜ ፤ እናቱ መሠረተ ትምህርት መጀመራቸውን ነግረውት ነበር ። ሆኖም ይህን ያህል እርኪ ውጤት ያሳያሉ ብሎ አልገመተም ነበር ። ሕፃናት ማንበብና መጻፍ ቢችሉ በዕድሜያቸው ምክንያት አያስደንቅም ። የወላጆቹ ከማይ ምነት መላቀቅ ግን ባህላችን ሆኖ ከደማችን እስኪዋሃድ ድረስ ለጊዜው ያስደንቀናል ።

' ተአምር ነው ! ' አለ አቤል በልቡ ፤ በዐይነ ሕሊናው በእጃቸው ብዕር ይዘው ከወረቀት ላይ ቃላት የሚያሰፍፉ እናቱን እየተመለከተ ። መንፈሱ በደስታ ተወራጨ ። ጥሩ ነገር ማየት ጥሩ ሕልም ያሳልማል ። አቤልም ለአፍታ ያህል በልቡ ትምህርቱን ጨርሶ ለኀብረተሰቡ ሊያበረክት የሚች ለውን የተቀደሰ ተግባር አሰበ ። ለብልጽግናና ለተቀደሱ ግቦች ሀገሪቱ የምትጠብቀው የጋራ እጅ ብሐሳቡ ታየው ። እናም አንዳች የደስታና የተስፋ ስሜት ሰውነቱን ወረረው ። ነገር ግን ደብዳቤውን ዘልቆ ሲያነብ በቅጽበት ስሜቱ ተለ ዋወጠ ።

" . . . ሳትጽፍልን ይህን ያህል ለመቆየት እንደምን አስቻለህ ልጄ ? ደብዳቤም እኮ ተስፋ ነው ። አደራህን የም ልህ ነገር ልጄ መመረቂያህ ቀን ሲደርስ እንድትነግረኝ ነው ። እንዲያው እንደ ምንም ብዬ እመጣለሁ ። ቆብህን የምትጭንበትን ያንን ወርቅ ቀን አጠገብህ ሆኜ እልል እያ ልኩ ማየት አለብኝ ። አሁንማ ዓመቱን አጋምሰኸዋል ፤ ትንሽ ነው የቀረህ ። አባትህ ጤናም የለው ። ሁለቱንም አህዮች ሽጦአቸው ውሎው ከቤት ሆኗል ። መንቀሳቀስ አልቻለም ። በአሁኑ ጊዜ የእሱ ጓደኞች በጋራ ተደራጅተው ያርሳሉ ። እንዴት የሞቀ ቤት አላቸው መሰለህ ! እርሶ ለባላባት መገ በር ከቀረ ወዲህ የገበሬው ቤት ሙሉ ነው ። ምን ይሆናል !

አባትህ ለዚህ አልታደለም ። ያ አስሙ በየጊዜው እየተነሣበት ያሠቃየዋል ። ቤተሰቡን ደግፋ የያዘችው ያቺ አንድ ላም ናት ። የሷንም ወተት ለተከራይዎቹ ማድረስ እንዴት ችግር መሰለህ ! ቤት ውስጥ የሚላክ ትንሽ ልጅ የለ ! እንዲያው መዋተት ነው ። ብቻ ግድ የለም ። ይኸው መውደቂያችን ላይ አምላክ አንተን አድርሶልናል ። እንግዲህ ምርኩዛችን ነህ ። እጅህን እየጠበቅን ነው ልጄ ! . . . ”

አቤል ደብዳቤውን ጨርሶ ማንበብ አልቻለም ። ደብዳቤው ላይ የሰፈሩት የሰቆቃው ጥሪ ፊደሎች እንባ ባቀረሩት ዐይኖቹ ጎልተው ብዥ ብዥ እያሉ ታዩት ። ወላጆቹ ዘንድሮ ይመረቅልናል ብለው ማሰባቸውና በአንጻሩ እሱ በዚህ ዓመት ትምህርቱን እንደማይጨርስ አድርጎ መገመቱ ግላዊ የአእምሮ ግጭት ውስጥ ከተተው ። ነገሮች ተምታቱበት ። ድህነት ! . . . ድህነት ! . . . ድህነት ! . . . ፍቅር . . . የዐይን ፍቅር ! . . . ትምህርት ! . . . ትምህርት !

‘ ድሀ ማፍቀር አይችልም ማለት ነው ? ’ ሲል ራሱን በራሱ ጠየቀ ። ‘ እምን አይችልም ፣ እንደምን ይችላል ! ከድህነቱ ለመፈወስ ይፍጨረጨራል ወይስ ፍቅሩን ያስታምማል ? . . . እኔ ግን ድህነቴን የማላውቅ ዕውር ነኝ ። ለድህነቱ መፍትሔ ሳላገኝ ፍቅር ጀመርኩ ። እና አሁን የወላጆቹ የሰቆቃ ጥሪ በጠበጠኝ ። . . . ግን ይታየኛል ። ለሁለቱም አልሆንም ። ከድህነቴም አልፈወስ ፣ ለፍቅርም አልበቃ ! . . . አዎ ! ለሁሉም አልሆንም ! ’ እያለ በሐሳቡ ተወራጨ ።

ድህነትና የዐይን ፍቅር በእሱ የተነሣ ከፊት ለፊቱ ቆመው ፍልሚያ የገጠሙ መሰለው ። ድህነት የተበጣጠሰ ጥብቆ ለብሶ ፣ ተባዮች በሰውነቱ ላይ ፈልተው ፣ የተንጨባረረ ጸጉሩን እየፎከተ “ አድንኝ ” እያለ የተጠጋው መሰለው ። በአንጻሩ ደግሞ ፍቅር የተኮሳቆለና የከሳ ሰውነቱን አኮራምቶ የተራቡ ዐይኖቹን እያስለመለመ “ አስታመኝ ” ብሎ የተጠጋው መሰለው ።

‘ ጥጋበኛ ድሀ ! ’ ሲል አቤል ራሱን ሰደበ ። ዐይኑ ላይ የተጠራቀመው እንባ እስካሁን ጠብ አላለም ። ያሳለፈው ረዥም የድህነት ዘመን ታየው ።



አቤል ለወላጆቹ አንድ ነው ። እናትና አባቱ ከተጋቡ በኋላ ብዙ ዓመት ቆይቶ ነው የተወለደው ። ለብዙ ዓመት ልጅ በማጣታቸው ምክንያት በቤተሰቡ ውስጥ ሰላም እንዳልነበረ ሲወራ ይሰማል ። አባቱ በእናቱ ላይ አንዲት መሽታ ነጋዴ ወሽመዋል እየተባሉ ይታሙ ነበር ። ይህን ያደረጉት ሚስታቸው ስለ መከኑ ፣ ልጅ ፍለጋ ነው የሚል ማስተባበያም ነበር ። ለማንኛውም የአቤል መወለድ በቤተሰቡ ውስጥ መጠነኛ ሰላም አወረደ ።

አባቱ አቶ ሙሉዬ ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩት በአህዮቻቸው ጭነት በማመላለስ ነበር ። አቤል ነፍስ ካወቀ በኋላ እንኳ የአገልግሎት ዘመናቸውን ጨርሰው የሞቱ ሦስት አህዮች ያስታውሳል ። አንዳንዴ እንደ እንስሳ ሳይሆን እንደ ሰው የቤተሰቡን ድህነት ተረድተው ለመርዳት የቆሙ ይመስለው ነበር ።

አብዛኛውን ጊዜ አባቱ የሚሠሩት በወፍጮ ቤት አካባቢ ነበር ። እህል በአህዮቻቸው ጭነው ወደ ወፍጮ ቤት ያደርሳሉ ። ወይም ደግሞ የተፈጨውን ወደየቤቱ ይመልሳሉ ። ሙሉዬ በዚህ ሁኔታ ከሚያገኙት ገንዘብ ውስጥ ከፊሉ የሚቀረው ወይዘሮ ይንጡ በዝናሽ ጠጅ ቤት ውስጥ ነበር ። አህዮቻቸውን “ ቶሽ ! ” በማለት ሲደርቅ የሚውል ጉሮሮአቸውን በመሽታ ጠጅ ሳያርሱ ወደ ቤታቸው ገብተው አያውቁም ። ጠጥተው ገብተው በሰላም አይተኙም ። የድህነታቸውን እልህ የሚወጡት በሚስታቸው ላይ ነበር ። ይጨቃጨቃሉ ። አብዛኛውን ጊዜ እህል አስፈጭተው ከሚያደርሱበት ቤት ስለሚኮራርሱ የቤታቸውን ምግብ አይበሉም ። የቤታቸውን አስተዳደር ችል የሚሉትም በዚሁ ምክንያት ነበር ። ይህም በመሆኑ የአቤል እናት አርፈው አልተቀመጡም ። ከገበያ ትናንሽ ሸቀጦችን እያመጡ ይቸረችሩ ነበር ። እኒህን ሁኔታዎች በማየት አቤል ገና በልጅነት ፍቅሩ ወደ እናቱ አጋደለ ።

አቶ ሙሉዬ ከአህዮቻቸው ጋር ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ ስለሚውሉ ፣ ማታ ቤት ሲገቡ የቦት ጫማቸው ሽታ እያስቀምጥም ነበር ። አቤል ዩኒቨርስቲ ከገባ በኋላ ፣ በጋራ የመኝታ ቤት ኑሮ ውስጥ የካልሲ ሽታ ሲነሣ የአባቱ ቦት ጫማ ትዝ

ይለዋል ። እሱም ከፍ ካለ በኋላ አብሮአቸው በየወፍጮ ቤቱ እየዞረ መጫኛ አስተሳሰር ተምሮ ነበር ። የአባቱ ምኞት አቤል ፈለጋቸውን ተከትሎ አህዮቹን እየጫነ በምትካቸው ቤተሰቡን እንዲያስተዳድር ነበር ። ከዚህ መሀይማዊ ፈለግ ያዳነው ጎረቤታቸው የሆነ አንድ መምህር ነው ። አባቱን አቶ ሙሉዬን እንደ ምንም ጎትጉቶ አቤል ትምህርት እንዲጀምር አደረገ ። የጨለማ ጉዞ የጀመረችውን ሕይወት መንጥቆ የብርሃን መንገድ እንድትይዝ አደረጋት ። ይህ መምህር ወደ ሌላ ክፍለ ሀገር ተቀይሮ እስከሔደበት ጊዜ ድረስ ለአምስት ዓመት ያህል ማንኛውንም የትምህርት ቁሳቁስ በመግዛት አቤልን ረድቶታል ።

ቤታቸው ከከተማው ወጣ ስለሚል ፣ አቤል ትምህርቱን የተከታተለው ብዙ መንገድ አቋርጦ አቶ ባርካ ድረስ እየመጣ ነበር ። አብረውት ከአንድ ሰፈር የሚመላለሱ ሌሎች ተማሪዎች ስለ ነበሩ የአህዮቹ ወሬ በክፍል ጓደኞቹ በቀላሉ ይሰራጭና "የአህያ ጫኚው ልጅ" እያሉ ያበሽቁታል ። ትምህርት ቤት አርፍዶ የደረሰ እንደሆነ "ለምን አህዮችችሁን አትጋልብም ?" ብለው ይተርቡታል ። በነአቤል አህዮች ላይ የማይነገር ምሳሌ አልነበረም ። ነገሩ የልጅነት ዘመን የቀልድ ቅንብር ነበር ። ነገር ግን ይህ ቀልድ ምን ሥነ-ልቡናዊ ጉዳትና መደባዊ ተጽዕኖ እንደ ነበረው አቤል መረዳት የጀመረው እየበሰለ ከመጣ በኋላ ነው ። የብዙዎቹ መራራ ቀልዶች ጠባሳ አእምሮው ውስጥ ቀርቷል ።

አቤል እያደገ በመጣ ቁጥር ድህነት ምን እንደሆነ የበለጠ እየተሰማው መጣ ። ድህነትን ጠላው ፤ ረገመው ። ድህነት የመሠረታዊ ፍላጎቶች ገደብ መሆኑ ገባው ።

ድህነት የበታችነት መሆኑን ተገነዘበ ። ድህነት የሕይወት እግር ብረት መሆኑን ተረዳ ። ድህነት ግማሽ ህይወት መሆኑን ዐወቀ ። እናም ከዚህ እግር ብረት ማምለጫው ብቸኛ መንገድ ትምህርት ታየው ። የሚደነቅ ግሩም ተማሪ ወጣው ። በአንደኛ ደረጃ ትምህርቱ ሁለት የተለያዩ ክፍሎች በድርብ ዐለፈ ። ይሁን እንጂ ፣ ሕይወቱን ለትምህርት ብቻ ስለሰጠ ማኅበራዊ ግንኙነቱ የላላ ነበር ። ከአካዳሚክ ሌላ በትምህርት ቤት ውስጥ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች አይሳተፍም ።



ይህም ነው የእሱንና የቤተሰቡን ድህነት ከማኅበራዊ ሥርዓቱ ነጥሎ እንዲመለከት አድርጎት የነበረው ።

በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ የኢትዮጵያ አብዮት ፈነዳ ። የለውጥ እሳት ተቀጣጠለ ። አቤልም በደመ-ነፍስ ይህ አብዮት በጋራ ለኅብረተሰቡ ፣ በግል ደግሞ ለወላጆቹ ድህነት መፍትሔ መሆኑን ተረዳ ። መሬት ለአራሹ ሆነ ። የነአቤልም መንደር ከከተማው ወጣ ያለ በመሆኑ አባቱ በማኅበር ተደራጅተው እንዲያርሱ ለአባልነት ተጠይቀው ነበር ። ነገር ግን አቶ ሙሉዬ ከአህዮቻቸው ጋር የተቆራኘ የረዥም ጊዜ ሕይወታቸውን መክዳት አልፈለጉም ። እናም ተደራጅቶ በማረስ ፈንታ ያንኑ የጭነት ሥራቸውን ቀጠሉ ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በዕድሜ መግፋትና መድከም የአህዮቹ ቁጥር እየቀነሰ መጣ ። የመጨረሻው ዜና ሁለቱን አህዮቻቸውን ሸጠው ከቤት መዋላቸው ሆነ ።

አቤል ከሐሳብ ጉዞው ሲመለስ በአካባቢው ያለው ነገር ሁሉ አስጠላው ። የተቀመጠበት አልጋ ቁልቁል የሚሰምጥ ፣ የተደረበው አልጋ ከላዩ ላይ የሚደረመስበት መሰለው ። ወንበሩ ላይ ተበታትነው የተቀመጡትን የትምህርት ቁሳቁሶችና በታይፕ የተባዙ ወረቀቶችን ማየት አልፈለገም ። ደብዳቤውን እንዳንጠለጠለ ክፍሉን ለቅቆ ወጣ ።

በምግብ አዳራሽ ውስጥ በትዕግሥት ፊት ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ ፍጹም የመንፈስ ጤንነት አልነበረውም ። ትምህርቱን ሳምንት ያህል አቋርጦ ነው የጀመረው ። ሰው አስጠልቶታል ። ማንንም ባያይ ፣ ከሁሉም ተነጥሎ ብቻውን ቢውል ይመርጣል ። ምንም ቢሆን ግን ትዕግሥትን በሆነ አጋጣሚ ሳያያት ፣ በልቡ የመልካሙን የዐይን ፍቅር ዜማ ሳያዜምላት አይውልም ። ከጥናት ጋር ፈጽሞ ተራርቀዋል ። የምግብ ፍላጎቱ እጅግ ቀንሶአል ። የተማሪውን ዐይን ስለሚፈራ ሁሉም በልተው ከጨረሱ በኋላ መጨረሻ ላይ ነው-ገብቶ የሚበላው ። አብዛኛውን ጊዜ ሳምሶን ፣ "ጥቅሙን ያውቃላ !" አቤል ምግቡን ለኮፍ ለኮፍ አድርጎ ሲተው "አይ ያንተ ነገር !" ይልና የአቤልን ሰሀን ወደርሱ ይስባል ። አቤል ሳይበላም ሳምሶን ሲበላ በማየት ይደሰታል ። አጠቃላሉና አጎራረሱ ፣ ለምግብ ያለው ትልቅ ፍቅር ያስደንቀ

ዋል ። ሆኖም ሳምሶን የአቤልን እስከ መጨረሻ ቆይቶ መግባት አልወደደውም ። ምግቡ ይቀዘቅዛል ። አንዳንዴም ሊያልቅና ጎደሎ ጭልፋ ሊጨልፍለት ይችላል ። ያም ሲሆን ጥቅሙን ከጉዳቱ በማመዛዘን ዘግይቶ አብሮት ይገባል ።

የአቤል ሕይወት በመንፈስ ጭንቀት ብትወጣጠርም በእስክንድርና ጓደኞቹ ብርታት መጥፎ ሁኔታ ላይ ከመውደቅ ተጠብቃ ልትቆይ ችላለች ። የአሁኑ ደብዳቤ ደግሞ ያንኑ የላላ መንፈሱን የባሰ የሚረብሽ ሆነበት ። ስለ ምግብ ማሰብ ከተወ ሰንብቷል ። በደመ-ነፍስ ሆኖአል የሚንቀሳቀሰው ።

የመኝታ ክፍሉን ለቅቆ እንደ ወጣ እግሩ ያለምንም ዓላማ ወደ 'ኮሪደሩ' መስኮት መራው ። ዘወትር ጠዋት ትዕግሥትን በዓይኑ የሚሳለምበት የሕይወቱ መስኮት ! ሁለቱንም መስታወት ወለል አድርጎ ከፈተው ። መስኮቱ ሰፊ በመሆኑ አቤል ሰውነቱን ከወገቡ በላይ ወደ ውጭአውጥቶ ቁልቁል ተመለከተ ። ትዕግሥት በዚህ ሰዓት አትኖርም ። የሚያልፍ የሚያገድም ማንም ሰው የለም ። አካባቢው ጭር ብሎአል ። አቤል ጭር ያለውን አካባቢ ተመርኩዞ የሆነ ሰይጣናዊ ስሜት ሰፈረበት ። ምድራዊውን ሥቃይና ጭንቀት ለመገላገል ፣ ያለ ዓላማና ግብ በመዋዠቅ ላይ ያለችውን ሕይወቱን ዕረፍት ለመስጠት ፣ በድህነት የማቀቀች ፣ በዐይን ፍቅር የተጠመደች ሕይወቱን ለማሳረፍ ከቆመበት ሦስተኛ ፎቅ ቁልቁል የመፈጥፈጥ ሐሳብ መጣበት ። ሁሉ ነገር መራራ መስሎ ታየው ። የቤተሰቡ ድህነት ጥንትም የሚያውቀው ጉዳይ ቢሆንም ፣ ከራሱ ጋር በሚጣላበት ሰዓት ተጨማሪ ሰቀቃው ሆኖ በመቅረቡ በጠበጠው ። ከሁሉም ነገር መገላገል ታየው ። ግልግል . . . ግልግል ! ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ ነፍሱ የምታገኘው ጸጥታ ታየው ።

' አዎ ይታየኛል ! ለሁለቱም አልሆንም ። ከድህነቱም አልፈወስ ፣ ለፍቅርም አልበቃ ! ለማንኛቸውም አልሆንም ' አለ እንደ ገና በሐሳቡ ።

ሕይወቱ የትጋ ፍጻሜዋን እንደምታገኝ ለመገመት ሞከረ ። ፎቁን ዐልፋ ሳትጨርስ ፣ በአየር ላይ ወይስ መሬት



ከተፈጠፈጠ በኋላ ፣ ዐይኖቹ እንደ ገና እንባ አቀረሩ ። እንባውን ለመዋጥ ጥርሱን ነከሰ ። ግንባሩን አኮማተረ ። 'ሕይወት መራራ ሆና ሳለ ፣ ልንለያት ስንል ምን ያስለቅሰናል ? ' ሲል አሰበ ። ከሦስት ፎቅ ወድቆ መሬት የተከሰከሰ ጭንቅላት ፣ የተፈረካከሰ አጥንትና የተበጣጠሰ ሥጋ በሐሳቡ ታየው ። ሬሣውን ከበው የሚጯጯሁት ሰዎች ድምፅ ሰቀጠጠው ። በዐይን ፍቅር ራሱን የገደለው የአቤል ርካሽ ዝና ከዩኒቨርስቲው ዐልፎ በአካባቢው ሁሉ ሲወራ ፣ መምህራን ምሳሌ ሲሰጡበት ፣ አንዳንዶች ሲያዝኑለት ፣ አንዳንዶች ሲሥቁበት ቁልጭ ብሎ ታየው ። ያቺ ትዕግሥት እንዴት ትሆን ይሆን ?

" ምን እያደረግክ ነው ፣ አቤል ? " የሚል ድምፅ ድንገት ከኋላው ሲሰማ ፣ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፈንጅ እንደ ተያዘ ሰው ከው አለ ። የእስክንድር ማንደፍሮ ድምፅ መሆኑን ግን ለይቶታል ።

" እ ፣ ምንም ። እንዲያው ነው " አለው ፣ ቀስ ብሎ ፊቱን አዞሮ ።

እስክንድር ፣ አቤል እጅ ላይ ደብዳቤ ባየ ጊዜ አንዳች ጥርጣሬ ገባው ። ደብዳቤው ውስጥ አቤልን ያስደሰተው ወይም ያስከፋው ነገር እንዳለ በንቁ አእምሮው ገመተ ። ሊፈስ የደረሰ እንባውን ለመግታት በመታገል ደም የመሰሉት ዐይኖቹን ባየ ጊዜ ደግሞ የተሰፋ ስሜት እንዳለው አወቀ ።

" ደብዳቤው ከየት ነው የመጣልህ ? " አለው ፣ ቁልቁል ተወርውሮ እንዳያመልጠው የፈራ ይመስል ፣ ቀስ ብሎ እየተጠጋው ።

" ከቤት ነው " . . . አለና አቤል ፣ ሊቀጥል የፈለገውን ነገር መልሶ ዋጠው ። ጥቂት ሲያሰላስል ቆዩና እንደ ገና ፣ " እኔ እምልህ እስክንድር " አለው ።

" አቤት ? " አለ እስክንድር በደከመ ድምፅ ።

" ይህችን መራራ ሕይወት ለምን እንወዳታለን ? "

" ጣዕሟ 'ኮ ከምሬቷ ውስጥ ነው የሚገኘው " አለው ።

እስክንድር ፥ በልቡ የአቤልን ስሜት እያጠና ።

" ሲበዛስ ? መራራነቷ ሲበዛስ ? "

እስክንድር የአቤል ሁኔታ አላማረውም ። ፊቱ እየተለዋወጠ ፥ እንባውን የሚታገለው ዐይኑ ደብሱን ደም እየመ ስለ ሲሔድ ፥ የግንባሩ ሥራሥሮች እየተግተረተሩ ሲሔዱ ተመለከተ ። ቀስ ብሎ ግራ ክንዱን ያዘውና ፥ " ና ቆይ ። ስለ ሕይወት ቤት ውስጥ ሆነን እንጫወታለን " አለው ።

" መኝታ ቤቱ አስጠልቶኛል " አለ አቤል በምሬት ። " እዚያ መግባት አልፈለገም "

" ግድ የለም ፥ ከእኔ ጋር ስትሆን ትወደዋለህ ። ይልቅ ና እንግባ " አለና ጎተት አደረገው ። አቤል በልቡ ፥ ' ይህን ሰው የሕይወቴ ዘብ ያደረገው ማነው ? ' አለ ። አደጋ ላይ ባለበት ሰዓት መድረሱ በእርግጥም አስገርሞት ነበር ።

እነሱ ወደ መኝታ ክፍላቸው ሲገቡና ሳምሶን ' ጉል ቤው ' ሲወጣ በር ላይ ተገጣጠሙ ።

" ታዲያስ " አለው እስክንድር ፥ ለመጨበጥ እየፈራ ። ሳምሶን ሲጨብጥ እጅ እስኪያም አጥብቆ ካልያዘ ወይም ካልነቀነቀ አይሆንለትም ።

" ምን አባክህ ! ልተኛ ነበር እንቅልፍ እንቢ አለኝ ። ይቺ ስልቻዬ ስለ ጎደለች ነው መሰለኝ " አለው ፥ ወደ ሆዱ እያሳየ ።

" ታዲያ አሁን ወዴት ነው ? "

" ወደ ራት ነዋ ! "

" እንዴ ! ሰዓት ' ኮ ገና ነው " አለ እስክንድር ፥ በልቡ እየሣቀ ።

" ቢሆንም እዚያው ሔዶ ቀድሞ ሰልፍ መያዝ ይሻ ላል እባክህ " አለውና ጥሎአቸው ሔደ ።

" ወደ ውስጥ ሲገቡ ፥ ' ድብርት ' እየተነጫነጨ ነበር የቆያቸው ። "



" ስማ አንተ እስክንድር ፥ ይህንን ሰው ብታስታግሡት ይሻላል ። እኔ አሀያ አይደለሁም ። እሱ የማኅበራዊ ኑሮ ቅርጉም አይገባውም ። "

" ማንነው እሱ ? " አለ እስክንድር ፥ ማን መሆኑን ልቡ እያወቀ ።

" ይሄ ሳምሶን ነዋ ፤ ፎጨጨኝ ይሔዳል እንዴ ? አበ ዛው ' ኮ ! "

" ምን አጣላችሁ ? "

" እንጃለት ! ለራት እንሰለፍ አለኝ ። ገና ነው እቆያ ለሁ ስለው ፥ ' በይ እንግዲህ ፥ ቀለምሽን ምጠጭ ' ብሎ እግሬ ላይ ረግጦኝ ሔደ ። እኔ የናንተ ጓደኛ ነው ብዬ ነው እንጂ እከሰዋለሁ ። "

" ግድ የለም እንመክረዋለን " አለው እስክንድር ፥ ሣቁን ለመግታት እየታገለ ። የድብርት ተፈጥሮ ያሥቀዋል ። ተደብሮ ሰው የሚደብረውን ያህል ፥ አንዴ መልጎምጎም ከጀመረም መቆሚያ የለውም ። ካልነኩት ግን አይነካም ።

" ምከሩት ፤ ይሄ ማኅበራዊ ኑሮ ነው ። ተከባብሮ መኖር ይሻላል " አለ ፥ እንደ ሕፃን ልጅ ትከሻውን እየነቀነቀ ። አቤልም ጎምዛዛ ሣቅ ሣቀ ።

## ምዕራፍ ዐሥራሁለት

እስክንድር ከኑጋ ያጨሰውን ሲጋራ ብዛት ቆጠረ ። እኩለ ቀን ከመሆኑ በፊት ዐሥራ አንድ አጭሷል ። ብር ልመና በገባበት ቢሮ ሲጋራ እየሰጡ ይሸኙታል ። ዊንስተን ከሚያጨሰው ዊንስተን ፣ ኒያላ ከሚያጨሰው ኒያላ ፣ ቤንሰን ከሚያጨሰው ቤንሰን ፣ ከባለርዝማኑ ርዝማን እየተቀበለ ሲያጨስ ይውላል ። ለወትሮው እስከ ምሳ ሰዓት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ከሁለት ሲጋራ በላይ አያጨስም ነበር ። በዚህ ዕለት ግን በየጓደኞቹ ቢሮ ገብቶ የመጣበት ዓላማ ባልተሳካለት ቁጥር ፣ "ለማካካሻ" ሲጋራውን ሲለኩስ ቁጥሩን ዐሥራ አንድ አደረሰው ።

‘ ትርፉ መቃጠል ነው ! ’ አለና ከምሳው በኋላ በማጨስ ላይ ያለውን ዐሥራ ሁለተኛ ሲጋራ ግማሽ ወገቡ ላይ ቆርጦ ጣለው ፤ ኪሱ ውስጥ ሌላ ሲጋራ አልነበረም ። ነገር ግን አድራጎቱ ከንቱ ፉከራ መሆኑን ልቡ ያውቀዋል ። ሲጋራ ለመተው በርካታ ጊዜ ዝቷል ። በርካታ ጊዜ ምሏል ። በርካታ ጊዜ ኪሱ ውስጥ የቀሩ ሲጋራዎችን ሰብሯል ። ሙከራዎቹንም የሚያከናውነው አልኮል ሲጠጣ ወይም በልቶ ሲያበቃ ፣ ማለትም በከፍተኛ የጥማት ጊዜያቶቹ ነው ። ነገር ግን ውሎ አድሮ ፣ አሳሳች ጋባዥ ሲጋብዘው እምቢ ብሎ እጁን መሰብሰብ ያቅተዋል ። በዚህ በኩል ራሱን ገምቶ በቅቶታል ። ለሃያ ስድስት ዓመት ወጣት ስምንት ዓመት ያህል በሲጋራ ሳንባን ማቃጠል ፣ ምን ያህል ሕይወት ላይ መቀለድ እንደሆነ ይገባዋል ። ለራሱም በጣም የሚገርመው ግን ፣ ብዙ ሲቸገር ለሲጋራ ማጨስ ወይም ሲጋራ ጋባዥ አለማጣቱ ነው - ሱስ ምርኮኞቿ እንዳይከዷት ጾም ጸሎት እያደረገች ወይም ለአማልክት እየሰገደች የምትጠብቃቸው ይመስል ።

እስክንድር አሁን ስለ ሉስ ለመመራ-መር ጊዜ የለውም ። ከማርታ ጋር የተቃጠረበት ሰዓት ስለ ተቃረበ፣ሸሚዙን ቀይሮ ከርዳዳ ጸጉሩን እየታገለ ያበጥር ጀመር ። ጸጉሩ ቶሎ ስለማ ያድግ ማበጠሪያውን ማስገባት ብዙም አያስቸግረውም ። ነገር ግን ፣ ጊዜ የሚያጠፋበት ሲያበጥረው በሁሉም በኩል ተስተካክሎ አለ መቆሙ ነው ። የማበጠሪያው ጣቶች በአንድ በኩል ገብተው ከፊሉን ጸጉር ሲያስተካክሉት ፣ በሌላ በኩል ያለውን ያጎደጉዱታል ። እንዴ ተስተካክሎ ከቆመ በኋላ ግን ፣ ቀኑን ሙሉ የሚነቀንቀው የለም ። ሳምሶን ቤት ውስጥ አለ መኖሩ ነው እንጂ ፣ እስክንድር ጸጉሩን በሚያበጥርበት ጊዜ ትንሽ መለካከፍ ልማዳቸው ነበር ።

" አንተ ጸጉርህን ስታበጥር እንኳንስ የተኛ ሰው ሬሣ ትቀሰቅሳለህ " ይለዋል ሳምሶን ፣ የእስክንድርን ጸጉር ድምፅ በማጋነን ።

" ምን ታረገዋለህ ! የንጹሕ አፍሪካዊ ጸጉር ነው ፤ እኮራበታለሁ " ሲል እስክንድር ይመልሳል ።

" የንጹሕ አፍሪካዊ ምልክት ጸጉር ሆነ እንዴ ? "
" ሌሎችም መመዘኛዎች አሉ ። ይህም ግን ከመመዘኛዎቹ አንዱ ነው ። "

" ኪንኪ ጸጉር የሌለው ንጹሕ አፍሪካዊ አይደለም ያለው ማነው እባክህ ? "

" እኔ በበኩሌ ባለ ሉጫ ጸጉሮቹ የዘር ሥራቸው ያጠራጥረኛል ። እንዲያውም አንተ ጸጉርህን የምትላጨው ይህን ለመደበቅ ይመስለኛል " ይለዋል ። ሳምሶንን ለማብሸቅ ሆነ ብሎ የሚያቀርበው መከላከያ ነው ። ሳምሶን ሉጫ ጸጉር ቢኖረውም ሁሌ መላጣ ነው ። የስፖርተኝነት ምልክት አድርጎ ስለሚወስደው ጸጉሩን አያሳድግም ።

እስክንድር ተሞሻሽሮ ከመኝታ ክፍሉ ወጣ ። መንገድ ላይ ማንንም ማግኘት አልፈለገም ። አቤልና ሳምሶን ለምሳ የገቡት መጨረሻ ላይ ስለሆነ ፣ መመለሻቸው መቃረቡን ገመተ ። ስለዚህ እንዳያገኙት ከወትሮው በተለየ መን



ገድ ታጥፎ ሔደ ። ከማርታ ጋር የተቃጠሩት ወደ የካቲት 12 ሆስፒታል ከሚያስወጣው ከዩኒቨርስቲው ዋና በር አካባቢ ነበር ።

በመንገድ ላይ ሆኖ ፣ ከተገናኙ በኋላ የት እንደሚወስዳት ያሰላስል ጀመር ። ምንም ያቀደው ነገር የለውም ። መገናኘት ብቻ ! በጠዋት ተነሥቶ አልተሳካለትም ። መጨረሻ የሔደበት ጓደኛው ብቻ አምስት ብር ሰጠው ። እሷውም ኪሱ መኖሯን ካረጋገጠ በኋላ ፣ ' አሁን በዚች አምስት ብር ምን ይደረግባታል ? ' ሲል አሰበ ፣ ' እንኳንስ ቤት ለማውጣት ወንድ ጓደኞችም ቡና ለመጋበዝ አትበቃም ። ' ኪሱ በደረቀበት ጊዜ ከማርታ ጋር መተዋወቁ አበሸቀው ።

አሁን ገንዘብ ሊያገኝ የሚችልበት ምንም ምንጭ የለውም ። አባቱ ሞተዋል ። ከእናቱ ምንም ሳንቲም አይጠብቅም ። የምትደርሳቸው ግማሽ የጡረታ አበል እንዴት ከወር እስከ ወር እንደምታደርሳቸው ሲያስብ ይገርመዋል ። በዚያ ላይ አብሮ አቸው የሚኖር የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ የሆነ ታናሽ ወንድሙ አለ ። ትንሽም የሚረዳቸው ጅማ የሚኖር መጠነኛ ግርሰሪ ያለው አጎት ነው ። እስክንድር በክረምቱ ወራት ሊጠይቀው ሔዶ ሦስት መቶ ብር ሰጥቶት ነበር ። ሲቀበለው የዓመት ድርጎው መሆኑን ያውቃል ። ነገር ግን ሁለት ወር ያህል እንኳ አላቆየውም ። የክረምቱን ዕረፍት ጨርሶ ትምህርት ሲጀምር ሰማንያ ብር ብቻ ነበር ፣ ይዞ የገባው ። እሷኑም ወዲያው አጠናቀቃት ። ኪሱ ገንዘብ ማቆየት አይችልም ። ቶሎ ብትንትን አርጎ አጠናቆ ፣ ከዚያ በኋላ ጫማውና ቀለም ሳይተያዩ ፣ የልብስ ማጠቢያ ሳሙና እየተበደረ ፣ ሲጋራ እየወጋ ዓመቷን ያሳልፋታል ። ያለቦታው ያቃጠለው ገንዘብ የሚያንገበግበው እንዲህ እንደ አሁኑ ዐይነት የበሰለ እንጆሪ ቀርቦለት የሚቀጥፍበት እጅ ሲያጥረው ነው ። ድህነቱንና ሲያገኝም ብኩንነቱን እያነጻጸረ ፣ እንዲሁ እየተገረመ ይኖራል ።

ከማርታ ጋር ያላቸው ግንኙነት ፣ አቤል ምግብ አዳራሽ ውስጥ ከወደቀበት አጋጣሚ ጀምሮ እየዳበረ መጥቶአል ። ከሰላምታ መሰጣጠት ዐልፈው ቆመው ማውራት ፣ ወይም በቀልድ ተጎሻሽሞ ማለፍ ከጀመሩ ሰንብተዋል ። ባያት

ቁጥር ፣ ‘ ድርብ ሚና የምጫወትባት ቤት ’ ብሎ መፎከሩ አልቀረም ። ነገር ግን እስካሁን እንኳን ድርብ ፣ አንዱንም ሚና መጫወት አልቻለም ። አንድ አቤልን እረዳዋለሁ ብሎ ያሰበበት መንገድ ነበር ። ሆኖም ትዕግሥት ለማርታ የልቧን አውጥታ ስለማታጫውታት ፣ ከማርታ በቂ መረጃ ማግኘት አልቻለም ። በሌላ በኩል ደግሞ ፣ የእስክንድር ልብ ማርታን ለወሲብ ቢከጅላትም ፣ የወንድነት ስሜቱ የሴትነት ገላዋን እያየ ቢጓጓላትም ፣ ኪሱ ባዶ በመሆኑ ስሜቱን ለመግታት ይገደዳል ። እሷ ግን ኪሱን አላየችለትም ። ወይም ስሜቱን እንዲገታ አልፈቀደችለትም ። ባገኘችው ቁጥር ወንድነቱን ትፈታተነዋለች ።

አንድ ቀን ዝንጥ ብላ ከግቢ ስትወጣ አገኛትና ፣ “ ዎ ! ዛሬ ወደ ካምፓስ የምትመለሺ አትመስይም ” ሲላት ፤

“ መጠርጠሩስ ” አለችው ።

“ ማን ይሆን የታደለ ፣ አንቺን መሳይ ጽጌረዳ የሚቀጥፍ ? ” ሲላት በምጸታዊ አነጋገር ፤

“ ዕድል ሳይሆን ልብ ይጠይቃል ! ” አለችው ።

‘ እኔ እስክንድር ልብ የለኝም ማለት ነው ? ! ’ ብሎ በልቡ ፣ ኪሱን ሲዳብስ ሳንቲም እንኳ አልነበረውም ። እልህም የወንድነት ስሜትም ወጥረው ስለ ያዙት ፣ በማግሥቱ ጠዋት ተነሥቶ የሦስተኛ ዓመት ተማሪ በነበረበት ጊዜ ሃያ ስምንት ብር የገዛውን አንድ መጽሐፍ ይዞ ወደ አሮጌ የመጻሕፍት ተራ ሔደ ። ሲሆን ሃያ ካልሆነም ዐሥራ አምስት ብር ያወጣልኛል ብሎ የገመተውን መጽሐፍ ፣ “ ስድስት ብር እንግዛህ ” ብለው ወገቡን ቆመጡት ። በሽቆ መጽሐፉን ይዞ ወደ ቤቱ ተመለሰ ። ልብ ይጠይቃል ያለችውን እያስታወሰ ፣ ‘ እጅ ከሌለ ልብ ብቻውን ምን ያረጋል ’ አለ በሐሳቡ ። የወንድነት እልሁም ሆነ የስሜት እሳቱ በገንዘብ እጥረት ተዳፍኖ ከረመ ።

በቅርቡ ደግሞ ፣ ከትዕግሥት ጋር ሆነው ወደሚያጠኑበት ዋርካ ሲሔዱ እሱ ከዋናው ቤተመጻሕፍት ወጥቶ ሲመጣ ተገናኙና ፣ “ ወዴት ነው የምትሔደው ? ” ሲሉ ጠየቁት ። “ ወደ ሽንት ቤት ” አላቸው ።



ማርታ ትዕግሥትን አስቀድማ ወደ ኋላ ቀረት አለችና ፤ “ ያ ነገር አለህ እንዴ ? ” አለችው ።

“ ምኑ ? ” ብሎ ሲጠይቃት ሲል እያስካካች ስለ ሔደች እሱም ገባውና ብቻውን እየሣቀ ሔደ ።

ነገር ግን በሣቁ ውስጥ አንዳች ስሜት ተናነቀው ። ያቺን ዕለት ሳያድር ምሽቱን መኝታ ቤቷ ድረስ ሔዶ ማርታን አስጠራትና ፣ “ በይ እሺ ፣ መቼ ይመችሻል ? ” አላት ።

ጣራ በሚሰነጥቅ ድምፅ እያካካች ፣ “ ለምኑ ? ” አለችው ።

እሱም በልቡ ‘ ምናባቷ ታሾፋለች ’ እያለ ፣ “ አብረን ስንጫወት ለመዋል ነዋ ! ” አላት ።

የእልህ ስሜት እንደ ያዘው ስለ ገባት ፣ ብዙ ልትቀልድ አልፈለገችም ። “ ያው ቅዳሜ ከሰዓት ይሻላል ! ” አለችው ።

ቀጥሯት ሲመለስ ፣ ‘ አሳያታለሁ ! ’ እያለ በልቡ ይዝት ነበር ። ነገር ግን እጅ እንደሚያስፈልግ ልቡ አላጣውም ። እናም ሰሞኑን ገንዘብ የሚገኝበትን መንገድ ሲያሰላስል ቆይቶ የመጨረሻ ውሳኔው ሠራተኛ ጓደኞቹን ማስቸገር ሆነ ። ከእነሱም የተገኘችው አምስት ብር ብቻ ሆነች ።

እስክንድር ይህን እያሰበ ፣ በአንጻሩም ‘ እንዲህ ዐይነት ጭንቀት ውስጥ ከገባሁማ አቤልን መርዳቴ ቀርቶ እኔውም ሌላው አቤል መሆኔ ነው ’ እያለ ከኅሊናው ጋር እየተሟገተ ፣ ድህነትን እየረገመ ፣ ትምህርቱን ጨርሶ የሚመረቅበትን ጊዜ በልቡ እየመተረ ከቀጠሮው ቦታ ሲደርስ ማርታ ቀድማ ቆማ አገኛት ።

ቀድማው በመገኘቷ እንደ መገረም እንደ መደናገጥም ብሎ ፣ “ ዘገየሁ እንዴ ? ” አለና ጨበጣት ።

“ እይ ! እኔ ትንሽ ቀደም ብዬ ነው ። ፈረንጅ ነህ ” አለችው ።

“ ቀጠሮ አክባሪነትን ለፈረንጆች ብቻ ማን ሰጣቸው ? ” አላት ።

" ሥልጣኔያቸው ነዋ ! ቀጠሮ ማክበር ' ኮ የሥልጣኔ ምልክት ነው ። "

"ታዲያ ሥልጣኔ በስመ ፈረንጅ መች ሆነልሽ ? ከአሀያ የማይሻል ፈረንጅ ሞልቷል ' ኮ ፣ እኔ አበሻ ነኝ ፣ ጥቁር ነኝ ፣ ፈረንጅ አይደለሁም " አላት ።

" ክብር አይወድልህም " አለችው ፣ ንግግሩን ናቅ አርጋ ።

" ፈረንጅ መባል ለኔ ክብር ሳይሆን ስድብ ነው ። ማርትዬ ሙች እልሻለሁ ፣ ስድብ ነው ። እኔነቴ ክብር ያጣ ይመስለኛል ። ጥቁርነቴ መሠረተ ቢስ ወይም ማረገ - ቢስ ሆኖ የተቆጠረ ይመስለኛል ። "

" ማርትዬ " በመባሏ ደስ አላት ፤ እንኳን ወንድ ሴቶችም እንዲህ አቆላምጠው ሲጠሯት ትወዳለች ።

"ጉረኛ !" አለችው በግድየለሽነት አነጋገር ። " ይልቅ አሁን በየት በኩል እንሒድ ? "

" እ ! በየት በኩል እንሒድ ? " ሲል እስክንድር ቃሏን ስልት ባጣ ድምፅ ደገመና ፣ " ሲኒማ ልጋብዝሽ እንዴ ? " አላት በልቡ የገንዘቡን አቅም እያሰላ ።

" አይ ዛሬ ቅዳሜ ነው ፤ ሰው ይበዛል " አለች ።

" እንግዲያው በዚህ በኩል እንሒድና አንድ ቤት ቁጭ ብለን እንጫወታለን !" አላትና ፣ አስፋልቱን ተሻግረው ወደ ሰባ ደረጃ የሚወስደውን መንገድ ያዙ ። ወዲያው ሐሳቡ ውስጥ የመጣችለት ሰባ ደረጃን ወርዶ በስተግራ በኩል የምትገኝ አንዲት ስም የለሽ ካፌቴሪያ ነበረች ።

የማርታ አለባበስ አልማረከውም ። የሰውነቷን ቅርጽ ከፋፍሎ ዳሌዋን እያነጠረ የወንድነት ስሜት የሚያግል ወይም የጡቶቿን መግቢያ እያሳየ ልብ የሚሰልብ ልብስ አልለበሰችም ። ለለውጥ ያህል ጂንስ ሱሪ ከቀላልና አነስተኛ ቃኮ ጫማ ጋር አድርጋ ከላይ እጀ - ጉርድ ሸሚዝ ለብሳለች ።



አለባበሷም ከተማሪ ጋር መውጣቷም ፣ " ለለውጥ ያህል " ይመስላል ። እስክንድርም ስሜቱን የሚያነቃቃ ልብስ ባለመልበሷ በልቡ በሽቋል ።

" በል እሺ ጨዋታ አምጣ " አለችው በመንዝ ላይ እንዳሉ ። ለተወሰኑ ሴኮንዶች በሁለቱም ዘንድ ጸጥታ ሰፍና ነበር ።

" ታዲያስ ፣ ትምህርት እንዴት ነው ? " አላት ፣ የጨዋታ እርዕስት እንዴት እንደሚጀመር ግራ ገብቶት ።

" እባክህ ሌላ ጨዋታ አምጣ ። የትምህርት ወሬ ራስ ምታት ሆኖብኛል!" አለችው ።

" ምነው ? "
" አስጠላኝ ! ሰው ስንት ዓመት ይማራል ? "

" ዕድሜውን ሙሉ ነዋ !" አላትና ፣ ፈገግ ብሎ ፣ " ግን ' ኮ ትምህርት የሚጠላ ነገር አይደለም ። ካልሺስ በሕይወት ውስጥ እንደ ትምህርት ጣፋጭ ነገር የለም ። የዘመኑ እኛነታችን ራሱ የትምህርት ውጤት ነው ። በሕይወት ላይ ትምህርት ያላስከተለው ለውጥ ምን አለ ? እስኪ ከምንራመድበት አስፋልት ጀምረሽ አካባቢሽንና ዐለምን በዓይነ ሕሊናሽ ዳስሺው ። ዕድገቱና ሥልጣኔው ሁሉ የትምህርት ውጤት ነው ። የሰው ልጅ በትምህርት ኃይል መልሶ እስከ መፍጠር የደረሰበት ሰዓት ነው ። እና ትምህርት የሚጠላ ነገር አይደለም " አላት ፣ ዮናታን " ትምህርት የሚገላገሉት ዕዳ አይደለም " ያሉትን እያስታወሰ ። " በእርግጥ እኛ አብዛኛውን ጊዜ ትምህርትን የምንመለከተው ጨርሰን ከመገላገሉ አንጻር ነው ። ይህ ጠባብና ደካማ አመለካከት ይመስለኛል ። ትምህርት ሕይወት ነው ። አያልቅም ። እኛ እንድንጠላው ፣ ከግልግል እንድንቆጥረው የሚያረጉን ነገሮች የትምህርት መስክ አመራረጣችንና የትምህርት አሰጣጡ ሁኔታዎች ናቸው ። የትምህርት መስክ ጨብጦ መታየት የለበትም ። እያንዳንዱ የሕይወት እንቅስቃሴ የምትበለጽገውና የምታድገው በትምህርት ነው ። "

" ተወኝ ባክህ ! ይልቅ የናንተ ትዕግሥት ይገርመኛል ። ዩኒቨርስቲ አራት ዓመት መቆየታችሁ ። "

" ምነው ? እንዴት ? "

" በጭንቀትና በውጥረት ግቢ አራት ዓመት ሙሉ ? ትዕግሥታችሁ ይገርመኛል ። "

" ምን ታረጊዋለሽ ! የህልውና ትግል ነው ። ከሁሉም የማይረሳኝ የውጥረትና የጭንቀት ጊዜ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ በነበርንበት ጊዜ ያሳለፍነው ነው ። የገናን ማዕበል እስከናልፍ ድረስ ከካምፓስ ውጭ ብቅ ብለን አናውቅም ነበር ። ዕውቀቱ ሳያንሳቸው ጭንቀቱ ብቻ የሚጥላቸው ልጆች ነበሩ ። በተለይ እኔ አጠገብ ይተኛ የነበረ ልጅ እስካሁን ትዝ ይለኛል ። ሴሚስተሩን ሙሉ ልብሱን አውልቆ መኝታ ውስጥ ገብቶ አያውቅም ። መጽሐፍ ወይም ደብተር እንደ ያዘ ፣ ልብሱን ሳያወልቅ ፣ አልጋው ላይ ጋደም ይልና ማንበብ ይጀምራል ። እንቅልፍ እያንገላጀው ያነባል ፤ ጥቂት ቆይቶ ደብተሩን እንደ ያዘ ዐይኑን ይከድናል ። ደሞ ትንሽ ድምፅ ሲሰማ ይባንናል ። ያሳዝነኛል ። ' ለምን አትተኛም ? ከፈለግክ እኔ ሌሊት እቀሰቅስሀና ታጠናለህ ። አሁን ተኛ እለዋለሁ ። ' አይ ደህና ነኝ ' ይልና ዐይኑን በጣቶቹ ደባብሶ ማንበብ ይቀጥላል ። አፍታም ሳይቆይ እንደ ገና ያንቀላፋል ። እንዲሁ እንዳለ ያነጋታል እንጂ ፣ ጨክኖ ልብሱን አውልቆ በደንቡ አይተኛም ። ታዲያ የሚያጠናው ነገር እንደማይገባው ይሰማኝ ነበር ። በዚያ ላይ እንደዚያ ሆኖ አድሮ ጠዋት 'ሌክቸር' መቀበል አይችልም ። መጨረሻ ያው የገና ማዕበል ጠርጎ ከዩኒቨርስቲ አባረረው ። እሱስ ተገላገለ እንጅ ተባረረ አልልም ። ትንሽ ቢቆይ ያብድ ነበር ። የሚያሳዝነኝ ግን እምስቱን የትምህርት ዐይነት 'ፍላት' ነው የወጣው ።"

" ውይ ምስኪን ! " ብላ ማርታ ከንፈርዋን መጠጠች ።

" እዎ ! ታዲያ እንዲህ ዐይነቱ ችግር ከምን የመጣ ይመስልሻል ? ተማሪው ስለ ትምህርት ያለው ደካማ አመለካከት ፣ የትምህርት አሰጣጡና የተማሪው መመዘኛ ሥርዓት ፣ እንዲሁም የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ኋላ-ቀርነት ተደራርበው የፈጠ



ሩት ችግር ነው እንጂ ፣ ዩኒቨርስቲ በመሠረቱ የጭንቀትና የውጥረት ቦታ መሆን የለበትም ። ይልቁንም የጥበብና የምርምር ቦታ ነው ።

" ለማንኛውም " ብላ ፣ መናገር የፈለገችውን ሳትጨርስ አቋረጣት ።

" አዎ ! ለማንኛውም አሁን ያለው ምርጫ በተሰጠን የትምህርት ክልልና መመዘኛ ውስጥ ተወዳድሮ ማለፍ ነው ። ፈተናም' ኮ ተቃርቦአል ። ቢበዛ ሦስት ሳምንት ነው የቀረው ። በርትተሽ ማጥናት ነው ። "

" ማን ይፈራል ሞት ! " አለችው ።

" እንዴት ? "

" ማለቴ ፣ እኔ መጨነቅ አልፈልግም ። ደግሞም ኢትዮጵያ ውስጥ እንደማልቆይ ዐውቃለሁ ። "

እስክንድር በልቡ ፣ ' ይህ በእንክብካቤ የተያዘ ሰውነትሽ እንደምንስ ጭንቀት ይችላል ? ' እያለ ፣ " የት ትሔጂ ያለሽ ? " ሲል ጠየቃት ።

" ውጭ ሀገር ነው ። "

ሰባ ደረጃ ስለ ደረሱ ፣ ደረጃውን ሲወርዱ ማርታ የእስክንድርን ክንድ እንደ መደገፊያ አርጋ ያዝ አረገችው ። የእጅዋ ሙቀት በክንዱ ዐልፎ መላ ሰውነቱን ሲያዳርሰው ፣ 'ምነው ክንዴን ለቀሽ ወገቤን ወይም አንገቴን ብትደገፊ !' አለ በሐሳቡ ።

" ስኮላርሺፕ ልትጠብቂ አስበሻል እንዴ ? "

" ኖ ! ኖው ! ብቻ በሆነ መንገድ እሔዳለሁ ። "

" የት ? አሜሪካ ? " አላት በምጸት አነጋገር ። እሷን ከመሰሉ ሴቶች የሌላ አገር ስም አይጠበቅም ብሎ ነው ።

እንዳሾፈባት አልገባትም ። " አዎ ! አሜሪካን አገር ወንድሞቼ አሉ ። እንግሊዝ አገርም የአክስቴ ልጆች አሉ ። እኔ ግን የአሜሪካኑ ይሻላል ብዬ በዚያ በኩል እየሞከርኩ ነው " አለችው ።

" ቤተሰብሽ ሁሉ ውጭ ሀገር ናቸዋ ? " ሲል ጀርጂድ አረጋትና ፣ " ለካ ቅድም እኔን ፈረንጅ ነህ ያልሺኝ አንቺ ፈረንጅና ስለሚሰማሽ ነው " አላት ።

" ማሾፍህ ነው ? "

እንደ በሸቀች ገባውና ፣ " ማርትዬ ሙች ፣ ማሾፌ አይደለም የምሬን ነው " አላት ።

"ደግሞ እንድታቀላምጠኝ የፈቀደልህ ማነው ? ማንም ወንድ ሳያስፈቅደኝ ሊያቀላምጠኝ አይችልም ።"

" ውበትሽ እንዳቀላምጥሽ ሲያስገድደኝስ ? "
"ውበቴንም ለማድነቅ ቢሆን ፈቃድ ያስፈልጋል ።"
" በተለይ ሴቶች ! " አላትና ክንዱን የያዘችበትን እጅዋን ጭብጥ አርጎ ወደ ጎኑ አስጠጋት ።

" ሒድ ፣ ደረቅ ! "

" የት ልሒድ " ርጥብ !"

ሁሉንም " ደረቅ " ማለት ስለሚቀናት ፣ እሱ ደግሞ " ርጥብ " እያለ ያበሽቃታል ።

ደረጃውን ወርደው ወደ ግራ ከታጠፉ በኋላ ፣ " ከቤተሰቦችሽ ጋር ነው የምትኖሪው ? " ሲል ጠየቃት ።

ለምን ጠየቀኝ ብላ አልተመራመረችም ፤ ወይም አልተደናገጠችም ።

" ዳዲ የለም ። ወንድሞቼም እንደ ነገርኩህ ውጭ ናቸው ። እኔና እናቴ ብቻ ነን እዚህ ያለነው ።"

" አባትሽ የት ሔዱ ? " አላት በጎዘኔታ ዐይነት ።

" ሔቨን " አለችው ፣ መሞታቸውን ብቻ ሳይሆን መጽደቃቸውንም ለማስገንዘብ ።

እስክንድር አንዴ ፣ ዘሥነ - ልቡና ትምህርት ክፍለ - ጊዜ መምህሩ በነገራቸው ቀልድ ውስጥ ፣ በምድር ላይ ለድሀ የመጸወተው አምስት ሳንቲም ተመልሶለት ከገነት በር የተባረ



ረው ሰው ትዝ አለውና ፣ ' የማርታ አባት በምድር ላይ ብዙ ገንዘብ መጽውተው ነበር ማለት ነው ' ሲል በልቡ ቀለደ ።

" ግን ምን ሆነው ሞቱ ? "

" ምን ያደርግልሃል ? " አለችና አመንትታ ዝም አለች ።

እስክንድር ምክንያቱን መናገር እንዳልፈለገች ገባውና ፣ ምናልባት የአብዮቱ ባቡር ጨፍልቆአቸው ይሆናል ብሎ ዝም አለ ። ለጥቂት ሴኮንዶች ሁለቱም ዝም ተባባሉ ።

" አደራሽን ማርታ ! ፈረንጅ ሀገር ስትሔጂ ነጭ እንዳታገቢ " አላት እስክንድር ፣ ጥቂት ሲያስብ ቆይቶ ።

" ለምን ? ምነው ?"

ስም የለሽ ካፌቴሪያ በር ላይ ስለ ደረሱ ፣ እሷን አስቀድሚት ገቡና ጥግ ቦታ መርጠው ተቀመጡ ። ብዙ ሰው አልነበረም ። ሞቅ ያለ የፈረንጅ ሙዚቃ ቤቱን ያናጋዋል ።

አሳላፊው መጥቶ ፣ " ምን ልታዘዝ ? " ሲል ከፊታቸው ቆመ ። እስክንድር ፣ ማርታ እንድታዝ ቅድሚያ ሰጣት ።

" ከጭማቂ ዘር ምን አላችሁ ? " ስትል አሳላፊውን ጠየቀችው ።

" ለምን ሌላ ነገር አትጠጪም ? ቢራ ምናምን ? " አላት እስክንድር ፣ ለማግደርደር ያህል ።

"እኔ የፍራፍሬ ጭማቂ ነው የምፈልገው " አለችና

ወደ አሳላፊው ተመለከተች ።

" ፓፓዬና ብርቱካን " አለ አሳላፊው ።
" ለኔ የብርቱካን ጭማቂ " አለች ማርታ ።
" በል እሺ ፣ ለኔም እንደዚያው " አለ እስክንድር ።
አሳላፊው ከሔደ በኋላ እስክንድር ፣ " የሚበላስ ነገር ፣ ሳንድዊች ምናምን ? " ሲል አግደረደራት ።

" ምንም አልፈልግም " ካላችው በኋላ ፣ ልቧ ተንጠልጥሎ ከቀረው ጨዋታቸው ላይ ተሰቅሎ ስለ ነበር ፣ " ይልቅ

ቅድም የውጪ ዜጋ እንዳታገቢ ያልከኝ ለምንድን ነው ?” ስትል ጠየቀችው ።

“ ለምን መሰለሽ ” አላትና ፣ እንዴት እንደሚገልጽላት በመቸገር ዐይነት ትንሽ ከቆየ በኋላ ፣ “ኑሮሽ ጤናማ የሚሆን አይመስለኝም ” አላት ።

“ እንዴት ? ”

“ አየሽ ! አንቺና የውጪው ዜጋ የተወለዳችሁበት ፣ ያደጋችሁበትና የኖራችሁበት አካባቢ የተለያየ ነው ። ባህላችሁ ይለያያል ። በምግብ ዓይነት ወይም በአመጋገብ ሥርዓት ፣ በአለባበስ ሁኔታ ፣ በጨዋታ ዐይነቶች ፣ በመዝናኛ ስፍራ አመራረጥ ፣ በእንግዳ አቀባበል ፣ በልጆች አስተዳደግ ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ በአስተሳሰብና በማኅበራዊ ኑሮ አመለካከት ልትለያዩ ትችላላችሁ ። ትዳር ማለት ደግሞ እነዚህን ነገሮች መጋራት ነው ፤ እና በባህልም ሆነ በሥነ-ልቡናዊ አመለካከት ብዙ የተራራቁ ጥንዶች ትዳር የሚያምር አይመስለኝም ።”

“ አባባልህ ልክ ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን ማንም ሰው በጋራ የሚፈልገው ነገር አለ ። ያም ያማረ ፣ የሠለጠነና የበለጸገ ኑሮ ነው ። ስለዚህ የጋራ መሠረታችንን ወይም ግባችንን ጥሩ ኑሮ አድርገን አንዳችን ከአንዳችን መማር እንችላለን ።”

ሁለቱም የቀረበላቸውን የብርቱካን ጭማቂ ተጎነጩ ። አሳላፊው ሌላ የሚታዘዛቸው እንዳለ ለማረጋገጥ ጥቂት ከቆመ በኋላ ተመልሶ ሔደ ።

“ ምን መሰለሽ ማርታ ፣ ነገሩ እንዲህ እንደምታስቢው ቀላል አይሆንም ” ሲል እስክንድር ቀጠለ ። “ አየሽ ፣ የአሁኑ ኣንቺነትሽ ከረዥም ዓመት አኗኗርሽና አካባቢሽ የተገነባ ነው ። ይህን ግንባታ ማደስ ወይም መለወጥ በጣም ከባድ ነው ። ሊሆንም ቢችል እንኳ ከባድ ትግል ፣ ጠንካራ መንፈስና ብልህ ጭንቅላት ይጠይቃል ።”

“ እባክህ ተው ፣ ዋናው ነገር ፍቅር ነው ። በሁለቱም መሐል መፈቃቀር ካለ ይህ ችግር አይፈጠርም ። ”



“ ችግሩ ግን ፣ ፍቅሩ ፣ ራሱ ትክክለኛ ምንጭ የለውም ፤ እንዲሁ በስሜት እሳት ይጀመራል ። አብዛኛውን ጊዜ ደግሞ እንዲህ ዐይነቱ ጋብቻ ቁሳቁሳዊ ይሆናል ። የረዥም ጊዜ መጠናናትና መፋቀርም የለም ። በስሜት እሳት የተጀመረ ‘ ሚክስድ ማሬጅ’ ደግሞ ዘላቂነት የለውም ፤ ዓመት አብረው ከቆዩ በኋላ ፣ የስሜት እሳቱ (አንቺ ፍቅር የምትይው) ይቀዘቅዝና ለኑሮ ቦታውን ይለቃል ። በዚያ ሰዓት በስሜት እሳት ተሸፍኖ የቆየው ፣ በሁለቱ መሐል ያለው የአስተሳሰብ ፣ የአስተዳደግ እና የአኗኗር ልዩነት ብቅ ማለት ይጀምራል ። ይልቁንስ ይህ ዐይነቱ ጋብቻ ዘላቂነት ሲኖረው ያየሁት በጥብቅ ሃይማኖት በተሳሰሩ ሰዎች ላይ ነው ። ይህ የእምነት ጉዳይ ነው ። በአንድ ሃይማኖት ተከታይነት ተዋውቀው የተጋቡ አንድ ኢትዮጵያዊና አንዲት አሜሪካዊት ለረዥም ዓመት የሚያስቀና ትዳር እንደ ነበራቸው አስታውሳለሁ ። እንዲያውም መውለድ ማቆም በፈለጉበት ወቅት ብልቱን በቀዶ ሕክምና ያስመከነው ኢትዮጵያዊው ወንድ ነበር ። ይህም የሚያሳየን ከነሱ ውጭ ሰሆን መለኮታዊ ኃይል ተጫኝነት ተሳስረው መኖራቸውን ነው እንጂ ፣ የአካባቢ ፣ የአስተሳሰብና የባህል ልዩነት አስወግደዋል ማለት አይደለም ።”

“ ድንቄም ” እንደ ማለት ያህል ከንፈሯን አጣማ ብርጭቆውን አነሣች ። የጨዋታቸው አርዕስት ቢለወጥ በወደደች ነበር ። እስክንድር ግን አርዕስቱን ሊለውጥላት አልቻለም ። እንዲህ ዐይነት ክርክር ሲነሣ ደስ ይለዋል ፤ መላ ህዋሳቶቹ ይግላሉ ። ሐሳቡና ንጥብ አመታቱ እያደገ ፣ እየጠነከረና እየተወሳሰበ ሲሔድ ለራሱም ይገርመዋል ። ከዕድገቱ ፣ ከአካባቢውና ከትምህርት ቤቱ ብዙ ዕውቀት መቅሰሙን የሚያውቀው በእንዲህ ዐይነቱ የግለት ወቅት ነው ።

“ ደግሞም የዚህ ዐይነቱ የተደቀለ ጋብቻ ችግሩ በባልና ሚስቱ ላይ ብቻ አይቀርም ” ሲል ቀጠለ ፤ “ ይብሱን ችግሩ የሚጎላው በሚወልዷቸው ልጆች ላይ ነው ። ልጆቹ እያደጉ ሲመጡ ፣ ራሳቸውን ከየትኛው ወገን እንደሚያስቀምጡ ይቸገራሉ ። የሥነ-ልቡና ጠበብቶች ይህንን ችግር ፣ ‘ አይደንቲቲ ክራይስስ ’ ይሉታል ። ልብ ብለሽ እንደሆን አብዛኛውን ጊዜ ለብኩንነት ፣ ለአልኮል ሱሰኝነት ፣ ለሴሰኝነትና ለመሳሰሉት ርካሽ ተግባራት የሚጋለጡት ከእንዲህ

ዐይነት ቤተሰብ የወጡት ወይም እኛ ክልስ የምንላቸው ናቸው ። ስለ ራሳቸው የሚናገራቸው የተዘበራረቀና የተበላሸ ስሜት ይመስለኛል ፣ ወደዚህ አድራጎት የሚመራቸው ።”

ማርታ ክርክሯን መሸሽ አልቻለችም ። ዝም ብላ በከፊል ሙዚቃ፣በከፊል እሱን ስታዳምጥ ትቆይና ፣ በነገር ወጋ ሲያደርጋት ወይም አነጋገሩ አልጥምሽ ሲላት አንድ ቃል ጣል ታደርጋለች ።

“ ልጆቹ እንዴት ራሳቸውን የሚያስቀምጡበት ቦታ ይጠፋቸዋል ? ከሁለት የተለያዩ ዜጎች ቢወለዱም የሚኖሩበትን አካባቢ መስለው ማደግ ይችላሉ ” ስትል ተጋተረችው ።

“ አይችሉም ! ” አላት በስሜት ጭንቅላቱን እየነቀነቀ ። “ የሚኖሩበት አካባቢ የእናታቸው ወይም የአባታቸው እንጂ የሁለቱም አይደለም ። ስለዚህ ከእንደዚሁ ዐይነት ቤተሰብ የተወለደ ልጅ ፣ ለምሳሌ እናቱ አበሻ ፣ አባቱ ፈረንጅ ቢሆኑና ኑሮው ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሆን በሙሉ ልቡ የኢትዮጵያውያንን አኗኗርና ባህል መቀበል ያዳግተዋል ። ግማሽ ፈረንጅነት ይሰማዋል ” ካለ በኋላ ፣ እስክንድር ትንሽ ሲያስብ ቆየና ፣ “ እንደሚመስለኝ ይህ ችግር በታዳጊና በበለጸጉ ሀገሮች መሐከል ያለው የልዩነት ችግር ነጸብራቅ ነው ። ፍርንጅና የዕድገት ፣ የሥልጣኔ የበላይነት ምልክት ተደርጎ ስለሚወሰድ፣ክልሱ ልጅም ይህ ተጽዕኖ ከራሱ ጋር እንዲጣላ ያደርገዋል ። ብቻ ምን ልበልሽ ፣ አሁን ባለንበት የተራራቀ የኑሮና የአስተሳሰብ ደረጃ (ሚክስድ ማሬጅ) በጣም አስቸጋሪ ነው ” አላት ።

“ ሊቅ ነህ ” አለችው ማርታ ፣ በልቧ እንደ ማድነቅ ዐይኗ ደግሞ እንደ ማሽሟጠጥ አድርጋ ።

“ ሊቅነት አይደለም ” አላት እስክንድር ኪሱን እየዳበሰ ። “ አንቺም ብትሆኚ መጽሐፍ አንብበሽ ልታገኚ የምትችዪው ዕውቀት ነው ። ”

ኪሱን የዳበሰው ሲጋራ ፍለጋ ነበር ። የክርክር ስሜቱ ሲግል ከንፈሩ እየደረቀ መጣ ። ሲጋራ ትዝ አለው ። ከምላ



በኋላ ሲጋራ ላለማጨስ ምሎ ፣ እፉ ላይ የቀረችውንም መስበሩን እንደ ቅዠት ወይም እንደ እንቅልፍ ልብ ውሳኔ ወስዶት ፤ አሁን ከኪሱ አንድ ብር አወጣና አሳላፊውን ሲጋራ እንዲያመጣላት አዘዘው ። የያዛት ገንዘብ ከቀረበላቸው ጭማቂ እንደምትተርፍ በልቡ አሰልቷታል ።

“ በነገራችን ላይ ፣ በስሜታዊ ብርገጋ ተንሣሥተው ነጭ እያገቡ ወደ ውጭ ሀገር የሚሔዱ አበሻ ሴቶች ዕጣቸው ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ ? ” ሲል ጠየቃት ።

“ ምንድነው ልትለኝ ነው ? ” አለችው ፣ ግንባሯን አኮማትራ ።

“ መጨረሻቸው ሽርሙጥና ነው ” አላት ድርቅ ብሎ ። “ አብዛኛውን ጊዜ ቅድም ባልኩሽ ምክንያቶች ስለ ማይስማሙ፣በመጨረሻ እዚያው ሽርሙጥና ይጀምራሉ ። ከአፍሪካ አግብቶ የወሰዳትን ሴት በጥንቃቄ የሚይዝ ነጭ ለሃይማኖቱ ያደረ ወይም ሕይወቱን ለሥራና ለምርምር የሰጠ ጥቂት ሰው ብቻ ነው ። ”

የማርታ ፊት ተለዋወጠ ። በአነጋገሩ እንደ ተከፋች ገባው ።

“ ምን ማለቴ መሰለሽ ? ” አለና እጅዋን ይዞ ሊያረጋጋት ሞከረ ።

“ እጄን ልቀቅና ማለት የፈለግከውን ተናገር ” አለችው ፣ ስልቷን ባጣ ድምፅ ።

“ ምን መሰለሽ ማርታ ፣ አንድ ልንክድ የማንችለው ነገር አለ ። ሰዎች ስንባል ብዙ ጊዜ ለጊዜያዊና እሳታዊ ስሜታችን ተገዥዎች ነን ። በሆነ እሳታዊ ስሜት ወይም ግንፍልተኝነት ተንሣሥቶ እናት ሀገርን ጥሎ መኮብለል ጉዳቱ የሚሰማው ቆይቶ ነው ። እስካሁን ድረስ በነጮች ሀገር ደልቶት የሚኖር ኢትዮጵያዊ አላየሁም ፤ አልሰማሁም ። አብዛኛው እዚህ ትውልድ ሀገሩ ውስጥ የሚንቀውን ሥራ ፣ እንደ ቤት ማጽዳት ፣ መስታወት መወልወል ፣ መኪና ማጠብ ሽንት ቤት ማጽዳትና የመሳሰለውን እየሠራ ነው የሚኖረው ።

ጥቂት ኢትዮጵያውያን በቂ ገንዘብና ቁሳቁስ ቢኖራቸውም ፣ ነጻነቱና ክብሩ ስለሌላቸው ሰላም አያገኙም ። በገንዘባቸው ብዛት ጎሊናቸውን የሚመክቱበት የአልኮልና የሐሺሽ ግንብ ሠርተው፣ ከዚያ ውስጥ እየዋኙ ይኖሩታል—መኖር ከተባለ!''

ማርታ የተዘበራረቀ ስሜት ተሰማት ። ዘመዶቿ ከውጭ ሀገር በሚልኩላት ደብዳቤ ደስተኞች እንዳልሆኑ ታውቃለች ። ስለዚህ እስክንድር የተናገረውን ናቅ አርጋ ልታልፈው አልቻለችም ። በሌላ በኩል ደግሞ ፣ የእሷ ስሜትና ፍላጎት ምንጊዜም ውጭ ነው ፤ ፈረንጅ ሀገር ነው ። ይህ ስሜት ስላየለባት ሐቁን ልትቀበል አልፈለገችም ።

" ይብላኝ ለምታገባት ! እኔ እንደዚህ አኛ አትመስለኝም ነበር " አለችው ።

" እንዴት ? " አላት እስክንድር ፣ ተገርሞ ።

" እንደዚህ ለጭቅጭቅና ለሙግት ሽንጥህን ገትረህ የምትቆም ዐይነት ሰው አትመስለኝም ነበር ።

በእርግጥ እንዳለችውም፣እንዳሁኑ ስራ አጋጣሚ አግኝተው ተጫውተው ስለማያውቁ፣እስክንድርን የምትገምተው እንደ ግድየለሽና ፣ ለኑሮውም ለሀገሩም ደንታ የሌለው ሰው አድርጋ ነበር ። አሁን ለኢትዮጵያዊነቱ እንዲህ ሽንጡን ገትሮ መቆሙ አስገርሞአታል ።

" ጭቅጭቅ'ኮ አይደለም " አላት እስክንድር ፣ የራሱ ያልሆነ ፈገግታ እያሳያት ። " ይልቅስ ሳናስበው ብዙ ትምህርት የተለዋወጥን ይመስለኛል ። "

አሳላፊው ሲጋራውን አምጥቶ ሰጠው ። እስክንድር በመጀመሪያ ማርታን ጋብዞአት፣ቀጥሎ ለራሱ ከፓኮው ውስጥ መዘዘ ።

" ይልቅ ይህን ሲጋራ የሚያስተውህ ወዳጅ ብታገኝ ጥሩ ነበር " ስትል ለከፍ አረገችው ።

" ያንችስ ምን ይባላል ? " አላት ፣ ክብሪት እየጫረ ። " እኔ እኮ አላጨስም ። ከሚያጨስ ወንድ ጋር ወይም



ጨዋታ ቦታ ስሆን፣እንዲሁ አጨሳለሁ እንጂ ሱሰኛ አይደለሁም " አለችው ።

እስክንድር እጫጫቷን አመነላት ። ሙሉውን ጭስ ነው ወደ ውጭ የምታስወጣው ።

" የሚገርምሽ ፣ ሁለት በቅርብ ማጨስ የጀመሩ ጓደኞቼን መከሬ አስትቼአለሁ ። ብዙ ዓመት ስላጨስኩት፣በግል ሕይወትም ሆነ በማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ የሚያስከትለውን ችግር በሚያሳምን ሁኔታ አቀርባለሁ ። መጥፎነቱን አስብካለሁ ። እኔ ራሴ ግን ማቆም አቃተኝ ። "

" ጠንቋይ ለራሱ አያውቅም ይባል የለ ? " ስትል አፌዘችበት ።

" ግድ የለም ። ጥሩ ሚስት ሳገባ ማጨሴን አቆማለሁ የሚል ተስፋ አለኝ ። "

" አንተ ያልተውከውን እሷ እንዴት ታስተውሃለች ? "

" ታስተወኛለች ። ጠንካራና ጥሩ ሴት ከሆነች እንኳን ሲጋራ መተው ሌላም ታስያርገኛለች ። ሴቶች ምን ያህል ኃይለኛ እንደሆኑ ዐውቃለሁ ።

" እንዴት ? " አለችው ።

ፊቷ በደስታ ሲፈካ ተመለከተ ። መልሱን በጉጉት እንደምትጠባበቅ ገባው ። ሊያኩራራት አልፈለገም ።

" እንዴት እንደሆነ አልነግርሽም " አላትና ፣ በልቡ 'ለምንድነው ሰዎች ኃያል መባል ደስ የሚለን ? ሌሎችን ማንበርከክ ፣ በቁጥጥራችን ሥር ማዋል ፣ እንዲሰግዱልን ማድረግ የምንፈልገው ለምንድነው ? የበላይ ሆኖ የመገኘት ስሜት ለምን ያጠቃናል ? ' እያለ ሲያስብ ቆይቶ ፣ " ግን'ኮ በባሎቻቸው ላይ ኃያል መሆን የሚችሉት ሁሉም ሴቶች አይደሉም ። ጥቂት ጠንካሮችና ልበሙሉዎች ናቸው " አላት ።

በመልሱ ባለመርካቷ፣ቀደም ብላ ዐይኖቿን ከእሱ ለማሸሽ ያህል ከማዶ ካለው ባዶ ግድግዳ ላይ ተከለች ።

" ለማሽኛ ማርቲና ? " አላት ፡ በቀልድም በቁልምጫም ዐይነት ።

" ደረቅ ! "

" ርጥብ ! "

እስክንድር ለአፍታ ያህል ዐይኑን ከዐይኗ ሳይነቅል ቆየ ። ከአፉ በሚያወጣው የሲጋራ ጢስ ቀለበት እየሠራ ሲወረውር ፡ በሰፊው ቀለበት ውስጥ ጠባብ ቀለበት ሠርቶ ሲያሾልክ ፡ የማርታ ጆሮ ሙዚቃውን እየቀዳ ልቧን ሲያወራው ፡ በዐይኗ የእስክንድርን የጢስ ቀለበቶች ፡ ተከትላ ጭልጥ ብላ ስትሔድ፡ ቀለበቶቹ እየሰፉ፡ እየተምዘገዘጉ ሔደው ሲበታተኑ ፡ እንደገና ዐይኗን ወደ እስክንድር አፍ መልሳ ሌሎች የጢስ ቀለበቶች ስትጠባበቅ — ደስ ሲል !

ማርታ ምርምሩና ክርክሩ ቀርቶ እንዲህ እንዲህ ዐይነት ጨዋታ ቢጫወቱ ደስ እንደሚላት እስክንድር ያውቃል ። የወጡትም ለዚሁ ነበር ። ‘ ታዲያ ለምንድነው የማይዋጥላትን ክርክር እያቀረብኩ የማደርቃት ? ’ ሲል አሰበ ። ‘ ግን ዘብ በማጣቴና ከእሷ ጋር ሌላ ዐይነት ጨዋታ መጫወት ባለመቻሌ ያቀረብኩት ማካካሻ ይሆን ? ጎበዝ ነው ብላ እንድትወደኝ ይሆን ? ወይስ በእርግጥ የምርምርና የክርክር ጥማት ይዞኝ ነው ? ’ እያለ ሲያስብ ፡ የሷው ጥያቄ አባነነው ።

" እውነት እስክንድር ፡ ሚስት ታገባለህ ? "

" ምን ማለትሽ ነው ? " አላት በአጠያየቁ ተገርሞ ። " እንዴት አላገባም ? "

" ማለት ፡ በቃ ፡ እንዲያው ግድየለሽ ዐይነት ትመስላለህ ። የትዳር ስሜት ያለህ አትመስልም ። "

ምን ለማለት እንደ ፈለገች ስለ ገባው ፡ " ለአለባበሱ ብዙ አለመጨነቁ ? ሲጋራ ማጤስ ወይስ ሌላ ምንድን ነው ከቁም ነገረኝነት አምባ ያገለለኝ የመሰለሽ ? ወይም ደግሞ ሙሉ ሰው ለመሆን ፡ ጥሩ ዜጋ ለመባል የሚያስፈልጉ ሌሎች መመዘኛዎች ካሉ ብትገልጪልኝ ? " አላት ፡ ፌዝ በተቀላቀለበት አነጋገር ።



" እንደዚያ ሳይሆን ፡ እሱ አይደለ ! እንዲያው ዝም ብዬ ሳይህ ፡ በቃ ... "

" እንዲያው ዝም ብለሽ ስታዪኝ ? " ሲል ቃሏን ደገመና ፡ " ታዲያ ምኑን ነው የወደድሽው ? " አላት ።

" ሔድ ፡ ደረቅ ! "

" ርጥብ ! "

ሽፋፍና ልታልፈው ብትሞክርም ፡ እስክንድርን እንድትወደው ወይም እንድትቀርበው ያደረጋት ነገር ለራሷም ግልጽ ሆኖ አይታወቃትም ። በቁመናው አልተማረከችም ። ጸጉሩ በእሷ ዐይንና አስተሳሰብ የሚጠላ ‘ ኪንኪ ’ ነው ። ለአለባበሱ ብዙም ደንታ የለው ። አስተሳሰብና ዕውቀቱን ለመታዘብ ከዚህ ቀን በፊት ዕድል አላገጠማትም ። ታዲያ ምኑን ነው የምትወደው ? የአቤል ጓደኛ በመሆኑ ? በዲግሪ ለመመረቅ የደረሰ ተማሪ በመሆኑ ? ወይስ ካያት ቀን ጀምሮ ወዲያውኑ በፍቅር እግሯ ሥር ስላልወደቀላት የእልህ ፍቅር ይዞአት ? . . . በተምታታ ሐሳብ ጭልጥ ብላ ሔደች። ከሚንቋት ወንዶች ጋር የእልህ ፍቅር ስለሚይዛት ይሆን አዝማሚያ ትፈራዋለች ። ነገር ግን እስካሁን ከእስክንድር ጋር ያላቸው ግንኙነት ከዚያ የሚያደርስ ባለመሆኑ በእልህ ፍቅር ልትደመድመው አልቻለችም ።

" ስሚ እንጂ ማርታ " አላት እስክንድር ፡ ከፓኮው ሌላ ሲጋራ እየመዘዘ ፤ " አንድ ነገር እጠይቅሻለሁ ብዬ ባገኘሁሽ ቁጥር እረሳዋለሁ ። "

" ምንድን ነው ? " አለችው ፡ የወፊ ህዋሳቶቿ መነቃቃቸው በገጽታዋ ላይ እየተነበበ ።

" ያቺ አጠር ወፈር ያለች ቀይ ልጅ ፡ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ፡ ጓደኛሽ ነች ፡ አይደል ? " አላት ስሟን እንደማያውቅ ሁሉ ።

" እ ፡ ቤቴ ? "

" አዎ ፡ ቤተልሔም ። እሷ ልጅ ‘ሊክቸረሯን’ አውርዳ ዋለች የሚል ወሬ ሰምቼ . . . "

የማርታ የነገር መቀበያ አንቴናዎች ሽቅብ ተቀሰሩ ። በቅናት የተወጣጠረው ሰውነቷ ተቆነጠነጠ ። በጆሮዋ ብቻ ሳይሆን በመላ ሰውነቷ እንደምታዳምጥ ሁሉ ፣ ፊቷን እስክንድር ፊት ደቀነችው ። የሐሜት ወሬ ሲጀመር ለመስማት ካላት ጉጉት የተነሣ ቅንድቦቿ ይርገበገባሉ ።

" ማን ነገረህ ? አቤት ወንዶች ፣ እኛን ትሳደባላችሁ እንጂ ፣ እናንተ'ኮ የባሰ ወሬኞች ናችሁ ! "

" እንደዚያ ሳይሆን ፣ በጨዋታ መሐል ተነሥቶ አንድ ጓደኛችን ነው የነገረን ። ሳምሶን 'ጉልቤውን' ታውቂዋለሽ ? '

" አዎ ፣ ያ ብዙ ጊዜ አብሮአችሁ የሚሔደው ስፖርተኛው ልጅ . . . ዐውቀዋለሁ "

" እሱ ነው የነገረኝ ። ከቤቲ ልሒም ጋር አንድ ዲፓርትመንት ውስጥ ስለሆኑ ሁኔታውን ያውቃል ። ወሬው ከዲፓርትመንቱ ተማሪዎች ጆሮ ደርሷል ። "

" የወለጋ ልጅ ነው ፣ አይደል ? " አለችው ፣ በምጸታዊ አነጋገር ።

" እኔ እንጃ ፣ እኔ የማውቀው በኢትዮጵያዊነቱ ነው ። ለማ ካብት ይመር ይባላል ። "

" አዎ የወለጋ ልጅ ነው ሲሉ ሰምቻለሁ ። ብታይ ወዶ እት ሊሞት ነው ፤ አብዶላታል ። "

" እሱን ተይው ! መቼም ሴቶች ቆዳችሁን ማዋደድ ታውቁበታላችሁ ። ተወደድን እንጂ ወደድን አትሉም ። "

" ሒድ ደረቅ ! እኔ የታዘብኩትን ነው የምነግርህ ። እንዲያውም ካላገባሁሽ እያለ ያደርቃታል ። "

" ታዲያ ለምን አታገባውም ? አግኝታው ነው ? ዘንድሮ እኮ ባል ውድ ነው ? " አላት እስክንድር ፣ ትንሽ ላሳርራት ብሎ ።

" ሒድ ጉረኛ ! ሚስት ለማግኘት ገና ከአሁን የበለጠ ደጅ የምትጠኑበት ዘመን ይመጣና " ብላ የብሽቀቷን ከተ



ናገረች በኋላ " ቤቲ እንደሆን ለጊዜው ነው እንጂ አታገባውም " አለችው ።

" ምነው ለምን ? "
" ውጭ ሀገር የመሔድ ሐሳብ አላት ። "
" እ ፣ ፈረንጅ ነዋ የምታገባው ? " አለና ቀለደባት ።

በሽቀችና አፍንጫዋንና ከንፈሯን አገናኝታ "እኝኝዋ!" አለችው ።

እስክንድር ሣቀና ፣ 'በድን ሥጋችሁ ነው እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ልባችሁና ነፍሳችሁ አውሮፓ ገብቷል ፣ አይ የኛ ዘመናውያን !' አለ በልቡ ።

"እኔ እንደ ሰማሁት ከሆነ ፣ ለማ በቤቲ ልሒም ምክንያት ከተማሪዎቹ ጋር ግጭት ውስጥ ገብቷል ይባላል " አላት ።

" የምን ግጭት ? " ስትል ግንባሯን አኮማትራ ጠየቀችው ።

መልሱ ቀጥተኛ አልነበረም ። " ፍርሀት የሚያስከትለው ግጭት ይመስለኛል " አላት ።

" አልገባኝም ። "

"ምን መሰለሽ ፣ ሳምሶን እንደ ነገረኝ ከሆነ ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለማ በተማሪዎቹ ላይ የሚያሳየው ጸባይ ተለዋውጧል ። ቀድሞ ክፍሉ ውስጥ ገብቶ አስተምሮ ከመውጣት በስተቀር ፣ ከተማሪው ጋር ምንም ዐይነት ግጭት አልነበረውም ፤ አሁን ግን ቁጡነት ይታይበታል ። ለተማሪዎቹ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ቀና አይደለም ። ጥያቄ የሚጠይቁት ለማወቅ ሳይሆን ለተንኮል ይመስለዋል ። ከተማሪው ጋር እንደ አይጥና ድመት መተያየት ጀምሯል ። እንደሚመስለኝ ከሆነ ፣ የዚህ ሁሉ ምንጩ ተማሪዎቹ እሱ ከቤቲ ልሒም ጋር ያለውን ግንኙነት ያወቁበት እየመሰለው የሚፈጥረው ጭንቀት ነው ። አትኩረው የሚያዩት ተማሪዎች ሁሉ የሚያሙት ሊመስለው ይችላል ። ደግሞ ያሙትም ይሆናል ። የጸባዩ መለዋወጥና የግንባሩ መኮማተር ፣ ለፍርሀቱ የሚቀርባቸው መከላከያዎች ናቸው ። ብቻ አኳኋኑ ውስጣዊ ሰላም ማጣቱን ያሳያሉ ። "

ማርታ ፣ ‘ እኔ ምን አገባኝ ? ’ የማለት ያህል እንገቷን ቅንጥስ ፣ ትከሻዋን ነቅነቅ አርጋ ዝም አለች ።

“ ይገርምሻል በፊት ግሩም መምህር ነበር አሉ ። ታዲያ ምን ይሆናል ! ሴቶች የገባችሁበት ነገር ምን ጊዜም ቢሆን ሰላም አያገኝ ” አላት በፊቱም ባይገልጸው በልቡ እርር ብሎ ።

“ ምን ? ” አለችው ፣ እጿም ተቆጥታ ።

ምንም አልመለሰላትም ። ቂጣዋን ለማብረድ ዝም አላት ።

“ ተማሪው ትምህርቱን ትቶ እንዲያው ነገር መፈት ፈት ይወዳል ” አለችው ፣ በንቀት አነጋገር ።

“ ነገር መፈትፈት አይደለም ። ተማሪውን የሚመለከት ጉዳይ ነው ። ለብዙዎቹ ተማሪዎች ዩኒቨርስቲው ከዕውቀት ይልቅ ለማርክ መፋለሚያ ቦታ ሆኗል ። በዛ ላይ ሴትነትና ውበት ጣልቃ ገብተው ሲበጠብጡ ምነው አያናድድ ! ”

ፊቷ ላይ ከፉኛ መከፋት አነበበ ።

“ እምልሽ . . . ” ብሎ ፣ መናገር የፈለገውን ሳይጨርስ አቋረጠችው ።

“ እውኝ አንተ አስተማሪ ብትሆንና ከምታስተምራቸው መሐል አንዲት ልጅ ብትወድ አጋጣሚውን ከመጠቀም ትቆጠባለህ ? ”

እስክንድር ጥያቄው ድንገተኛ የሆነበትን ያህል ፣ ከው ብሎ ለጥቂት ሴኮንዶች አሰበ ። ፈዛዛ ሣቅ ሥቆ ፣ በልቡ ‘ ምን አስደነገጠህ እስክንድር ? ራስህን ትጠራጠረዋለህ እንዴ ? ’ እያለ ፣ “ አይመስለኝም ። ማርክ የነገሠበት ሥርዓተ — ትምህርት እስካልቀረ ድረስ ፣ እንዲህ ተማሪዎችን የሚከፋፍልና የሚያማርር ድርጊት የምፈጽም አይመስለኝም ” አላት ።

“ ጉረኛ ” አለችው ፣ ከቀድሞው ቀዝቀዝ ባለ ስሜት ። “ ጉራህ ከቁመትህ ይበልጣል ። ”



“ ማንም ሰው ቢሆን ለራሱ ከፍ ያለ ግምት ይኖረዋል ። እና ተሳስቼ ይሆናል ” ።

ሲናገር ድምፁንም ሆነ እሱነቱን ለምን እንዳዝናናው አልገባውም ። የሆነ ጽላሏዊ ስሜት ተጫጫነው ። በአንጻሩ ደግሞ የማርታ ገጽታ እየደመቀ ሲሔድ ተመለከተ ። ‘ ምን እንዲህ አስቦረቃት ? ሙዚቃው ይሆን ? ወይም ድምፁ መላ ላቱን ሰምታ የተረታሁላት መስሏት ይሆን ? ’ አለ በልቡ ። ሐሜትና ሙዚቃ የማርታን ሕዋሳቶች ምንኛ እንደሚያነቃቁ ገመተ ።

የሽሚዟን የደረት ቁልፍ ፈትታ ፣ ጡቶቿን ለእስክንድር ዐይን አጋለጠቻቸው ። ከተቀመጠችበት ባትነሣም ባለችበት ትከሻዋን እየሰበቀች ከሙዚቃው ጋር አብራ ታዜም ጀመር ። “ እታዎን ” የተጫወቱት “ ሽ. ኤዝ ኦል ” የሚል የእንግሊዝኛ ሙዚቃ ነበር ።

“ ሙዚቃ ትወጃለሽ ? ” አላት እስክንድር ፣ ዐይኑን ከጡቶቿ ላይ ለመንቀል እየታገለ ።

“ ሙዚቃ የሚጠላ አለ እንዴ ? ሕይወት የሌለው ፍጡር ካልሆነ በስተቀር ፣ ” አለችው ! እንቅስቃሴዋን ሳትገታ ። “ ማለቴ ፣ የመውደድ ደረጃ ሊለያይ ይችላል ። ”

“ እኔ ግን ይገርምሃል ፣ ሙዚቃ እንደ ነፍሴ ነው የምወደው ። በተለይ በዚች ሙዚቃ ትልቅ ትዝታ አለኝ ። ”

“ ከብዶቱ ምን ያህል ይሆን ? ” ሲል ቀለደባት ።

“ ደረቅ ! ” አለችውና ፣ “ የራሴ የሆነ ትዝታ ነው ” ብላ የትከሻ እንቅስቃሴዋን ሳታቆም ዐይኗን በጠረጴዛው ባዶነት ላይ ተክላ ፣ ጭልጥ ብላ ትዝታዋ ውስጥ ገባች ።

ከአንድ ዓመት በፊት ነበር ። ማርታ አንድ ወንድ ጓደኛዋ ቤት ስትሔድ ጓደኛዋ ከጥቂት ጓደኞቹ ጋር ያዘጋጀው ፓርቲ ላይ ደረሰች ። በአጋጣሚ የተዘጋጀ የጓዳ ፓርቲ በመሆኑ በቂ ቅንብር ስላልነበረው ፣ ሴቶች አልነበሩበትም ። ስምንት ያህል የመንደሩ የሚቀራረቡ ወንዶች ብቻ ራሳቸውን ለማዝናናት ያን ዕለቱኑ ያወጡት ፕሮግራም ነበር ። ማርታን

መልካም እግር ጣላት ። የአንዷት ሴት ከመሐከላቸው መግ
ኘት ሁሉንም አስደስታቸው ።

በመጀመሪያ ከእያንዳንዳቸው ጋር ተራ በተራ እየተነ
ሣች ስትደንስ ቆየች ። ለዳንስ ያላት ስሜት ከምንም የላቀ
ነው ። ወፍራሙ ሲያስፈጯት አውለው ዳንስ ላይ ቢያቀርቧት
ሌሊቱን ሙሉ ስትነከው ታድራለች ። በዕለቱም ጨዋታው
እየሞቀና የጎረምሶቹ ሰውነት እየጋለ በሔደ ጊዜ፣ ተራ መጠ
በቁ ቀርቶ ሁሉም አንድ ላይ እየተነሡ ይጨፍሩ ጀመር ።
ማርታም መሐላቸው ገብታ ሁሉንም ማጫወት ቀጠለች ።
ላባቸው ፊታቸውን እያጠበ ፣ ከአንገታቸው ሊቀነጠሱ
እየደረሱ ፣ ከወገባቸው እየተሸበረኩ ፣ ከእግራቸው እየተብ
ረከረኩ ዙሪያዋን ከበው ሲደንሱ ማርታ የላዕላይነት
ስሜት ተሰማት ። በሴትነቷ ተኩራራች ። ነገር ግን ኩርታ
ከመደነስ አልተቆጠበችም ። ይብሱን ፣ ከወገቧ በላይ በጡት
መያዣ ብቻ ዕርቃኗን ሆና እስከ በቃት ተፍነከነከች ።
ቦረቀች ፤ ተወዛወዘች ።

“ ሺ ኢዝ ኦል ” የሚለውን ሙዚቃ ስድስት ጊዜ ደጋ
ግመው ደነሱበት ። እሷን ከመሐላቸው እንዳረጓት እያንዳን
ዳቸው የሙዚቃውን ስልት በመጠበቅ ጣታቸውን ወደ ማርታ
እየጠቆሙ ፣ “ ሺ ኢዝ ዲስኮ ” አሏት ። ከሙዚቃው ጋር
እያንዳንዳቸው የዲስኮን ቃላት በተናጠል ይሉና በአንድነት ፣
“ ኦ ኦ ኦ . . . ኦ ” የሚለውን ድምፅ ሲደጋግሙ ፣ አንገቷን
እቅንታ ይብሱን ቁልቁል እየተሽከረከረች ትፍነከነክላቸ
ዋለች ።

ማርታ በርካታ የዳንስ ቀናትም ሆኑ ምሽቶች አሳልፋ
ለች ። ከሁሉም ይልቅ በዚህ ቀላል የዳንስ ቀን ፣ “ ዲስኮ ”
ጭንቅላቷ ውስጥ ተቀርጾ የቀረው፣ ምንም ሴት ባልነበረበት
አዳራሽ እሷ ፣ “ ዲስኮ ሌዲ ” ሆና በወንዶች መሐል እንደ
ጫኦት ተከባ ያሳለፈችው ዕለት ስለሆነ ነው ። ከዚያን ዕለት
ጀምሮ ለሴትነቷ ልዩ ግምት ሰጥታዋለች ።

“ ዳንስስ ትወጂያለሽ ? ” አላት እስክንድር ፣ ከትዝታ
ባሕር ውስጥ መግባቷን ሳያጤን ፣ የትከሻዋን መነቃነቅ
ብቻ እየተመለከተ ።



“ ጥ ! ነፍሴ ነው ! ” አለችና ፣ የሚቀጥለውን የእስክን
ድር ቃል በመጠባበቅ ከአንገቷ ቀና አለች ።

“ ጥሩ ነው ” አላትና ዝም አለ ።

“ አንተስ ? ”

“ እኔም እወዳለሁ ። በውጭ ሀገር ሙዚቃዎች እደንሳ
ለሁ ። የበለጠ ደስ የሚለኝ ግን ፣ በሀገር ባህል ሙዚቃዎች
ስጫወት ነው ” አላት ።

“ ኤፍ ! ” ብላ ፊቷን ወደዛ አዞረችና ፣ “ አቤት አቤት፣
እንዲያው ቁና ሙሉ ጉራ ! ” አለችው ።

“ ጉራ አይደለም ። ከምደንሰው የበለጠ እስክስታ እወ
ርዳለሁ ፤ አብዛኛውን ዐይነት የሀገር ባህል ጨዋታ እጫወታ
ለሁ ። በ “ ትዝታ ” አንጎራጉራለሁ ፣ “ ጉብልዬ ” ን
እዜማለሁ ፣ “ እየዬው ድማሙ ” ን እተከዝበታለሁ ። አንቺ
ግን እስክስታ መውረድ ቀርቶ የሀገርኛውን ዘፈን ግጥም
አንድ ቤት መምታት መቻልሽን እጠራጠራለሁ ” አላት
ፊቱ ላይ የፌዝ ሣቅ ብልጭ ድርግም እያለ ።

“ ማወቅም ሆነ መቻል አልፈልግም ” አለችው ፣ በግ
ድየለሽነት ትከሻዋን እየሰበቀች ።

“ ይሄንን ነው ’ ኮ የምልሽ ፣ አንቺ የማታውቂው አንቺ
ነትሽን ነው ። እኔ ግን እኔነቴን ሳላውቅ መኖር አልችልም ።
የሀገሬ ባህልና ጨዋታዎች የእኔነቴ ክፍሎች ናቸው ። አን
ዳንዴ ለብዙ ጊዜ አከታትዬ በውጭ ሀገር ሙዚቃ የደነስኩ
እንደሆን ከራሴ ጋር ጸብ እጀምራለሁ ። መሠረቴ የተናጋ
ይመስለኛል ። ባዶነት ይሰማኛል ። ባህሌን ንቄ ለውጪ
ባህል የተንበረከክሁ ይመስለኛል ። ”

የንቀት ሣቅ ሣቀችና ፣ “ ሐቀኛ ኢትዮጵያዊ ነህ ” አለ
ችው ።

“ አንቺ ግን ሁለቱንም አይደለሽም ” አላት እያ
ሾፈ ፤ “ ማለቴ ፣ አውሮፓዊትም ኢትዮጵያዊትም አይደለ
ሽም ። ”

የንግግሩ ክብደት አልተሰማትም ።

“ እስቲ እናንተው ሁኑበት ” ብላ ቀለደችና ፣ “ እውነት ግን ከልብህ ነው እንዲህ ሀገር ወዳድ ሆነህ የምትከራከረው ? ” አለችው ።

“ ከአንጀቴ ነው ” አላት ወደ ኋላው ለጠጥ ብሎ ። ራሷን ነቀነቀች ፣ “ ግን የውጭው ሙዚቃ የሀገር ባህሉ ምን አሰኘህ ? ሁሉም መዝናኛ እስከሆነ ድረስ ፣ በቃ ! ”

“ አዎ ሁሉም መዝናኛ ነው ። ለውጭዉ እየተገዙ የራስን ናቅ ማድረግ ግን ፣ ራስን መርሳት ይመስለኛል ። ከውጭ የምንቀበለውን ያህል የራሳችንንም ባህል ወደ ውጭ ብናንጸባርቅ ምንኛ ባማረብን ። በሀገርና በውጭ መካከል የባህል ልውውጥ መኖር እንዳለበት አምናለሁ ። ከአንድ ጎን ብቻ ሲመጣ ወይም ሲንጸባረቅ ግን ፣ የባህል ተጽዕኖ ይሆናል ። በምዕራባውያን ሙዚቃ ረገድ እኛ የተያያዝነው ይህን ይመስላል ።”

“ እረ በናትህ ! አርዕስት ቀይር እስክንድር ። ምን ሞዛዛው ነህ ! ልታደርቀኝ ነው እንዴ ያወጣኸኝ ? ” አለችው ፣ ከልቧ በሽቃ ።

“ እረ ላዝናናሽ ነው ማርትዬ ! ይልቅ ጭማቂውን ድገሚ ” አላት ልቧን ሊያሟሽሸው ።

“ በቃኝ ፤ ይልቅ እንሒድ ! ”

“ ቆይ እንጂ ተጫወቺ ! የት እንሔዳለን ? አይዞሽ አንድ ቀን እንጨፍራለን ።”

“ መቼ ? ” አለችው ፣ ዕለቱን በናፍቆት በመጠበቅ ዐይነት ።

“ መቼ ? መቼ ? ” እያለ ቃሏን በልቡ ደጋገመና ፣ “ ግድየለሽም ፣ አንድ ቀን ” አላት ።

“እኮ አንድ ቀን መቼ ? ” ስትል የገዛ ሐሳቡ አፋጠጠው ። ‘ እጅ አጠረኝ ፣ ኮረንቲ ብስብ ’ የሚባባሉት የልጅነት



ጨዋታ ታወሰው ። ምናልባት በሐሳቡ የሚገምተው ፣ የመመረቂያው ጊዜ በሚቀርብበት አካባቢ ነው ። ያኔ አጎቴ ለምርቃቱ ሥነ-ሥርዓት ልብስ ማሠፊያ ብሎ ገንዘብ እንደሚልክለት ይተማመናል ። እና ምናልባት ያኔ ! ግን ከዚያ በፊት ይቺ ልጅ ከዩኒቨርስቲው ወድቃ ብትባረርስ ? ነገሩ ሁሉ ከንቱ ዝማሬ መሆኑ አይደለም ?

“ ስማ አንተ እስክንድር ! ” ስትል ማርታ ከሐሳቡ አባነነችው ። “ ያሄ አቤል ለምንድን ነው ሲያየኝ ግን ባሩን የሚያኮማትረው ? ”

ይሉኝታ ይዞአት ነው እንጂ ፣ ከእስክንድር ጋር ከተገናኙባት ደቂቃ ጀምራ ከአሁን አሁን ላንሣው እያለች ስታስላስለው የቆየችው አርዕስት ነው ።

“ ይኮማተርብሻል እንዴ ? ” አላት እስክንድር ፣ ሁኔታውን እንደማያውቅ ሁሉ ።

“ እረ ብታይ እንዴ ጠላቱ ነው የሚያየኝ ! ”

“ ምን እሱ እኮ ከማንም ጋር ቢሆን ያን ያህል አይጫወትም ” አላትና ሐሳቡን ቀርጦ ፣ “ ለመሆኑ ትዕግሥት ደህና ናት ? ” ሲል ጠየቃት ።

“ ደህና ነች ፣ እሷም ብታያት የተዘጋች ናት ። ፈጽሞ የውስጥ ስሜቷን አትናገርም ። እኔ መቼም በመኝታ ክፍል የቅርቧ ነኝ ብዬ ብዙ ላደርግላት ሞከርኩ ። እሷ ግን ግልጽ አይደለችም ። ከአቤል ጋር ፍቅር እንደ ጀመረች ያወቅኩት ከስንት ማውጣጣት በኋላ መሰለህ ! ”

እስክንድር ለተወሰኑ ሴኮንዶች በትካዜ ዝም ብሎ ቆየ ። ምን እንደሚናገር ግራ ገብቶታል ። የአርዕስቱ መነሣት ቢያስደስተውም መፍትሔ የሌለው ድግግሞሽ ጨዋታ መሆኑ ስሜቱን ከፋፍሎታል ። አቤልን ለመርዳት በምን መንገድ ይቻላል ? ሁለቱም ስሜታቸውን ለሰው የማያካፍሉ ፣ የርስ በርስም ልሣናቸው ዐይናቸው ብቻ !

“ እጅግ ያስገርሙኛል ” አለችው ማርታ ፣ የእስክንድር ዝምታ ጨዋታውን እንዳያቆመው ፤ “ ፍቅር በረከ

ሰበት ዘመን ደግሞ ይህን ያህል መጨነቅ ። ያውም በዐይን ፍቅር ! ምን ከረፈፎቹ ናቸው ! ”

“ ከረፈፍነት አይደለም ፤ አያድርስ ነው ። በፍቅር ጀግንነት የለም ” አላት አምርሮ ።

“ ምነው ደርሶብሃል እንዴ ? ”

እስክንድር ምንም አልመለሰላትም ። ጥቂት ሲያስብ ቆይቶ ፥ “ ይልቅስ ልንረዳቸው የምንችልበትን መንገድ ብንፈልግ ጥሩ ነበር ” አላት ።

“ እንዴት ? ” አለችው ፥ የሱን ስሜት በማየት ለነገሩ አትኩሮት ሰጥታው ። “ እምልህ ፥ የልባቸውን እስከላጫወቱን ድረስ እንዴት መርዳት ይቻላል ? ”

“ አዎ ፥ ችግሩ'ኮ እሱ ነው ” አለና ፥ መፍትሔ ከጣራው ላይ የሚወርድ ይመስል - ጣራ ጣራውን እያየ ፥ “ ምን መሰለሽ ፥ እስካሁን አቤልን ለመርዳት የሚታገሉት ዮናታን ብቻ ናቸው ። ”

“ ዮናታን ? ” ስትል ግራ በተጋባ ስሜት አቋረጠችው ።
“ የፍልስፍና መምህር ። እኝያ ረዥም ቀይ ፥ ጸጉራቸው ትንሽ ገባ ያለ ሰውዬ ! ብዙ ጊዜ እንኳ ብቻቸውን ነው የሚሔዱት ። ”

“ እ . . . ዐወቅኋቸው ። ”

“ እንዴት ዐይነት ግሩም ሰው መሰሉሽ ። ታዲያ ምን ይሆናል ፥ ብቻቸውን ነው የሚፍጨረጨሩት ። አቤልን ለማዳን ሌላ በቅጡ የሚረዳቸው ሰው አላገኙም ። እኔን አንዳንዴ እየጠሩ ስለ ሁኔታው ይጠይቁኛል ። ነገር ግን በቂ መረጃና ድጋፍ ልሰጣቸው አልቻልኩም ። አቤል ታፍኖ መሞት የሚፈልግ ልጅ ነው ። ”

“ እውነት ፥ ምን ዐይነት ተፈጥሮ ነው ? ” አለችው ፥ ከፋኛ እንደ ተገረመችበት በሚገልጽ ስሜት ።

“ ተፈጥሮ አይደለም ። ከአካባቢው የወረሰው በሽታ ነው ። ፍቅር ምስጢር ተደርጎ በሚወሰድበት አካባቢ እስከ



ዶገ ድረስ ፥ እሱም ያንኑ ስሜት ነው የሚያንጸባርቀው ። በዚያ ላይ ደግሞ እኔ እንደሚመስለኝ ፥ አቤል ለፍቅር ጥሬ ነው ። ይህችኑ ትንሽ ዕድሜውን ሙሉ በሙሉ ደብተሩ ላይ ነው ያሳለፋት ። የሱን የባላገር ንጹሕ ስሜት ከእኛ የከተማ የትርምስ ሕይወት ጋር ልናወዳድረው አንችልም ” ካለ በኋላ ፥ ነገሩን ለማዘመድ አሰላስለና ፥ “ ሁለታችን ይልቅ አሁን እሱን ለመርዳት ብንችል ጥሩ ነበር ” አላት ።

“ እንዴት ? ” አለችው በጉጉትና ሞራል በተሞላበት ስሜት ። እንደ ማንኛውም ሕያው ፥ ሌላውን የመርዳት ጉጉት ተሰማት ። ገና ምንንም ሳትጀምረው ደስ ደስ አላት ። “ የሚቻል ከሆነ ፥ በደስታ ! ” አለችው ።

“ አዎ ፥ እንዴት መሰለሽ ፥ እኔና አንቺ በዘዴ ሁለቱን አገናኝተን ለማነጋገር ብንችል ። ”

“ እንዴት ? ” አለችው ፥ እንደገና ተቻኩላ ።

“ እኔና አንቺ አንድ የሆነ ቦታ እንቃጠርና አንቺ ትዕግሥትን ፥ እኔደግሞ አቤልን እዚያ ቦታ በዘዴ ይዘናቸው ለመምጣት እንሞክር ። በአጋጣሚ እንጂ በቀጠሮ የተገናኘን አናስመስለውም ። ”

“ እሺ መቼ ? ”

“ ነገ ነዋ ! ምን ጊዜ መስጠት ያስፈልገዋል ? ” አላት ፥ እስክንድርም ራሱ ተቻኩሎ ስሜቱ በደስታ እየተቁነጠነጠ ።
“ በስንት ሰዓት ? ”

“ ከቀትር በኋላ ፥ ወደ አሥር ሰዓት አካባቢ ። “ ዝም ብሎ አፉ ላይ የመጣለት የሰዓት ምርጫ ነበር ።
“ የት ቦታ ? ” አለችው ።

“ የት ይሻላል ? እ . . . እዚያ አንቺና ትዕግሥት የምታጠኑበት ዋርካ ሥር እያጠናችሁ ጠብቁን ፤ እኔ እንደ ምንም እሱን ይዤ እመጣለሁ ። ”
“ በደስታ ! ”

እስክንድር ከዚች ደቂቃ ጀምሮ ሐሳቡ ተቁነጠነጠ ። ከማርታ ጋር ካፊቴሪያው ውስጥ ጥቂት ሲጫወቱ ቆይተው

ሔዱ ። ከአቤል አርዕስት በኋላ ፥ ማርታ የምታወራለትን እን ዱንም ከልብ አላዳመጠም ። አቤልና ትዕግሥትን ለማገና ኘት ታላቅ ጥበብ የተከሠተለት መሰለው ። ነገ . . . እሑድ . . . ከአንድ ሌሊት በኋላ . . . አቤት ርቀቱ! ሐሳቡ በርር እሑድ ላይ ዐረፈ ። እዚያች ጥርካ ሥር ትዕግሥትና ማርታ የሚያጠኑ መስለው ሲጠብቋቸው . . . እሱ አቤልን አጅቦ ከተፍ ሲል . . . ተማሪ ሙሽሮች ከነሚዜዎቻቸው . . . ግን አቤል እምቢዮ አልሔድም ቢልስ ? ወይም ደግሞ ትዕግሥትን ሲያያት የኋሊት ቢበረግግስ ? . .



## ምዕራፍ አስራሦስት

እሑድ ጠዋት፥እስክንድር ማንደፍሮ ከእንቅልፉ ሲነቃ ከሳምሶን "ጉልቤው" በስተቀር ቀድሞት የተነሣ ሰው አል ነበረም ። ሳምሶን እንደ ልማዱ በጠዋት ተነሥቶ ስፖርት በመሥራት ላይ ነበር ።እስክንድር እንደ ነቃ ዐይኑን በጣቶቹ ጠራርጎ ሳምሶንን አጮልቆ ተመለከተው ። ሳቡ በግንባሩ ላይ እየወረደ ፥ መሬቱ ላይ ተንጋሎ ፥ እንገቱን በእጁ እየደገፈ ከወገቡ በመነሣትና በመተኛት የሆድ ጂምናስቲክ ይሠራል ። ሳምሶን ለስፖርት ያለው ፍቅር እስክንድርን ሁሌም ያስደን ቀዋል ። ጠዋት ጠዋት ቀድሞ ተነሥቶ ሰውነቱን ሳያፍታታ ምንም ቢሆን ወደ ውጭ አይወጣም ።

እስክንድር በሳምሶን እንቅስቃሴ ተነቃቅቶ ፥ "ስፖርት ለጤንነት ! " አለና ከመኝታው ውስጥ ተፈናጥሮ ወጣ ። ድካም ስለ ተጫጫነው ከአልጋው ለመነሣት የፈጠረው ዘዴ ነበር ። ልብሱን ለባብሶ ከጨረሰ በኋላ ፥ ክፍሉ ውስጥ ይንጎራደድ ጀመር ።

" ምነው ዛሬ በሌሊት ? " አለው ሳምሶን ፥ በእሑድ ቀን የእስክንድር ማልዶ መነሣት እንግዳ ነገር ሆኖበት ።
" አንዳንዴ ለውጥ ያስፈልጋል ። "

" የምን ለውጥ ? " አለ ሳምሶን ፥ ጂምናስቲኩን ጨርሶ ዱብ ዱብ በማለት ሰውነቱን እያዝናና ።

" አንዳንድ ሰንበቶችን ማልዶ የመነሣት ለውጥ ! " አለውና እስክንድር ወደ መስኮቱ ሔዶ ከፈተው ።

የጠዋት ፀሐይ፥ማር ቀጠሉን ልዩ ድምቀት ሰጥታዋለች። ከእሑድነቱም ሌላ ፥ ጠዋት እንደ መሆኑ መጠን በግቢው ውስጥ የሚንቀሳቀስ ተማሪ አልነበረም ። ለአታክልቱ ከፀሐይ ብርሃን ጋር ውበትና ድምቀት የሰጠው ጸጥታውም